አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

በአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሂደት ወዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና

## (በአጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


በ አካል ግርማ



መስከረም ፣ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ሂደት ወዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት
# የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና
## (በአጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

በአማርኛ  ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አማካሪ   ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)

መስከረም፣ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

በአማርኛ  ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ሂደት ወዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና

(በአጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ አካል ግርማ

የፈታኝ ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን________

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት “ሂደት ወዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና (በአጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ- ምረቃ መርሐ ግብር አማርኛን ለማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት፣ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ______________________________

ፊርማ፡- ______________________________

ቀን፡- ______________________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ደረጃ ከመልካም ስነ-ምግባር ጋር አስፈላገውን ድጋፍ ላደረጉልኝይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ሳይሰለቹና ደከመኝ ሳይሉ የጥናቱን ትክክለኛ አቅጣጫ በማመላከት ያለመሰልቸት በማንበብ አስፈላጊውን እርማትና አስተያየት በመስጠት ከፍተኛ እርዳታ ላደረጉለኝ  አማካሪዬ ግርማ ገብሬ (ዶር.) ያለኝን ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በተጨማሪም  ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው በተዘጋጀው መረጃ መሰብሰቢያ ተገቢ ምላሽ ለሰጡኝ በአጋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ ለምወዳቸው ጓደኞቼ፣ በትምህርት ቤቱ አስተዳደሮች፣ ጥናቱ ከግብ ይደርስ ዘንድ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለተባበሩኝ የጥናቱ ተተኳሪ የት/ቤቱ መምህራን፣ተማሪዎች፣የቋንቋ መምህራንና እንዲሁም በሃሰብም ሆነ በጽሑፍ ስራ ዕገዛ ላደረጉልኝ እና በስም ላልጠቀስኳቸው ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ


የሰንጠረዥ ማውጫ ........ vi

አጠቃሎ ........ viii

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. ሰበበ ጥናት ........ 2

1.3. የጥናቱ መላምቶች ........ 5

1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 5

1.4.1.ዓብይ አላማ ........ 5

1.4.2.ንዑሳን አላማዎች ........ 5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.7.የጥናቱ አደረጃጀት ........ 6

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ........ 8

2.1. የመፃፍ ክሂል ምንነት ........ 8

2.2. የመፃፍ ክሂል ጠቀሜታ ........ 8

2.3. ትውርታዊ ማዕቀፍ (Theoretical Frame work) ........ 9

2.4. የጽሐፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች ........ 9

2.4.1. የውጤት ተኮር አቀራረብ ........ 10

2.4.2. የሂደት ተኮር አቀራረብ ........ 14

2.5. የፅሕፈት ሂደት ደረጃዎች ........ 16

2.5.1.ቅድመ ጽሕፈት ........ 16

2.5.2. ረቂቅ ማዘጋጀት ........ 16

2.5.3. አርትኦ /የማጥሪያ ንባብ ........ 17

2.5.4.ህትመት እና አቅርቦት ወይም ትውውቅ ........ 17

2.6.የመፃፍ ክሂል አካላዊ ውቅር ........ 18

2.7.ዘውጋዊ የማስተማር ስልት እና የመጻፍ ክሂል ........ 19

2.8. የዘውግ- ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ሞዴል ........ 22

2.8.1. ዐውድን መገንባት ........ 22

2.8.2. ሞዴል ጽሑፍን መገንባት ........ 22

2.8.3. ጽሑፍን በጋራ መገንባት (Collaborative Construction of the text .......... 23
2.8.4. ፅሁፍን በራስ መገንባት .......... 25
2.8.5. በጽሁፍ ላይ ፅብረቃ (Reflecting on writing) .......... 25
2.9.የቀደምት ጥናቶች ቅኝት .......... 26
ምዕራፍ ሶስት .......... 29
የአጠናን ዘዴ .......... 29
3.1. የምርምር ንድፍ .......... 29
3.2. የጥናቱ ዓይነት .......... 30
3.2.1. የናሙና አመራረጥ .......... 31
3.2.2. የስልጠና መመሪያ .......... 33
3.2.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች .......... 33
3.2.4. የመረጃ አተናተን ስልት .......... 33
ምዕራፍ አራት .......... 34
የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ .......... 34
4.1. አጠቃላይ መረጃዎች .......... 34
4.2. ቅድም ትግበራ ውጤት .......... 35
4.3. ቅድም ፈተና ውጤት .......... 50
4.4. ድህረ ትግበራ ውጤት .......... 53
4.5. ድህረ ፈተና ውጤት .......... 62
.......... 68
ጠቃለያ፣ግኝት፣መደምደሚያ እና አስተያየት .......... 68
5.1. ማጠቃለያ ና ግኝት .......... 68
5.2. መደምደሚያ .......... 72
5.3. አስተያየት .......... 72
ዋቢ ፅሁፎች .......... 74
አባሪዎች .......... I

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ1. ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪ ................... 35
መጠይቅ (ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ) ........................................................................ 35
ሠንጠረዥ 2 ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪ መጠይቅ (ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ) ........................................................................ 37
ሠንጠረዥ 3. የመ/ሩ ሚና በተመለከተ ከቁጥጥሩ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ ........................... 39
ሠንጠረዥ 4. ቁጥጥር ቡድኑ ላይ የተደረገ የምልከታ ቼክሊስት የተገኘ ውጤት .................. 42
ሠንጠረዥ 5. ከሙከራው ቡድን የተገኘ መረጃ ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር ...... 43
የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ ........................................................................ 43
ሠንጠረዥ 6. የመ/ሩ ሚና ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ............................................ 46
ሠንጠረዥ 7. ከምልከታ ቼክሊስት የተገኘ ውጤት(በቅድመ ትግበራ) .................................. 49
ሠንጠረዥ 8. ቅድመ ፈተና ውጤት ........................................................................ 50
ሠንጠረዥ 9. የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት .......................................................... 52
ሠንጠረዥ 10. የሙከራው ቡደን ተማሪዎች ውጤት......................................................... 53
ሠንጠረዥ 11.ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ55
ሠንጠረዥ 12. የመ/ሩ ሚና ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ............................................ 58
ሠንጠረዥ 13. ከምልከታ ቼክሊስት የተገኘ ውጤት(ከሙከራ ቡድኑ) .................................. 61
ሠንጠረዥ 14. ድህረ-ፈተና ውጤት አንድ ........................................................................ 62
ሠንጠረዥ 15. የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት .......................................................... 63
ሠንጠረዥ 16. የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት............................................................ 63
ሠንጠረዥ 17. ድህረ-ፈተና ውጤት ሁለት ........................................................................ 64
ሠንጠረዥ 18. የቁጥጥር ቡድን........................................................................ 65
ሠንጠረዥ 19. የሙከራ ቡድን........................................................................ 66
ሠንጠረዥ 20. በሁለቱ ቡዶኖች መካከል የታዩ ለውጦች.................................................... 66

## የስዕላዊ ውቅር ማውጫ

ስዕላዊ ውቅር 2.1. የፅሕፈት ሂደት  ደረጃዎች ........ 18
ስዕላዊ ውቅር 2.2. የመፃፍ ክሂል አካላዊ ውቅር ........ 19
ስዕላዊ ውቅር 2.3 ዘውጋዊ የማስተማር ስልት እና የመጻፍ ክሂል ........ 21
ስዕላዊ ውቅር 2.4 የዘውግ- ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ሞዴል ........ 26

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ወዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና ፈትሿል፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ሙከራ ቢጤ የጥናት ንድፍ (Quasi expermental research design) በመጠቀም ለመፈተሽ ይቻል ዘንድ ተማሪዎችን በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድን በሁለት በመክፈል ጥናቱ ተካሂዷል፤ በመሆኑም ምሁራን ባነሷቸው ሀሳቦች በማኅልበት በዋነኝነት ፈተና በደጋፊነት ደግሞ የፅሁፍ መጠይቅና ምልከታ በመጠቀም መረጃ በመሰብሰብና መረጃውን የቲ-ቴስት የመተንተኛ ዘዴ በመጠቀም በአግባቡ ተደራጅተው ትንተና የተደረገባቸው ናቸው፡፡ የተገኘውም ውጤት እንዳመለከተው በሂደታዊ ዘውግ የተማሩት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በልማዳዊው (በመርሃ ትምህርቱ) ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተሻለ የመጻፍ ክሂላቸው እንዳሻሻሉ፣ በቂ ደረጃ ላይ እንደደረሰ፣ የመጻፍ ተሳትፏቸው የተሻሻለ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሂደታዊ ዘውግ የመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልን ማሻሻል፣ በቂ ደረጃ ላይ ማድረስና ተሳትፎቸውን መጨመር ተማሪዎችን ለደረጃቸው የሚመጥን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ ማድረስ ይቻላል የሚል አስተያየት ላይ ተደርሷል፡፡በዚህም በወጉ ያረሰ እንደልቡ ጎረሰ እንደሚባለው መምህራን ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን በተገቢ ሁኔታ አዳዲስ አሰራሮችን በመጠቀም በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ላይ መጠቀም ከቻሉ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት እንደሚቻል በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ለሰው ልጅ ብቻ የተሰጠ ሰብአዊ መግባቢያ ነው ። የሰው ልጅ ከእንሰሳት የሚለየው መግባቢያ ቋንቋ ስላለውና ይህም መግባቢያ ቋንቋ በስርዓት የተሰደሩ ድምጾች ስብስብ መሆኑ ነው። ይህን ቋንቋ ለማዳበር ትምህርቱ በስርዓተ ትምህርት ተቀርፆ በትምህርት ቤት ደረጃ ለተማሪዎች ይሰጣል። ይኸውም በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ራሱን የቻለ ዓለማ ስላለው ነው። ይህም አላማ በዋናነት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማስተማር ማዳበር ነው። እነዚህን ክሂሎች ጠቅለል በማድረግ Stren (1983፤506) የአፍልቆትና የመቀበያ ክሂሎች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ በማለት ይገልፃሉ ። ይህም ማለት የአፍልቆት ክሂሎች የምንላቸው መናገር እና መፃፍ ሲሆን የመቀበያ ክሂሎች የምንላቸው ደግሞ ማዳመጥ እና ማንበብ ናቸው። በመሆኑም መፃፍ ከአፍልቆት ክሂሎች አንዱ ሲሆን የዚህም ክሂል ትምህርት ዋና ዓላማ አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ገልፀዋል። እንደ ብራውን(2007) አገላለጽ የተግባቦት ሂደት እንዲፋጠን ከሚቻልባቸው ክሂሎች መካከል አንዱ መጻፍ ነው። ከዚህም ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ከአፍልቆት ክሂል አንዱ የሆነውን የመፃፍ ክሂልን ማጎልበት ተግባቦታቸውን ለማሳደግ ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ይህን በማስመልከት Tangperpoon (2009) መፃፍ፣ የተለያዩ ጽሐፋዊ ክንውኖች የመጨረሻ ውጤት የሆነ የሀሳብ ማስተላለፊያ እንደሆነ ገልጿል። ይሁን እንጂ በተለይ ከንግግር ክሂል ጋር ሲነፃፀር ብዙ ጥቅም የማይሰጥ ወይም ክሂሌን ለማስተማር በጣም አስቸጋሪ ተደርጎ ይወሰድ ነበር (Willson, 2003)። ይህ ክሂል ውስብስብና አስቸጋሪ ተደርጎ የሚታይበት ምክንያት ለትምህርትነት የሚቀርበው ፅሁፍ ከቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ ከዓረፍተ ነገር አሰዳደር፣ ከስርዓተ ነጥብ አገባብ፣ ከይዘት አደረጃጀት እና የሰዋሰው ህግን በተገቢው ቦታ ከመጠቀም ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ነው። በጥቅል ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበትና ተራክቦ የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ የቋንቋ መሳሪያ ነው (Byrne, 1990)።

የፅሁፍ ክሂል የቋንቋ ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያንሸራሽሩና እንዲያደራጁ የሚያግዝ ክሂል ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን የማጠቃለል፣ የመተንተንና አስተያየት የመስጠት ችሎታ የሚያዳብር መሳሪያ ነው፡፡ የመጻፍ ክሂል ሃሳብን ለሌሎች ለማስተላለፍ፣ትምህርትን ለመከታተል እና ቋንቋን ለመማር የሚያስችል መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል(ማረው፤1998)፡፡

ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እንዲኖራቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው፤ምክንያቱም የሚማሩትን ትምህርት በአግባቡ በመከታተል እና የተረዱትን፣ከሌሎች የእውቀት ምንጮች ያገኟቸውን መረጃዎች እና እውቀት በማስታወሻ ደብተራቸው ይዘው መረጃውን ማስታወስ በሚፈልጉ ሰአት መልሶ ለመከለስ እና ለማስታወስ ያስችላቸው ዘንድ የመጻፍ ክሂል በእጅጉ ያስፈልጋቸዋል፡፡እንደ ሬይምስ(1983)ትንተና ተማሪዎች ለምን እንደሚጽፉ በውል መገንዘብ እና ለማን እንደሚጽፉ ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ለዚህም የስራ እቅድ ማውጣት አለባቸው፡፡

ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ገና በለጋነት እድሜያቸው የሚለማመዱት የክሂል አይነት ነው፤ይህም ሲባል ፊደላትን በወረቀት ላይ ቅረጻቸውን አስተካክሎ ከመጻፍ ከዚያም ቃላትን ብሎም ዐ.ነገርን በመቀጠል አነቀጽ እና ሙሉ ምንባብን ከሚያንፂቸው መጻፍት በመጻፍ ሊለማመዱ ይችላሉ፡፡ ይህ ክሂላቸው እያደገ ሄዶ ሃሳባቸውን በማፍለቅ አዳዲስ ግጥሞችን፣ታሪኮችን፣ልቦለዶችን እንዲሁም ሌሎች መሰረታዊ የፈጠራ ጉዳዮች እና የመሳሰሉትን በጽሁ የመከተብ የተሻለ ክሂል እነዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህን ለማድረግ ተማሪዎች የሃሳብ ፍሰት፣ አደረጃጀት፣ የአንቀጽ አመሰራረት፣ አወቃቀር፣ የዐ.ነገር አወቃቀር፤ የቃላት አመራረጥ እና አጠቃቀምን በአግባቡ ሊረዱና ሊያዳብሩ ይገባቸዋል፡፡ የመጻፍ ክሂል በባህሪው ኪሂለ ብዙ ነው(ማረው፣2003)፡፡

## 1.2. ሰበበ ጥናት

ይህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሱት ምክንያቶች ከዚህ እንደሚተለው ተገልጿል፡፡ የመፃፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ወቅት የሚታዩ ችግሮች ከክሂሉ የውስብስብነት ባህሪ ብቻ የሚከሰቱ ሳይሆኑ ከስነትምህርታዊ ሂደቶች ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ናቸው፡፡ ክብሩ ታያቸው(2006)ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ“በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂ የመምህራን የማስተማር ዘዴ አተገባበር” ላይ በሰራው ጥናት በአማርኛ ቋንቋ

ትምህርት መፃፍን የማስተማር ዘዴ ትዕግስትና ሂደትን የሚጠይቅ ቢሆንም ተግባራዊነቱ ይህን ሁኔታ የተላበሰ እንዳልሆነ ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህ ስነትምህርታዊ ሂደቶች መካከል፤ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ አመራረጥ እና ትግበራ፣ የመምህሩ የማስተማሪያ ስልት፣ እንዲሁም የተማሪው የመማር ፍላጎት እና ስትራቴጂ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት እና የይዘቶች አመራረጥ የፅሁፍ ክሂሌን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነት ይወስኑታል (Silva, 1990)፡፡

ክዚሁ ጋር ተያይዞ ሌላው አጥኚዋ በ9ኛ ክፍል የብዙ ዓመት የማስተማር ልምዷ በመነሳት የተመለከተችውን የመፃፍ ክሂል ላይ የሚታዩ የተማሪዎች ዝቅተኛ ተሳትፎ ሲፅሩ በአግባቡ የአፃፃፍ ስርዓትን ተከትሎ መፃፍ  ያለመቻል ሁኔታ ላይ ሲሆን በዚህ ዓመት የጎላ ችግር ሆኖ መታየቱ ለዚህ ጥናት መነሻ ጉዳይ ነው፡፡  በተለይ የመጻፍ መልመጃዎችን በተገቢው ልክ ያለመረዳታቸውና ምላሽ ለመስጠት መቸገራቸው “እኛ መምህራን ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል የምናስተምርበት ስልት  ክፍተት  ይሆን?” የሚል ጥያቄ በአጥኚዋ አዕምሮ ውስጥ ጥያቄ በማጫሩ የተነሳ ነው፡፡ በተጨማሪም በዘጠነኛ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች ዳራቸው በሁለት መንገድ የመጡ ሲሆን ይኸውም ከአንድ እስከ ስምንተኛ ክፍል በኦሮሚኛ ብቻ እየተማሩ የመጡ እና በአማርኛ ቋንቋ ተምረው የመጡ በመሆናቸው በተለይ በኦሮሚኛ ተምረው የመጡት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ሲማሩ በከፍተኛ ደረጃ ሲቸገሩ በማየቴ የተነሳ ነው፡፡

የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችግር ስንመለከት ብዙ ተመራማሪዎች የችግሩን ጉዳት በተለያየ መልክ ጉዩን በጠልቀት ተመልክተውታል ለአብነት ያህል ተካልኝ ለማ (2009) ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና አለካካከት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ በመፈተሽ በዚህ የማስተማር ዘዴ በምዕራብ ሸዋ ዞን በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ በሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ለውጥ እነዳመጣላቸው በጠናታቸው አመላከተዋል፤ በተጨማሪም ዳባሽ ዮንስ (2011) የተባሉ አጥኚ በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በማተኮርና የተለያዩ አካሄዶችን በመከተል በጠናታቸው ለውጥ ማምጣታቸውን ገልፀዋል፡፡  መምህራን እንደሚሉት የተማሪዎችን ችሎታ የሚያሳድግ ወይም ችግራቸውን ሊቀርፍ የሚችል የመፃፍ አቀራረብ መኖር እንዳለበት ይስማማሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እንዲሻሻል ላለፉት ዓመታት የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በቀደሙት ጊዜያት የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረቱ ለሰዋሰው ትክክለኛነት ከፍተኛ ቦታ ይሰጥ ለነበረው ውጤት ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አቀራረብ የተማሪዎችን ፈጠራና የቋንቋ ክሂል ችላ በማለት የመፃፍ ውጤታማነትን ይለካ የነበረው በሚታየውን  የፅሁፍ እድገት ሳይሆን በሚገኘው የፈተና ውጤት ነበር፡፡

የመፃፍ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቀዲሚ ትኩረት ከሚሰጣቸው መሰረታዊ የክሂል ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚታሰበው የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው በሚያስችል ሁኔታ መማር እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት እየተሰጠ ባለባቸው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በፅሁፍ ሀሳባቸውን የመግለፅ ችግር ያለባቸው እንደሆኑ ስዩም (1988) እና ሀና (2003) ገልፀዋል፡፡

ከዚህ አንፃር በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ ለሚታዩ ችግሮች ብዙ ተመራማሪዎችና መምህራን ውጤታማ የሆነ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ የሚያሻሽል አቀራረቦች እዲኖሩ ይፈለጋል፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች በድርሰት ፅሁፍ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ተማሪዎችና መምህራን ብዙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢም በአጋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ለበርካታ ዓመታት ባስተማረችባቸው ጊዜያት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን እና ችግሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ መሄድን ማጤን ችላለች፡፡ በተለይም አጥኚዋ በትምህርት ቤቱ በቆየችባቸው ረጅም ጊዜያቶች የታዘበቻቸው ነገር ቢኖር ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች እንኳን ድርሰት የመፃፍ ክህሎት ሊያዳብሩ ይቅርና ስማቸውን እንኳ በአግባቡ በመፃፍ ሀሳባቸውን ሊገልፁ አለመቻላቸውን ለመረዳት ችላለች፡፡

የችግሩን መንስኤ በመፈተሽ የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም አስፈላጊ መሆኑን በማመን በመፃፍ ክሂል ትምህርት ዙሪያ የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶች በመዳሰስ በትምህርቱ አቀራረብ ላይ ዶክመት መኖሩን ለመረዲት ችላለች፡፡ በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል የተማሪዎችን ሀሳብን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ለማዳበር ያስችላል የተባለውን የዘውግ ተኮር አቀራረብ የአማርኛ ቋንቋ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ማስቻል አለማስቻሉን ለማረጋገጥ መፈለግ ለዚህ ጥናት ችግርና መንስዔ በመሆን እንደ አነሳሽ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በዚህ ክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ችግርን በዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ አቀራረብ መፍታት መቻል ወይም አለማቻልን ለመፈተሽ ተነሳስታለች፡፡

## 1.3. የጥናቱ መላምቶች

1. በሂደተ ዘውግ ተኮር እና በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል አቀራረብ በተማሩ ተማሪዎች መካከል ትርጉም ያለው ልዩነት የለም፡፡
2. በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል አቀራረብ የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ የፅሁፍ ክሂል ውጤት አላቸው፡፡
3. በሂደተ ዘውግ ተኮር የተማሩ ተማሪዎች በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ የፅሁፍ ክሂል ውጤት አላቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት ዓብይ እና ንዑሳን ዓላማዎች ያሉት ሲሆን ዓላማዎቹም በሚከተለው መልኩ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### 1.4.1.ዓብይ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአጋሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት የ9ኛ ክፍል ሂደት ወዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና መመርመር ይሆናል፡፡

### 1.4.2.ንዑሳን አላማዎች

ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ዓብይ ዓላማ መነሻ በማድረግ ጥናቱ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ንዑሳን አላማዎች ላይ ያተኩራል፡፡

1. ሂደት ወዘውግ ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር ያለውን ፋይዳ ይፈትሻል፣
2. ሂደት ወዘውግ ዘዴ በመጠቀም በተማሪዎች የመጻህፍ ትምህርት ላይ ሊያመጣ የሚችለውን የአመለካከት ለውጥ ይመረምራል፣
3. በመምህራን የዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ ሂደት የታዩ ችግሮችን ያመለክታል፣

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ግኝት አውድን ተጠቅሞ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ጥረት ለሚያደርጉ መምህራን እና ተመራማሪዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ጥናቱ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ የሚጎለብትበትን መንገድ ያሳድጋል፡፡ ተማሪዎች ለመፃፍ ክሂል አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡ መምህራን የመፃፍ

ትምህርት አቀራረባቸውን እንዲያጤኑት ያደርጋል፡፡ በመጨረሻም በክፍል ውስጥ ሂደታዊ ወዘውግአዊ ዘዴዎችን ለማቀናጀት

1. የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ክሂል የማሳደግ ዝንባሌ ያሳያል፡፡
2. መምህራን የዘውግ ተኮር የማስተማር ችግር እንዲቀርፉ ያስችላል፡፡
3. ወደፊት የመፃፍ ክሂልን ||ማሳደግ ለሚፈልጉ አጠኒዎች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡
4. ያጥኚዋን የጥናትና ምርምር ክህሎት ያዳብራል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን የአጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

የጥናቱን ትኩረት በሚመለከት የዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመፃፍ ትምህርት የተማሪዎችን ሂደተ ወዘውጋዊ በማቀናጀት ማስተማር የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ የሚኖረውን ሚና መመርመር እንዲሁም ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን በአጋሮ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9 ‘A’ 9ኛ ‘D’ ክፍሎች ላይ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት አምስት ክፍሎች ይዟል፡፡

የመጀመሪያው ምዕራፍ  የጥናቱ መግቢያ ሲሆን፡- በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ችግርና አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የቁልፍ ቃላት መግለጫ እና የጥናቱን አደረጃጀት የሚያጠቃልል ክፍል ይሆናል፡፡

ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝቶች ይዟል፡፡ እነዚህም፡- ትዕውርታዊ ማዕቀፍ እና  የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ሲሆኑ በዚህ ስር በዋነኝነት የማስተማሪያ ጽሁፎች፣ የትምህርቱ አቀራረብ፣ በመፃፍ ትምህርት ወቅት ከተለያዩ  አቀራረቦች አንፃር የመምህሩ እና የተማሪው ሚና እና ሌሎች ሁኔታዎች በስፋት ተዳሶበታል፡፡ የተዛማጅ ፅሁፍ ዋነኛ አላማ ለዚህ ጥናት ድጋፍ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ንድፈ ሀሳቦችን ለማግኘት ነው፡፡

ሶስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ንድፍ እና ዘዴ የተካተተበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር ጥናቱ እንዴት እንደተነደፈ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በስራ ላይ እንዴት እንደሚውሉ፣ መረጃዎች እንዴት እንደተሰበሰቡና እንደተተነተኑ ወዘተ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

አራተኛው ምዕራፍ ደሞ በሙከራ ጥናቱ (pilot study) የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚብራሩበት እና የሚተነተኑበት እንዲሁም ከሙከራ ጥናቱ የተገኙ ትምህርቶች የሚጠቃለሉበት ነው፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ አምስት ስር የጥናቱ ማጠቃለያ እና አስተያየቶች የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

### 2.1. የመፃፍ ክሂል ምንነት

ስለ መጻፍ ክሂል የተለያዩ የቋንቋ ሙህራን ከራሳቸው አተያይ በመነሳት የመፃፍ ክሂል በተላያየ መልኩ ገልፀውታል፡፡ Caroll (1999)የመፃፍ ክሂል ከአፍልቆት ክሂል አንዱና መደበኛ በሆነ መልኩ ከታች ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች  በተለይም የተማረው አካል ከትምህርት ተቋም ውስጥም ሆነ ውጪ አመለካከቱን፣ ስሜቱን ፣ እመነቱን፣ እሴቱን በአንፃሩ ቋሚ በሆነ ሁኔታ የሚከተብበት ብሎም ፍላጎቱን የሚያስተላልፍበት መሳሪያ ነው፡፡ ከሌሎች ክሂሎች የመፃፍ ክሂልን ማዳበር የሆነውን ለማድረግ ያሰብነውን በራስ መተማመን ስሜት ለማቅረብ የሚያስችልና ዕውቀትን ለሌላው ተሻጋሪ  እነዲሆን ማድረጊያ ስልት ነው Mojica (2010 ) በማለት ገልፆታል:: ዮናስ ስምና ሌሎችም (2001) ፅህፈት ማለት ንግግር ቋንቋን ለዘለቄታው ወይም ለተወሰነ ጊዜ በቋሚነት ቀርጾ የማኖሪያ ስልት ነው፡፡ ከዚህ ብያኔ የምንረዳው ጽህፈት የንግግር ቋንቋ እንዳይጠፋ የቋንቋ ድምጾችን በመጠቀም ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚረዳ መሳሪያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### 2.2. የመፃፍ ክሂል ጠቀሜታ

አበው ሲተርቱ "በቃል ያለ ይረሳል በወረቀት" ያለ ይወረሳል ይላሉ:: ካሉት የቋንቋ ኪሂሎች ውስጥ መጻፍ/ጽህፈት ለሰው ልጅ እጅግ መሰረታዊ እና አስፈላጊ የሚባለው የኪህል አይነት ነው፡፡ ጽህፈት ባይኖር አለም ዛሬ ላይ የደረሰችበት ደረጃ እንኳን ላት ደረስ ትችል ይሆናል፤ምክንያቱም ሃሳቦች ወይም የችግር መፍቻ ብልሃቶችን መፈለግ በራሱ የሚወስደው ጊዜ ቀላል ሊባል አይችልም ይከልቁንም ከሁሉም ተግባራት የላቀው እንጂ፡፡ Abduh Nasser(2018) ሰዎች ጽህፈትን የግልቸውን ሃሳብ ዝውውር ለማካሄድ እና ለማሳካት ከሂወታቸው ጎንለጎን ወይም ትይዩ የሚያስኬዱት ጉዳይ ወይም ተግባር ነው፡፡ እንዲሁ እንኳን ብንመለከተው የትኛውንም አይነት ት/ት ለመማር መጻፍ መሰረታዊ ጉዳይነው፡፡ በአይናቸው ማየት የማይችሉ እንዲሁም በጆሯቸው መስማት የማይችሉ ወገኖች ሊማሩ የቻሉት በጽህፈት አማካይነት ነው፡፡ የነዚህ ሰዎች ችግሮችን ሊፈቱ የቻሉ መረጃዎች እና የችግር መፍቻ ሃሳች ለትውልድ የተላለፉት በጽሁፍ አማካይነት ነው፤ሰለዚህ ጽህፈት/ጹሁፍ ለሰውልጅ መሰረታዊ ጉዳይነው ቢባል የሚያከራክር አይሆንም፡፡ተማሪዎች እራሳቸውን እንዴት በጽሁፍ መግለጽ

ካልቻሉ ከሚያተምሯቸው መ/ራን እንዲሁም ከጓደኞቻቸው ጋር በጽሁፍ ለመግባባት ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡(walsh,2010). ስለጽሁፉ ጠቀሜታ በዚች አጭር ጽሁፍ ብቻ አውረቶ የሚበቃ አይሆንም እንደው ለማሳየት ያክል ተፍለን እንጂ፡፡

ከዲያ ጽሁፍ እጂግ አስፈላጊ ከሆነ እና ጠቀሜታው ምት የሌለው ከሆነ ልጆች እንዴት መማር አለባቸው፡፡ ፊደል የሚያወቅ ሁሉ ገዢ ጽሁፍን በመጻፍ እና አሳማኝ መልእክቶችን በማስተላለፍ በኩል ሁሉም ተማሪ ወይም መጻፍ የሚችል ሁሉ ማስተላለፍ ይችላል ብሎ ማሳብ አይቻልም፡፡ ጽህፈትን በመማር መሻሻል እና ማሳደግ ይቻላል፡፡ ዋናው ቁምነገር እንዴት በምን መንገድ መማር አለባቸው የሚለው ነው ዋናው ቁምነገር፤ ስለዚህ በዚህ የዳሰሳ ጽሁፍ ውስጥ ለጥናቱ የተመረጠውን ይዘት ወይም ርዕስ መጻፍን ለማተማር ያለወን ፋይዳ በመዳሰስ በሰፊው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 2.3. ትውርታዊ ማዕቀፍ (Theoretical Frame work)

ጽሁፍን ለመፃፍ ፀሃፊው የመንደፍ፣ የማርቀቅ እና የመከለስ ችልታ ኖሮት የድርሰቱን ፈጠራዊነት እና ተደጋጋሚ ባህሪያቱን በመገንዘብ የማርቀቅ እና የመከለስ የቋንቋ አጠቃቀምና ይዘቱን የመከለስ የማደራጀት እንቅስቃሴዎችን ተግባራት ማከናወን ይኖርበል፡፡ በተወሳሰበ ሂደት ድርሰት ሲፃፍ ሊገለፅ የተፈለገው ፍቺ መፈተሽና በጽሁፍ ሊተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ በተፈለገው ማህበራዊ ዓውድ እንዲተላለፍ ከአንባቢው ጋር ተግባቦትን የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡

መፃፍን በማስተማር ላይ ያለ አመለካከት የውጭ ቋንቋን በማስተማሩ ዘርፍ ትኩረት በሚሰጥና የሚደረግ ለውጥ ነፀብራቅ ነው፡፡ በትምህርቱ ላይ የሚደረገው ትኩረት በተማሪ፣ መምህራንና መርሃ ትምህርት መካከል በሚደርጉት ዝንባሌ የተለያየ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ዝንባሌዎች የተነሳ የተለያዩ ዝንባሌዎች ብቅ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም መፃፍን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሰዎችን የመማር ስሌት ግንዛቤያቸውን፣ ውጤታማነታቸውን፣ ማህበራዊ ዲራቸውንና ዕውቀትን መሰረት ያደርጋሉ፡፡

## 2.4. የጽሑፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

መፃፍ መልዕክትን የሚወክል ስዕላዊ ምልክቶች ብቻ የያዙ ሳይሆን አዲስ ግኝትን የመፈልግ እና ትርጉም የመስጠት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም መፃፍ የፊደልን ቅርጽ ለይቶ ከመፃፍ ጀምሮ አዲስ ሀሳብን ከማፍለቅ ቃላትን እና ሀረጋትን አቀናጅቶ ዐረፍተ ነገርና አንቀጽን በማዋቀር

ሀሳብን በተደራጀ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ለሌላው ማስተላለፍ የሚያስችል ሂደታዊ ተግባር ነው (Janet, 2003: 3245) የተለያዩ ምሁራን እንደገለፁት የመፃፍን ክሂል ለማስተማር የሚያገለግል የተለያዩ አቀራረቦች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት አግኝተው በስፋት እየተሰራባቸው ያሉት ውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር አቀራረቦች ናቸው ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ካለፉት ሀያ አመታት ወዲህ የዘውግ ተኮር አቀራርብ ስራ ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ Ramies (1983)፣ Brown (2000) እና Silva (1990)፡፡

### 2.4.1. የውጤት ተኮር አቀራረብ

መፃፍን በማስተማር ረገድ ውጤት ተኮር አቀራረብ ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም መምህር ተኮር ነው:: በዚህ ዘዴ ተማሪው ሞዴሎችን እዲቀዳ ይበረታታል (Brakan, 2003; Gabrielatos, 2002):: ይህ ዘዴ በመፃፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ እስከ 1970ዎቹ ድረስ ብቸኛው የማሰተማሪያ ስልት ሆኖ አገልግሏል:: የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ለሚፅፏቸው ፅሁፎች ምሳሌ ይሆናሉ፣ ጥሩ ተፅፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ፅሁፎችን አቅርቦ ሰዋስዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣ የአፃፃፍ ስልትን ወዘተ ተንትኖ ማሳየት እና ተማሪዎች የተመለከቱትን በፅሁፋቸው እንዲተገብሩ የማድረግ ስልትን የሚከተሉ ሲሆን ዋነኛው ትኩረቱ የቋንቋውን ሰዋስው ማስተማር ነው (Pica, 1986:6):: የውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው በተለያዩ አንቀፆች እና አውዶች መዋቅር እና አደረጃጀት ላይ ነው:: አላማው ትክክለኛ ፅሁፎችን ማፍለቅ ነው::

የውጤት ተኮር አቀራረብ ዋና ዋና ባህሪያቱን እና መርሆቹን Richards (2002:30-32) እንደሚከተለው ገልፀውታል::

1. የድርሰት አፃፃፍ መመሪያዎችን እና የሰዋስው ህጎችን በተለያዩ የድርሰት አይነቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማሳየት ተማሪዎች በተግባር እንዲለማመዋዷቸው ያደርጋል::
2. የመፃፍ ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋም ወይም በግል የሚተገብሯቸውን ፅሁፎች መፃፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው:: በተለያዩ የድርሰት አይነቶች ቅርፅ እና አደረጃጀት ላይ ያተኩራሉ::
3. ትክክለኛ የአረፍተነገር መዋቅር መሰረት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው:: በዚህ የተነሳ የሰዋስው ችሎታ ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል::

4. ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲፅፉ እና ስህተት እንዲይሰሩ ለማድረግ ይሞክራሉ::
5. የእጅ ፅሁፍ፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የቃላት አገባብ፣ የፊደል አጣጣል ወዘተ እውቀት በትምህርትነት ይቀርባሉ::

በአጠቃሊይ የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ድርሰቶችን በማረም እና ተማሪዎች ስህተት እንዲይሰሩ በመቆጣጠር ላይ ነው:: በዚህ የፅሁፍ ትምህርት አቀራረብ የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ አንቀፆችን መገንባት እና ድርሰቶችን መፃፍ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ የሚደረጉ ልምምዶች፣ የሚመረጡ ሞዴሎች እና የዐረፍተ ነገሮች አመሰራረት የሰዋስው ህግጋትን የተከተሉ ናቸው :: የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመፃፍ ትምህርት አንድን ድርሰት ለመፃፍ ከሚታለፍበት ሂደት ይልቅ መጨረሻ በሚገኘው ውጤት ላይ ትኩረት ያደርጋል::

በአጠቃሊይ ውጤት ተኮር አቀራረብ ከሂደት ይልቅ ውጤት ላይ ያተኩራል:: እንደ Richards (2001:107), Pincas (1982:14), Raims (1983:7) አገላለፅ በውጤታማ የመፃፍ ክሂል አቀራረብ በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ:: እነዚህ ተግባራት ውስን መፃፍ (Controlled Writing) ፣ መር መፃፍ (Guided Writing) እና ነፃ መፃፍ (Free Writing) ናቸው::

### 2.4.1.1. ውስን መፃፍ

ውስን የመፃፍ መልመጃ ትኩረት የሚያደርገው ስህተትን ያለመስራት ወይም በትክክለኛነት ላይ ሲሆን ብዙ ጊዜ መልመጃው ለጀማሪ የመፃፍ ትምህርት ተማሪዎች የሚቀርብ ነው:: ይህ የመፃፍ መልመጃ በአንፃራዊነት ነፃነት ለሚሰጠው መር መፃፍ እንደመሸጋገሪያ ሆኖ ያገለግላል:: በውስን መፃፍ መልመጃ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በመከተል ሲሆን ሰህተት እንዳይሰሩ ቁጥጥር የደረግባቸዋል:: የክንውኑ ዓላማም በአንፃራዊነት ከስህተት የፀዱ አረፍተነገር ወይም አጭር ጽሁፍ መፃፍ ነው::

ውስን የመፃፍ መልመጃ ተማሪዎች የፅሁፍ ቅርፅ እና ይዘት ቀርቦላቸው የሚያከናውኑት በመሆኑ የራሳቸውን ሀሳብ የማፍለቅ ዕድል የላቸውም:: ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ የመምህሩ

ጥገኛ ናቸው:: በመሆኑም ስህተት ለመስራትም ሆነ የራሳቸውን ቅርፅ እና ይዘት ለመከተል አጋጣሚው አይኖራቸውም (Raimes, 1983:95-96)::

መፃፍን በመለማመድ ሂደት ተማሪዎች እንዲያስቡ እንዲመራመሩ፣ ሃሳባቸውን በጽሁፍ እንዲያሰፍሩ እና እንዲገልጹ ማበረታታት በትምህርት መርህ አስፈላጊ ነው:: ይሁን እንጂ ውስን የመፃፍ መልመጃ የሚያካትታቸው ተግባራት ማሰብን እና ማፍለቅን የማይጠይቁ ናቸው:: Raimes (1983:117) እንዳቀረቡት በውስን የመፃፍ መልመጃ አማካይነት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው::

- ክፍት ቦታዎችን መሙላት፣
- ሞዴል አረፍተነገሮችን አስመስለው እንዲጽፉ ማለማመድ፣
- አያያዥ ቃላትን ተጠቅመው አረፍተነገሮችን መመስረት፣
- በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማያያዝ አረፍተ ነገርን መመስረት፣
- ቅደም ተከተላቸው የተዛባ አረፍተነገሮችን አስተካክሎ መልሶ መፃፌ እና
- በአንቀፅ ውስጥ የፆታ፣ የቦታ እና የጊዜ ለውጥ በማድረግ እንደገና መፃፍ ናቸው::

### 2.4.1.2. መር መፃፍ (Guided Writing)

እንደ Pincas (1982:102) አገላለፅ መር የመፃፍ ክሂል መልመጃዎች ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ ሲገልፁ ያጋጥሟቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ችግሮችን ለመቀነስ የሚፈጥሯቸውን ስህተቶች ለማሳነስ የሚያግዙ ተግባራት የሚቀርቡበት ደረጃ ነው:: መር የመፃፍ መልመጃዎች በውስን እና በነፃ የመፃፍ መልመጃዎች መካከል የሚገኝ ሲሆን በናሙናነት የቀረበን ጽሁፍ በአግባቡ በመገንዘብ ቅደም ተከተል ጠብቆ የሚከናወን ነው:: በመር የመፃፍ መሌመጃ ተማሪዎች በጅምር የቀረበን አረፍተነገር በራሳቸው ያሟላሉ:: በዚህም የተነሳ ስህተት የሚፈፅሙበት ሁኔታ ከፍ ያለ ይሆናል:: ከዚህ በሊይ ከቀረበው ሀሳብ የምንገነዘበው በመር የመፃፌ ክንውን የተሻለ የመፃፍ ነፃነት መኖሩን ነው፡፡ ሆኖም ግን ስህተት በመስራት በኩል ከውስን የመፃፍ መልመጃዎች አንፃር ሲታይ ከፍ ያለ ነው::

በመር የመፃፍ መልመጃዎች ወቅት የሚከናወኑ ተግባራትን Raimes (1983:103) እንደሚከተለው ይዘረዝሯቸዋል::

1. ዝርዝር መረጃዎችን በመስጠት ሀሳቡን እንዲያስፋፉትት ማድረግ፣

2. በሰንጠረዥ የቀረቡ ሀሳቦችን ወደ ጽሁፍ መቀየር፣
3. ያልተጠናቀቁ ታሪኮችን ማጠናቀቅ፣
4. ንድፎችን ተጠቅሞ አንቀፅ መመስረት፣
5. አረፍተ ነገሮችን በማወዳደር በጽሁፍ መግለፅ እና
6. አንድን ፅሁፍ አንብበው የተረዱትን በፅሁፍ መግለፅ ናቸው::

### 2.4.1.3. ነፃ መፃፍ/ Free writing/

እንደ Pincas (1982:110) አገላለፅ በነፃ የመፃፍ መልመጃ ለተማሪዎች ርዕስ ይቀርብላቸዋል ወይም እንዲመርጡ ይደረጋል:: በዚህም የተነሳ በራሳቸው ለመፃፍ ነፃ ናቸው:: በነፃ የመፃፍ መልመጃዎች ላይ የሚያደረገው ቁጥጥር አነስተኛ ነው:: በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በሚመርጡት ወይም በሚቀርብላቸው ርዕሰ ጉዳይ በነፃነት የሚፅፈበት ሲሆን በዚህ የመፃፍ ስራ የመምህሩ ሚና አነስተኛ መሆኑን አክለው ገልፀዋል::የነፃ መፃፍ መለኪያ ምን? እንዴት? ለምን? እና ለማን? ተፃፈ የሚሉት ጥያቄዎች ሳይሆኑ ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያልበዙበት ፅሁፍ ቀረበ የሚለውን ሁኔታ ይመለከታል::

### 2.4.1.4. በውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች

በውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተለያዩ ሙሁራን ትችት አቅርበውበታል:: በዚህ አቀራረብ ሊይ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ቀጥለን እንመልከት::

Raimes (1983:17) በሰጡት አስተያየት ውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች እንዴት እና ለምን እንደሚጽፉ ከማሳየት ይልቅ የጽሁፍ ቅርጾችን እና የሰዋስው ህጎችን ተከትለው እንዲጽፉ የሚያደርግ ከመሆኑ ባሻገር የማስተማር ስልቱ በትዕዛዛዊ መመሪያ ላይ የተመሰረተ ነው:: በዚህ አቀራረብ ተማሪው በራሱ ተገፋፍቶ ሀሳቡን በተገቢው መንገድ ለመግለፅ የሚያስችለውን እውቀት አያዳብርም:: ለዚህ ሰበቡ አቀራረቡ ተማሪውን የሚገድብ በትዕዛዝ የተሞላና ተማሪው በራሱ ሀሳብ አመንጭቶ እንዲፅፍ የሚያበረታታ አለመሆኑ ነው:: የመማር ማስተማር ሂደቱ ደረጃዊነት፣ መስመራዊነት እና ትዕዛዛዊነት ይበዛበታል:: ይህ አቀራረብ ለሂደታዊ ፅሁፍ ፣ ለተማሪዎች ዳራዊ እውቀት እና ክህሎት ዋጋ የማይሰጥ ከመሆኑም በላይ ዋና ትኩረቱ ጽሁፍ ተጠንቶ የሚቀርብበት ውጤት ላይ ነው:: ውጤቱም የሚለካው ከትክክለኛነት አንጻር ነው (Badger and White, 2000:157)::

እንደ Zamel (2011:165) አገላለፅ በትክክለኛነት ላይ ትኩረት የሚያደርገው የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ከሚያጋጥመው ችግር መፃፍን በማጠናቀር ሂደት የተማሪዎችን ተጨባጭ ፍላጎት መፈተሽ እና ያላቸው ልምድ ለማጠናቀሩ ሂደት አጋዥ ነው ወይ የሚለው ይጠቀሳሉ:: Richards (2001:105), Maray (1980)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት በውጤት ላይ ያተኮረ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመጨረሻ የጽሁፍ ውጤት እንጂ የተከተሉትን የአፃፃፍ ሂደት አያመለክትም ሲሉ በተጫማሪም በምሁራን የጥናት ውጤት መሰረት ይህ አቀራረብ ችግር እንዳለበት እና የችግሮቹም መንስኤ አቀራረቡ አንድን ፅሁፍ ለመፃፍ ምን አይነት አካሄድ እንከተል ከሚለው ይልቅ አንድ የመፃፍ ተግባር እንዴት ሆኖ ተጠናቋል በሚለው ላይ ትኩረት ከማድረጉ ባሻገር ለተፃፈ ነገር ትክክለኛነት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣል:: በዚህ አቀራረብ ተማሪው የሚያውቀው አረፍተነገርን ከአረፍተነገር እንዴት  ማያያዝ እንዳለበት እና ልዩ ልዩ የጽሁፍ ቅርፆችን እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል ነው:: ይህ አካሄድ ተማሪው በራሱ መንገድ ተጉዞ ሃሳብ አፍልቆ እና አደራጅቶ የራሱን ጽሁፍ እንዴት መፃፍ እንዳለበት አያለማምድም:: በአጠቃሊይ የውጤት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የመፃፍ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ስህተት እንዲይሰሩ የሚለውን ሀሳብ የሚያንፀባርቅ ነው:: የመፃፍ ችሎታ የሚያድገው በተደጋጋሚ ልምምድ እንጂ በቅፅበት ባለመሆኑ አቀራረቡ ችግር ይታይበታል:: በመሆኑም መምህራን ይህን አቀራረብ ለብቻው ከመጠቀም መታቀብ ወይም ጠንካራ ጎኑን አጢነው ደካማ ጎኑን ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል::

## 2.4.2. የሂደት ተኮር አቀራረብ

ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተጀመረው በእንግሊዝ እና በአሜሪካ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መፃፍን ለማስተማር ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በርካታ ሀገሮች በሁለተኛ እና በውጭ ቋንቋ መፃፍን በማስተማር እያገለገለ ይገኛል፡፡ አቀራረቡ ከቅርጹ ወይም ትክክለኛነት አንፃር ከማስተማር ይልቅ በአፃፃፍ ሂደት ማተኮር እንደሚገባ ያምናል (Raime, 1983)፡፡

ሂደት ተኮር አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ከመጀመሪያው፣ አንስቶ በመፃፍ ወቅት በሚከናወኑት ተግባራት ወይም ወደ ውጤት ለመድረስ በሚያስችለው ሂደት ላይ እንጂ በመጨረሻው ውጤት ላይ አይደለም፡፡ በሂደት ተኮር አቀራረብ የፀሀፊው ትኩረት ፅሑፍን እንዴት እንደሚጀምር መወሰን ሊይ ነው  (Ramines, 1993)::

ሂደት ተኮር አቀራረበ ተማሪዎች በራሳቸው አካሄድ በሂደት መፃፍን እንዲማሩ እና ከመምህራን ጋርም ተግባብቶ የመስራትን ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ አሳታፊ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ

የተማሪው እና የመምህሩ ተሳትፎ በግልጽ የሚታይበት ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች ለመፃፍ በሚፈልጉበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ አዲስ ሀሳብ በማምጣት እና በማደራጀት እንዲፅፉ እድል የሚፈጥር ነው (Ramines, 1993)::

### 2.4.2.1. በሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች

ሂደት ተኮር አቀራረብ ለሰዋሰውና መዋቅርና አነስተኛ ትኩረት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ በፅሁፍ ለሚገኝ የመጨረሻ ውጤት የሚሰጠው ግምት አነስተኛ ነው። መፃፍን በሂደት አቀራረብ የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች በየግላቸው የራሳቸውን ውስጣዊ ችልታ እንዲጠቀሙ ከማበረታታቸውም በላይ ትክክለኛነትን ችላ ይላሉ። ሂደት ተኮር የመፃፍ ትምህርተ አቀራረብ መፃፍን በመማር ማስተማር ሂደት የሚከተሏቸው የማስተማሪያ ስልቶች አሉታዊ ሚና አሏቸው። ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ብዙ ረቂቆች እንዲጽፉ የሚሰጠው ትኩረት በየጊዜው ለሚጽፉት ጽሁፍ በተገቢው ሁኔታ የሚያዘጋጀው አይደለም። (Horwite, 1986)::

### 2.4.2.2. ዘውጋዊ ዘዴ የመፃፍ ትምህርት ተኮር

ባለፉት አስርት ዓመታት ተፈጥሮአዊ አቀራረብ በተለያዩ ቋንቋን የማስተማሪያ ዐውዶች ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ አቀራረብ መሰረት የሚያደርገው ተማሪው በበቂ ሁኔታ ለቋንቋው ከተጋለጠ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እና በአጋጣሚ ቋንቋን ይማራሉ የሚል ነው።

መምህራን ተፈጥሮአዊ አቀራረብን ስራ ሊይ ሲያውሉ ግብአቱን ካቀረቡ በኂላ ብዙ ጊዜ ጣልቃ መግባት አይፈልጉም ለዚህ ምክንያቱ ጣልቃ መግባት በትምህርት ላይ ችግር ይፈጥራሉ የሚል ነው።

ተማሪዎች ዐውዳዊ እና ስነልሳናዊ ገጽታዎችን በሚገባ በማስተዋል ፅሁፍን ቅርፅ ለማስያዝ እና ለማዋቀር እንዲችሉ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጥሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በትምህርት እና በሌሎች መስኮች የዘውግ አቀራረብን በማስተዋወቅ ረገድ አውስትራሊያ የመጀመሪያዋ ተጠቃሽ ናት (Sklvia, 1990)

የዘውግ አቀራረብ የሚታይ ስነ-ትምህርታዊነት አቀራረብ ቋንቋን ለማስተማር ስራ ላይ ውሏል። የዘውግ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪው ስለ ቋንቋ ግልጽ የሆነ እውቀት እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን በመምህሩ እና በተማሪው እንዲሁም በተማሪው እና በተማሪው መካከል ለሚኖረው መስተጋብር ዋጋ ይሰጣል። አፅመ ሀሳብ (Coceptual Frame work)

ደረጀ ገብሬ (2011) በመፅሀፋቸው ሲገልፁ “ፅህፈት የትጉሃን ሥራ ነው።” በማለት ይገልፃሉ። መምህራን ተማሪዎችን በፅህፈት ስራ በአንድ መንገድ ብቻ ሣይሆን የተለያዩ ስነዘዴዎችን በመጠቀም ልናተጋቸው የገባል።ትጉሃን የማሰብ የመመርመር ፍላጎት ደጋግሞ የመሞከር ትዕግስት፤እንዲሁም ማየቻሉና የማይሰሩ የሚመስሉ ተግባራት ላይ እንዲተጉ ማድረግ የገባል።ተማሪዎችን በመረጡት እና በተደራጀ ምንገድ እንፅፉ እነዲለማመዱ ማድረግ ተገቢ ነው።

## 2.5. የፅሕፈት ሂደት  ደረጃዎች

### 2.5.1.ቅድመ ጽሕፈት

በዚህ ሂደት ስር ተማሪዎች የሃሳብ ውጣ ውረድ በሂሊናቸስ በማድረግ የፈጠሩትን የሃሳብ ክምችት ወደ ሙግት በመቀየር ያሸነፈውን ዋና ሀሳብ ወይም ገዢ ሃሳብ በመለየት ወደ ወረቀት ለመቀየር የምንወስንበት ሂደት ነው። ተማሪዎች በዚህ ሂደት ያላቸውን ቃላትን በማገጣጠም ገዢ ወይም ሳቢ ዓ.ነገሮችን የማምረት አቅማቸውን የሚፈትኑበት ወይም በማምረት ሂደት የሚለማመዱበት ደረጃ ሊሆን ይችላል። በዚህ የአዕምሮ ክንውን ሂደት ሃሳብን የማደራጀት መልሶ የመናድ ሁኔታዎች ሁሉ ይኖራሉ። መልሶ የመጻፍ እና የማሻሻል አካሄድን ሁሉ ይጨምራል።

### 2.5.2. ረቂቅ ማዘጋጀት


በዚህ ሂደት ውስጥ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ተማሪዎች ሃሳብ በማጉረፈረ እና ያጎረፉትን ሃሳብ በማሚገት እና በማውጣት እና በማውረድ እንዲሁም በማንሳት ሂደት ውስጥ የተገኘውን ፍሬ ሃሳብ በፊደላት ውክልነት በወረቀት ላይ በማስፈር ለሌሎች የምናስተላልፍበት ሂደት ነው። ልክ በአዕምሯችን ስናወጣ ስናወርድ የነበረውን ሂደት እንዳከናወንን ሁሉ በዚህ ሂደት ውስጥ በወረቀት ላይ ማስፈር መልሶ መሰረዥ እንደገና መሻሻል ወይም ማደራጀት ተግባረቶች ይከናወናሉ። በዚህ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች በነጻፍቃዳቸው እንዲያከናውኑ መተው እና በራሳቸው መንገድ እንዲሰሩ ከሰሩ በኋላ መመልከት እና ስለሚያሻሽሉት ጉዳይ ከመልካም ጎን በመነሳት የማሻሻያ ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ስራ ይሆናል።

### 2.5.3. አርትኦ /የማጥሪያ ንባብ

የተጻፈውን ጽሁፍ ሌሎች በማሳየት አስታያየት ወይም ማስተካከያ ሃሳብ የምንቀበልበት እና የማስተካከያ ስራ በመስራት መልሰን የምናዘጋጅበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ ነጻ በመሆን እና ግልጽ ሆኖ ሌሎችን መቅረብ እና ከአንድ በላይ ከሆኑ አካላት ልምድን እና እስተያየትን በመቀበል ጽሁፍን ለማሻሻል ዋነኛ እና አይነተኛ ተግባር የሚሰራበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ልጆች ነጻነትን እና ለምድን ከሌሎች መካፈል ወይም መቀበል የሚለማመዱበት እንጂ ከእናቱ ጡት አንደሚጠባ ጎጻን ሁሉም ተግባር የሚሰጥበት ወይም ተቀባይ የሚሆኑበት ሂደት አይደለም፡፡ ተማሪዎች ይለፋሉ ከሌሎች ሃሳብ አስተያየት ይቀበላሉ መልሰው ይለፋሉ፡፡ በልፋት ውስጥ የሚጣፍጥ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል እና ያለልፋት ውጤት ማምጣት እንደማይቻል የሚማሩበት ሂደት ጭምር ነው፡፡

### 2.5.4.ህትመት እና አቅርቦት ወይም ትውውቅ

ይህ ክፍል የመጨረሻው ክፍል ሲሆን የተለፋበትን ፍሬ ወይም ምርት ለሰው የምናቀርበበት እና በመረጥነው ርዕስ ዙሪያ ሃሳብ እና ስሜታችን ለሌሎች በማስተዋወቅ በማቅረብ የምናሳይበት ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎችን ስንመለከት ስለተሰጣቸው ተግባር ምንያህል እንደለፉ በመምህራቸው ተግምግሞ ውጤት የሚያገኙበት ክፍል ይሆናል፡፡





**ስዕላዊ ውቅር 2.1. የፅሕፈት ሂደት ደረጃዎች**

## 2.6. የመፃፍ ክሂል አካላዊ ውቅር

እንደሚታወቀው የፊደላት ቅንጅት ቃላትን፣የቃላት ቅንጅት ደግሞ ዓ.ነገር፣የዓ.ነገር የቋንቋ ስረትዓትን ተከትሎ የሚደረገው አሰነዳድ አንቀጽ የተባለውን የጽሑፍ አካል ይሰጠናል፡፡ በየትኛው ሂደት አንቀጽ በመልክት ማስተላላፉ በኩል የጣፈጠ እንዲሆን የተመረጠውን ርዕስ በማብራራት ወይም በመግለጽ በኩል ሃሳብ ገላጭ ቃላትን መምረጥ እጅግ ወሳኝ እና አስቸጋሪው ተግባር ነው፡፡ ይህንን እቸጋሪ ተግባር ለመወጣት የቃላት ቤት በእምሯችን ሊኖረን የግድ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ጥሩ ጸሃፊ ለመሆን ጥሩ አንባቢ መሆን ያስፈልጋል እንዲሁም የቃላት ባለስልጣን መሆን አስፈላጊነው፡፡ የቃላት ሃብት ከምንም በላይ ለጽሁፍም ሆነ ለንግግር በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ሁሉም ሰው የንግግር ሂደትን የሚጀምረው ከሃሳብ ነው፡፡

ሃሳባ ሲደራጅ ምንጩ አዕምሮ ሆኖ ቀጂው እጅ ይሆንእና ተቀባይ ወረቀት ይሆናል፡፡ የስው አመለካከቱ ሁሉ በአብዘኛው በሚጽፈው ጽሁፍ ሁሉ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ይዘት ወይም ዋና ሃሳብ ልክ እንደ ኤክትሪክ መንጭ ወይም መነሻ ስፍራ ሲሆን ገመዱን ማርዘም እና ማሳጠር እንደሚቻለው ሁሉ ሀሳብንም ማርዘም እና ማሳጠርም እንዲሁ ይቻላል፡፡ በመጨረሻ ከመነሻ የተወሰደውው መብራት በገመድውስጥ መኖሩ እና አለመኖሩ ማረጋገጫው አንፖል ይሆናል ያማለት ከጽሁፍ ጋር ስናገናኘው በአዕምሮ የታሰበው እና የተወጠነው እንዲሁም የታሰበው እና የገረፈው ሃሳብ መኖሩ የሚታየው በሚታይ ወረቀት ላይ ሲጻፍ ይሆናል፡፡




**ስዕላዊ ውቅር 2.2. የመፃፍ ክሂል አካላዊ ውቅር**

## 2.7. ዘውጋዊ የማስተማር ስልት እና የመጻፍ ክሂል

በመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች አዲስ ነገር በመፈለግ እና በማምረት በኩል ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይፈለጋል፤ምክንያቱም መማር ትርጉም ከመፈለግ ወይም ከመስጠት ጀምሮ በአምሯችን ያለውን ወይም የቀደመ እውቀት አዲስ ከምናገኘው እውቀት ጋር በማቀናጀት እንደገና በማደራጀት የነበረን እውቀት በማበልጸግ መማር ከዚህም ሲያልፍ አዲስ ነገር መፍጠር ዋነኛ የመማር ተግባር ነው፡፡ (Fiorella and Mayer 2015;). እንደሚሉት መማር ማለት መረጃን በአምሮውስጥ እንደገና በማደራጀት እና ከነበረው የቀደመ እውቀት ጋር በማጣመር ወይም በማስማማት ላይ በመመስረት ትርጉም በመስራት ወይም በመስጠት በኩል ንቁ ተሳትፎ የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ሃሳብ በመማር ሂደት ውስጥ አዲስ ነገር መፍጠር


ወይም ማፍለቅ እንደላ ያሳያል፤በመሆኑም ይህን ጉዳይ ጽህፈትን ከመማር ጋር ብናገኛኘው ተማሪዎች ጽህፈትን በሚማሩበት ሂደት አብዘኛውን ጊዜ በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም ጥረት እና ብርታት ላይ ማትኮር እንደሚጠቅማቸው ይጠቁማል።
አዳዲስ ሃሰቦችን ለማፍለቅ ወይም ለማምረት ሰሪ አዕምሮ ያስፈልጋል። አዕምሮ ሰሪ የሚሆነው ማሰብ እና ማስታወስ እንዲሁም የቃለት ባንክ መሆን የሚችል የአዕመሮ ክፍል ሲኖር ነው። ተማሪዎች በመማር ሂደት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይፈለጋል። በተለይ ጽህፈትን በማስተማር ወይም በመማር ሂደት ውስጥ የአዕምሮ በስለት እና የእጅ አካለዊ አንቅስቃሴ ወይም ልምምድ በእጅጉ ወሳኝ ነው። ተማሪዎች ጽህፈትን በሚማሩበት ወቅት መሞከር እና መሳሳትን መለማመድ ችሎታቸውን ለማሻሻል በእጅጉ ቁምነገረኛ ተግባር ነው። ለዚህ ደግሞ ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ወይም ስልት አይነተኛ መሳሪያ ሊሆን ይችላል።

ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ መሰረት የሚያደርገው የራስን ግንዛቦት በትክክል መገምገም እና ለመምረጥ ለማደራጀት እና ለማቀናጀት የሚያስችል የመማር ስልት መምረጥን ጨምሮ ነው።( Fiorella and Mayer፣2015)። መምረጥ፣ማደራጀት እና ማቀናጀት ዋነኛ የአዕምሮታዊ የመማር ንድፈ ሃሳብ ምድብ ቢሆንም ሃሳብን በአዲስ መልክ ለማመንጨት እና ወደ ሰሪ አይምሮ እና አካላዊ እንቅስቃሴ በመቀየር የጣፈጠ እና ተወዳጅ መልክት አስተላላፊ ጽሁፍ ለመጻፍ ይቻል ዘንድ ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ጠቃሚ ነው።

በመማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ከአዝጋሚነት ወደ ታታሪነት ከሃሳብ ሰሪነት ወደ ተሳታፊነት መሻጋገር ከነሱ የሚጠበቅ አይነተኛ ስራ ነው። ዘውጋዊ የማስተማር ተግባር ውስጥ ተማሪወች መጻፍን በሚለማመዱበት ጊዜ ቃላትን ማነሳት እና መጣል እንደገና መፈለግ እና መምረጥ ከዚያም መጠቀም የተሸለ ሃሳብ ማፍራት ይችሉ ዘንድ የራሳቸውን ጥረት በማድረግ እና የሌሎችን አስተያየት በመቀበል በእጅጉ ይጠቅማቸዋል እና መ/ራን ለተማሪዎች ነጻነት በመስጠት እና ገንቢ ግብረመልስ በመስጠት በኩል አይነተኛ ሚና ሊኖራቸው ይገባል።

መጻፍ ሌሎችን በመመልከት እና ሞዴል በማድረግ የሚከወን ተግባር ሳይሆን የራስን ጥረት የሚጠይቅ ተግባር ነው። ይህ ሲባል ግን የሌሎችን ጽሁፍ ማነበብ እና ልምድ እና አካሄድን እንደምሳሌ መወሰድ የለበትም ማለት አይደልም።በሚከተለው ገጽ ለማሳየት የተሞከረው የዘውጋው ማስተማር ዘዴ አውታርን ወይም ጽንሰ ሃሳብ ፍሰትን ነው። በማእቀፍ ውስጥ ከላይ

የተገለጸው ሃሳብ ወይም ዘዴ ከሌሎች ሃሳቦች ወይም ተግባራት ጋር ሊኖረው የሚችለውን ዝምድና ወይም ግንኙነት ለማሳየት በሚችል ሁኔታ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።




**ስዕላዊ ውቅር 2.3 ዘውጋዊ የማስተማር ስልት እና የመጻፍ ክሂል**

## 2.8. የዘውግ- ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ሞዴል

ፊዝ እና ጆዩ (1998) የዘውግ- ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ሞዴል በአምስት ደረጃዎች ማለትም ጽሑፍን መገንባት፣ የጽሁፍን ሞዴል መተንተን፣ ጽሑፍን በጋራ መገንባት እና በጽሑፍ ላይ ጽብረቃ መስጠትን ያካተተ ነው:: ይህ ሞዴል ተማሪዎች የዘውግን ውስብስብ እይታ እንዲያሳድጉና በጽሑፍ ወቅት እንዲጠቀሙበት የማድረግ አላማ አለው:: በሌላ በኩል ይህ ሞዴል እንደሁኔታው ተለዋዋጭ በሆነ ሁኔታ ስራ ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን መምህሩ በማንኛውም አስፈላጊ ጊዜ እገዛ ሊያደርግ ይችላል:: በእያንዳንዱ ደረጃ የተማሪዎች ትኩረት የተለያየ ቢሆንም ነገር ግን አንዱ ከአንዱ ይኸውም የጽሐፍ ማህበራዊ አውድ፣ ይዘት፣ የጽሁፍ አደረጃጀት፣ የጽሁፍ ስነልሳናዊ ገፅታ፣ ዘውግን ከሂደት ጋር በማጣመር የተያያዙና ግንኙነት ያላቸው ናቸው:: ቀጥለን አንድ በአንድ እንመልከታቸው::

### 2.8.1. ዐውድን መገንባት

ለተማሪዎች ዐውድን መገንባት በጣም አስፈላጊው ደረጃ ሲሆን መምህራን ለትምህርቱ ጠንካራ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ:: በዚህ ደረጃ ጠቃሚው መርህ ተማሪዎች ጽሑፍ ከማህበራዊ አውድ እንደሚገኝ እና በድርጊቱ ውስጥ ማህበራዊ ግንኙነትን እንደሚያካትት እነረዲገነዘቡት ማድረግ ነው:: በመሆኑም ተማሪዎች የዘውግን አላማ ለመረዳት በተፈጠረው ግንኙነት ዐውድን መረዳታቸው አስፈላጊ ነገር ነው (Cllaghan 1993:181) በዚህ ደረጃ በቋንቋ አገልግሎት እና በዐውድ ውስጥ ፍቺ እንዴት እንደሚፈጠር ትኩረት ይደረጋል (Feez, 2002, Hyland, 2004):: በዚህ ደረጃ በክፍል ውስጥ ከሚከናወኑት ተግባራት መካከል በአውድ ላይ ውይይት እንዲደረግ የሚያበረታቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ማቅረብ፣ ስለፅሁፍ በስዕል መግለፅ፣ እንግዳ ተናጋሪዎችን መጋበዝ እና የመሳሰሉት ተግባራት ሊከናወኑ ይችላሉ Hyland (2004:130-131)::

### 2.8.2. ሞዴል ጽሑፍን መገንባት

በዚህ የሞዳሌ ጽሐፊ ትንተና ደረጃ መምህሩ ያለውን ግንኙነት በጠንካራ ሁኔታ ይመራል:: በዚህ የሞዴል ጽሑፍ ታላሚው ዘውግ በአውድ ላይ ትኩረት ያደርጋል:: (Feez, 2002:66):: መምህሩ እና ተማሪው ስለጽሁፍ አደረጃጀት፣ ሰዋስዋዊ ገጽታው በተለየ አውድ ውስጥ የጽሑፍን አገልግሎት በተመለከተ እና የቃላት ምርጫ ላይ መነጋገር አለባቸው::

Hyland (2004) ባቀረቡት ሀሳብ ትንተናው ከታች ወደ ላይ ከሚሆን ይልቅ ጽሁፍ ሙሉ በሙሉ ቢሆን ይሻላል ብለዋል:: ከተለየ አንባቢና መልእክት ጋር አላማን ለማሳየት ጽሁፍ እንዴት እንደተደራጀ ግምት ውስጥ መግባት አለበት:: በመሆኑም ሁለም የጽሁፍ አካል የተግባቦትን አላማ ለማሳካት እንዴት መፃፍ እንዳለበት ለምሳሌ አንቀፅ እና አረፍተ ነገር እንዴት እንደሚደራጅ፣ እንደሚዋቀሩና በስርዓት እንደሚፃፍ መገንዘብ ያስፈልጋል:: በሌላ በኩል መምህራን ለተማሪዎች በአረፍተ ነገር ውስጥ ሰዋስውን በግለፅ እንዲጠቀሙ ማሳየት ያለባቸው ሲሆን ይህም ለተማሪዎቹ ጠቃሚ ነው (Hyland, 2004)::

በሞዴል ጽሐፍ ትንተና ወቅት በመዋቅር ላይ መነጋገር፣ በሰዋስው፣ ከማህበራዊ አላማ ጋር በተገናኘ ልምምድ ማድረግ ጠቃሚ የክፍል ውስጥ ተግባራት ናቸው (Pallridse, 2001)::

## 2.8.3. ጽሑፍን በጋራ መገንባት (Collaborative Construction of the text)

በዚህ ደረጃ መምህሩ ሚናውን በመቀነስ ሁኔታዎችን ወደማመቻቸት ይሄዳሉ (Hyland 2004፣134):: ተማሪዎች በማርቀቅና በማዘጋጀት ደረጃዎች ላይ እያለ በግለፅ መነጋገር እና በፍቺ ላይ መስማማት እንዲኖር መደገፍ ያስፈልጋል:: በጽሑፋቸው ላይ ቁጥጥር ለማድረግና አጠቃላይ የሆነ የዘውግ ምሳሌ እንዲሰጡ በአነስተኛ ቡድኖች እንዲደራጁ ይደረጋል:: ይሁን እንጂ ተማሪዎች በጽሁፍ አደረጃጀት ላይ ችግር ላለባቸው ወደቀደመው ደረጃ ስለአውድና ስለ ጽሁፍ አወቃቀር ዳግመኛ ሊመለከቱት ይችላሉ:: Callaghan (1993)::

የዚህ ደረጃ ጠቃሚ ገፅታው መምህር የጽሑፍ ሂደት የሆኑትን ሀሳብ እና ተማሪዎች ጽሑፍ በሚያጠናቅሩበት ጊዜ የዐውድ የዘውግ እና በጽሑፍ ሂደት እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ መሆኑ ነው:: ተማሪዎች ካለፉት ደረጃዎች ያገኙትን የዘውግ እውቀታቸውን እንዲጠቀሙ ተከታታይ ልምምድ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የመፃፍ ሂደት እንዴት እንደሆነና የጽሁፍ ክሂላቸው እንዲዳብር በጽሑፋቸው ይዘት መፃፍ፣ መንደፍ እና መከለሰን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል:: Hyland (2004):: በክፍል ውስጥ ጽሑፍን በጋራ የመገንባት ተግባር በሚከተሉት ቅደም ተከተል ሊከናወኑ ይችላሉ::

1.በአገባቡ ላይ መነጋገር

ተማሪዎች በሚፃፈው ጽሁፍ አገባብ ላይ ንግግር ማድረግ ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ጽሁፍ የሚገነባበት ሁኔታ አላማው የፀሀፊው እና የአንባቢውን ሚና መለየት ይኖርበታል:: ይህ አይነቱ ጽሁፋዊ ገፅታ ለማህበራዊ ሁኔታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ መለየት አለበት::

2. ይዘትን ማሳደግ

ተማሪዎችን የሚያነቃቃቁ ስሌቶችን ተጠቅሞ የሚቀርቡ ጽሁፎች ይዘትን ያጎለብታል:: በዚህ መሰረት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማስቀረት ተገቢነት ያላቸውን ይዘቶች ለማሳደግ ስለአውዱ ያላቸው እውቀትና በአውዱ ላይ ለመነጋገር እንደ ማፅቀፍ መጠቀም አለባቸው::

3. ጽሐፍን ማደራጀት

በዚህ ተግባር ተማሪዎች ያገኙትን ሀሳብ ያደራጃል:: ከዚህ አንፃር መዋቅርን መሰረት አድርገው ጽሁፍ ስለሚፈጠርበት የቋንቋ ገፅታ ይነጋገራሉ::

4.ራስን በመገምገም

ንድፍን መከለስ ተማሪዎች የንድፍን ይዘትና አደረጃጀት በዐውድ ውስጥ ዓላማውን ማሳካቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ግምገማ ያካሂዳሉ::

5.ንድፍ ማዘጋጀት

በቅድመ መፃፍ ተግባራት ወቅት የተፃፈውን ንድፍ መሰረት በማድረግ የፅሁፍን ንድፍ ያዘጋጃሉ::

6.ራስን መገምገምና ንድፍን መከለስ

ተማሪዎች የዘውግ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ራሳቸውን መገምገምና ፅሁፍን የመከለስ ተግባር ያከናውናሉ::

7. የብጤ ግምገማ

ተማሪዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ በተማሩት የዘውግ ዕውቀት አማካይነት የፅሁፍን ውጤታማነት ይገመግማሉ:: በዚህ መሰረት መምህራን ተማሪዎች ንድፍን ለመገምገም የሚያስችል መመሪያ ያዘጋጃሉ:: ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው ጋር ንድፋቸውን በመለዋወጥ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት የቢጤዎቻቸውን ንድፍ አርመው ምጋቤ ምሊሽ ይሰጣሉ:: ከዚህ በኋሊ ሁለቱም በጋራ በንድፍፎቻቸው ላይ ይነጋገራሉ:: መምህሩም በውይይቱ በመሳተፍ ተጨማሪ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ::

8.ከቢጤ በተሰጠ አስተያየት ንድፍን መከለስ


በንድፉ ላይ ከቢጤ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ተማሪዎች ከውይይትና ከምጋቤ ምላሽ በመነሳት ንድፋቸውን ይከልሳሉ::

### 2.8.4. ፅሁፍን በራስ መገንባት

ተማሪዎች የዘውግ ዕውቀታቸውን እና የፅሁፍ ክሂላቸውን ተጠቅመው ዐውድን በመመርመር የራሳቸውን ፅሁፍ በግላቸው ይፅፋሉ:: ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ቢጤዎቻቸውን እና መምህራንን ሀሳብ መጠየቅ ይችላሉ:: እንዲሁም ባለፈው ፅሁፍን በጋራ የመገንባት ደረጃ የአገባብ ዕውቀት፣ የዘውግ እና ሂደት ጥምረትን የመጠቀሙ ልምድ የራሳቸውን ፅሁፍ በነፃነት እንዲፅፉ ያግዛቸዋሉ:: በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በየግላቸው የመፃፍን ተግባር የሚያከናውኑ ከመሆኑም በላይ የዘውግን ዕውቀት ማቀናጀታቸውን ለማረጋገጥ መምህሩ የተለያዩ ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ያበረታታቸዋል::

### 2.8.5. በጽሁፍ ላይ ፅብረቃ (Reflecting on writing)

ተማሪዎች ንድፍ ፅፈው ከጨረሱ በኋላ በፃፉት ፅሁፍ ላይ ፅብረቃ እንዲያደረጉ ይጠበቃል:: ይህ ሁኔታ የፅሁፍን አገባብ፣ ማህበራዊ ዐውድ ላይ የሚያሳርፈውን ተፅዕኖ እንዲገነዘቡ ያግዛል:: ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በአገባብ ላይ ያለን ተመሳሳይነትና ሌሎች ያጠኗቸውን ፅሁፎች እንዲያጤኑት ይበረታታሉ:: በፅብረቃ አማካይነት በተግባር ላይ ባለው ፅሁፍ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ ሁኔታዎች እና ተግባራትን ለማጠናቀቅ ስለሚከተሉት ስልት በፅብረቃ እንዲገለፁ ይበረታታሉ Johans (1997፣134) :: በአጠቃላይ በፅሁፍ መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንዲያጤኑት ይህም በፅሁፍ ውስጥ የታለመውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል ዕድል የፈጥርላቸዋል::




**ስዕላዊ ውቅር 2.4 የዘውግ- ሂደት ተኮር የመፃፍ ማስተማሪያ ሞዴል**

## 2.9. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በአማርኛ ቋንቋ በመፃፍ ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህ ስር ለማመልከት የተፈለገው ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት የተካሄደ ጥናቶች ከርዕሳቸው፣ ከአላማቸውና ከአጠናን ዘዴያቸው አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር በተዘዋዋሪ ወይም በቀጥታ መንገድ ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ማመልከት ነው፡፡

ክፍለ ሀብተማሪያም (1986) ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ፅሁፍ ባቀረቡት ጥናት የሁለተኛ ደረጃ በተለይም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ጉዳይን ቃኝተዋል፡፡ በጥናታቸው የተገኘው ውጤት ጥናቱ ያሳተፌቸው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት በትክክል የመግለፅ፣ ቃላት የመምረጥ፣ ሰዋስዋዊ አገባብን የመጠበቅ፣ በስርዓተ ነጥቦች በተገቢ ሁኔታ የመጠቀም፣ ዓረፍተ ነገርን በተገቢ ሁኔታ አዋቅሮ የመፃፍ እና ሀሳብን አቀነባብሮ የመግለፅ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለከቱ ሲሆን በጥናቱ ለተደረሰበት ውጤት ምክንያት ከሆኑ ነገሮች መካከል

የመማሪያ መፃህፍት አቀራረብ እና የትምህርቱ አሰጣጥ ዘዴ ዋነኛ ነጥቦች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ማረው ዓለሙ (1987) "በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ማጠቃለያ ላይ የደረሱበት ድምዳሜ በግል ከሚፃፉ ድርሰቶች ይልቅ በቡድን የሚፃፉ ድርሰቶች የተሻለ መሆናቸው፣ በጥሩ ድርሰት እና በቡድን ስራ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን እና የቡድን ስራ ለዴርሰት ፅሁፍ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል፡፡

ስዩም ከበደ (1988) "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለ9ኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት" በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት ሂደታዊ የመፃፍ አቀራረብን ተጠቅሞ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መፃፍን የማስተማር ክሂልን ለማሳደግ ውጤታማ ሆኖ መገኘቱን ጠቁመዋል ዘዴው ጠንካራ ጎን እንዳለው ቢታመንም ትምህርት የሚቀርብበት ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆነ ተማሪዎችን፣ ለመረዳት፣ ለመፃፍ፣ ፈተና ለማዘጋጀት እና ለአካዲሚያዊ የመፃፍ ክንውኖች ተማሪዎቹን ብቁ በማድረግ ረገድ ድክመት እንዳለው ጥናቶች ስለሚያመለክቱ እና ተማሪዎች በመፃፍ ሂደቱ ደጋግመው በመፃፍ መፃፍን ይማራሉ በሚለው ትወራ ውጤት ለማየት ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ በአማርኛ ድርሰት ማስተማር በኩሌ ያለውን ችግር ያቃልላል ማለት አያስደፍርም፡፡

ሰለሞን ዮሀንስ (1991) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ድግሪ መሙያ "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂ የመምህራን የማስተማር ዘዴ መጣጣም" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የደረሱበት ውጤትም በመምህራን የማስተማር ዘዴ እና በተማሪዎች የመጻፍ ስትራቴጂ መካከል ክፍተት የመኖሩ ሚስጥር መምህሩ የሚከተለው የማስተማር ዘዴ፣ ተማሪዎች በተፈጥሮ ያላቸውን የመፃፍ ስትራቴጂ የሚያሳድግላቸው አለመሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አስቴር ሳሙኤል (1998) "የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመፃፍ ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአራት የአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቤቶች ጥናት ያካሄደች ሲሆን የጥናቷ ውጤት የሚያመለክተው መምህራን መፃፍን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ በማፃፍ ሳይሆን በአብዛኛው ስነልሳናዊ ዕውቀቶችን ለማስጨበጥ ትኩረት በመስጠት ላይ መሆኑን ጠቁማለች፡፡

ተመስገን ፈቀደ (2001) "የ11ኛ ክፍል መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት ተዛምዶ" በሚል ርዕስ ግምገማ አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በሀድያ ዞን በሾኔ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል መምህራን የመፃፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሃት መካከል ያለውን ግንኙነት በመፈተሽ የመምህራን የመፃፍ ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎችን የድርሰት የመፃፍ ብልሀት መመርመር ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት በመምህራን የማስተማሪያ ዘዳ እና በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀት መካከል ተዛምዶ አለመኖሩን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናታዊ ስራዎች የመፃፍ ክሂል ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች፣ የማስተማር ስነዘዴ ትግበራ፣ የመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ እና ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ባለው ተግባራዊነት ላይ በመመስረት የቀረቡ ናቸው፡፡ ከዚህ ጥናታዊ ስራ ጋር ያላቸው አጠቃላይ ዝምድና ማዕከላዊ ነጥባቸው ከመፃፍ ክሂል ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በክለሳ ድርሳናት ውስጥ የሚቀርቡበት አንዳንዱ ንድፈ ሀሳባዊ ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ሊኖረቸው ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የዚህ ጥናት በዋናነት ከነዚህ ጥናቶች የሚለየው ከትኩረት አቅጣጫው፣ ከአጠናን ስልቱ አንፃር ሰፊ ልዩነት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ፣ የተተኳሪ መጠን ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የጥናቱ ዘመን እና ዓላማ ከቀደምት ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል፡፡ ይህ ጥናት በአጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የዘውግ ተኮር የድርሰት አፃፃፍ የመማር ሂደት ሊይ ያተኮረና የመምህራንን የዘውግ ተኮር የፅሁፍ ክሂል የማስተማር ሂደት ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የአጠናን ዘዴ

አጥኚዋ ለዚህ ጥናትና ምርምር አምስት የአጠናን ክፍለ ስልቶች ለመከተል ጥናቱን አከናውናለች። እነዚህም የጥናት ስነ-ዘዴ ክፍሎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል። እነሱም የምርምር ንድፍ(፣ የጥናት ዓይነት፣ የመረጀ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጥናት ናሙና አመራረጥ ዘዴና የመረጃ አተናተን ስልት ናቸው። አጥኚዋ እያንዳንዱን፣ ሂደት /ዘዴ/ በቅደም ተከተል እንደየአስፈላጊነቱ የተጠቀመች ሲሆን፤ በተጨማሪም የጥናቱን ሂደት በተሳካ ሁኔታ ለማሳለጥ ይረዳ ዘንድ በእያንዳንዱ አብይ የጥናት ዘዴ ስር ንዐሳን የጥናት ስልቶችንም ለመጠቀም ችላለች።

### 3.1. የምርምር ንድፍ

በጥናትና ምርምር ዓለም ትክክለኛውን የምርምር ስልት መምረጥ ለምርምሩ አካሄድ ወሳኝ ነው። የምርምሩን አቅጣጫ ለማወቅም ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል። እንደ ተመራማሪ የምርምሩን ስልት ቀድሞ ከወሰነ የጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለመተርጎምና የምርምሩን መሳሪያዎች ለመወሰን ቀላል ይሆንለታል (Norman and Yavona 1994):: ከተገቢ የመረጃ ምንጭ ለመሰብሰብ ለመተርጎምና የምርምር መሳሪያዎችን በቅድሚያ ወስናለች።

በዚህም መሰረት በዓለም ላይ ምሁራን ከነደፏቸው የምርምር አካሄዶች በዋናነት ፓዘቲቪዝም እና አንቲፖዘቲቪዝም ይገኙበታል። ፓዘቲቪዝም ምልከታና ምክንያት መሰረታዊ ነገሮች መሆናቸውን የሚቀበለ አቀንቃኞች የሚከተለት የምርምር አካሄድ ሲሆን የዚህ እሳቤ ተከታዬች እምነትና አመለካከት እውነተኛ እውቀት የሚመነጨው በሙከራና በምልከታ ከስሜታችን በሚገኝ ልምድ እንደሆነ ይታመናል። ስለሆነም የፖዘቲቪዝም የምርምር አካሄዱ በሀያኛው ክፍለ ዘመን ትምህርት ላይ በሚካሄደ ምርምሮች አዎንታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል። የፖዘቲቪስቶች አመለካከት ከሰዎች ባህሪ አንፃር ማህበራዊ ሁኔታዎች በተጨባጭ የሚለኩ፣ የሚታዩና የሚተገብሩ እንደሆም ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችለ መሆን አለባቸው የሚል እምነት አላቸው። በዚህም የተነሳ ምርምር ለማካሄድ የሙከራ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። የሙከራ ንድፍ ተመራማሪው መላምቶችን ለመመርመርና በተለዋዋጮች መካከል ያለውን

ግንኙነት በመፈተሽ ተቀባይነት ያለው መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ ያስችለዋል (Best and Khan, 1993)፡፡

አጥኚዋ በዚህኛው የጥናትና ምርምር ስራዋ የኩዋዚ ሙከራዊ የምርምር ንድፍን በመከተል በጥናቷ ላይ ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ የኩዋዚ ሙከራዊ የምርምር ንድፍ በሚተገበርበት ጊዜ ክትትል መቼ እና በነማን ላይ መካሄድ እንዳለበት ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡በኩዋዚ ሙከራዊ የምርምር ንድፍ አሰራር ውስጥ ተጠኚዎች በዘፈቀደ የሚመረጡ ሳይሆን ከልብ በሆነ መንገድ የሚመረጡ ናቸው፡፡(Creswell ,2012. P.310). ይህ የጥናት ንድፍ የምክንያት እና ውጤትን ለማጥናት ስለሚጠቅም እና አስፈላጊ በመሆኑ በቀጥታ ለአጥኚዋ አመቺ ንደፍ እንደሆነ ታይቷል፤ ስለዚህ ይንን የሙከራ የጥናት ንድፍ መርጣዋለች፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት አጥኚም ጥናቷን በሙከራዊ ንድፍ ለመተግበር ከአጋሮ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ሁለት ክፍሎችን ማለትም 9ኛ 'A' እና 9ኛ 'D' ክፍሎችን በናሙና በመምረጥ ሁለት የጥናት ቡድኖችን መስርታለች፡፡ እነዚህ ክፍሎችም የተመረጡበት ምክንያት አንድም በትምህርት ቤት አዘወትሮ በመገኘት የተሻሉ ያሉበት ክፍሎች በመሆናቸውና ከቋንቋ ስብጥር አንፃር ተመጣጣኝ በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚዋ ለጥናቷ ተግባራዊነት ያመቻት ዘንድ የጥናት ቡዴኖቿን በሂደት ወዘውግ እና ልማዳዊ የማስተማር ዘዴ በድርሰት አፃፃፍ ላይ እንዲሳተፉ አድርጋለች፡፡ በዚህም መሰረት የ9ኛ 'A' ክፍል ተማሪዎች የሙከራ ቡድን እንዲሆኑ ስታደርግ የ9ኛ 'D' ክፍል ተማሪዎችን ደግሞ የቁጥጥር ቡድን በማድረግ የኬይዝ ሙከራዊ የምርምር ንድፍን በመጠቀም ጥናቷን ለማከናወን ችላለች፡፡

## 3.2. የጥናቱ ዓይነት

እንደሚታወቀው ኩዋዚ የሙከራዊ የጥናት ንድፍ የመጠናዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ ከሚመደቡ የንድፍ አይነቶች አንዱ በመሆኑ ይህ ጥናት በዋነኝነት መጠናዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ በተጨማሪም አይነታዊ የጥናት ዘዴን በአጋዥነት በመጠቀም እና በመከተል ገላጭ የመረጃ አተናተን ስልት የተከተለ ጥናት እንዲሆን አጥኚዋ አልማ ለመስራት ችላለች፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ ከቅይጥ የምርምር ዘዴዎች ውስጥ ገላጭ የቅይጥ የጥናት ንድፍን በአጋዥነት አጥኒዋ ተጠቅማለች፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በሙከራዊ ንድፍ የተገኘውን መጠናዊ መረጃዎች የበለጠ ለማብራራት እና የተገኘውን ውሳኔ ለማስጌጥ እና ለማሳመር ወይም ተቀባይነቱን/ታማኝነቱን ለመጨመር ገላጭ (Explanatory mixed research design) በመካተት አጥኚዋ ጠናቷን ሰርታለች፡፡ገላጭ (Explanatory mixed research design)

መጠናዊን የጥናት ንድፍ በዋነኝነት በመጠቀም እና በመጀመሪያ ደረጃ መረጃን በመሰብሰብ እና በመተንተን ከዚያም ውጤቱን በመለየት በማስከተል አይነታዊ መረጃን በመሰብሰብ እና በመተንተን በመጠናዊ የጥናት ንድፍ የተገኘውን ውጤት በማስጌት የተገኘውን ውጤት የምናሳምንበት የቅይጥ የምርምር ዘዴ ንድፍ ውስጥ አንዱነው በመለት (Creswell,2012, Gay and e.tal, 2012) ገልጸውታል። የዚህ ጥናት አላማ ተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ የዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ክሂሎች የማስተማር ዘዴ አማካኝነት በተጠኚዎች ላይ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን ለመለየት የሚያስችል የጥናት አይነት እንዲሆን አጥኚዋ አልማ አከናውናለች።

### 3.2.1. የናሙና አመራረጥ

እንደ Frankel and Wallen (2001:91) በምርምር ሂደት ውስጥ ናሙና መረጃ የሚያስገኙ ቡድኖች ናቸው በማለት ገልፀዋል። Best and Kahan (1993:13) ናሙና ከአጠቃላይ ቁጥር በአነስተኛ ወካይ በሆነ ቁጥር የሚመርጥ ነው ብለዋል። ናሙና ለመምረጥ ደረጃ በጥናቱ የተገኘው ውጤት ሊያጠቃልላቸው የሚችሉ ክፍሎችን መግለጽ እንደሚያስፈልግ (በመለት (Creswell,2012, Gay and e.tal, 2012) ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት ናሙና የተወሰደባችውን አካላት እና ለነሙና መውሰጃ እና የጥናት አካል ሊሆኑ የተፈለገበትን መክንያት ሁሉ አንደሚከተለው ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

### የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ተመራማሪም አሳማኝ የሆነ የናሙና አወሳሰድ ስሌትን በመከተል ለጥናቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ፈቃደኛ የጥናት ናሙናዎችን ተጠቅማለች። በዚህም መሰረት በአጋሮ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአጋሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ለሙከራ ጥናቱ መርጣለች። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንኒያት መምህርቷ በዚሁ ትምህርት ቤት ውስጥ በማስተማር ላይ የምትገኝ በመሆኗ ነው፤ እንዲሁም በቀላሉ የሙከራ ጥናቱን ለማካሄድ እና በመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው። እንደ Creswell,(2012), Gay and e.tal, (2012) አገላለጽ በአስፈላጊነት የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በአጥኒው ልምድ እና በሚጠኑት ቡድኖች እውቀት ላይ መሰረት ተደርጎ የሚወሰን ነው ይላል፤በመሆኑም የዚህ ጥናት አከናዋኝ ወይም አጥኒዋ ከላይ በስም የተጠቀሰውን ት/ቤት ካላት ልምድ አንጻር ሆብላ ልትመርጥ ችለዋል።

## የክፍል ደረጃ አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪነት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠው ሆን ተብሎ ነው፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት አጥኚ በዚሁ የክፍል ደረጃ ለረጅም ጊዜያት ሰታስተምር የቆየች በመሆኗ ምክንያት ነው፡፡ እንደ Creswell,(2012), Gay and e.tal, (2012) አገላለጽ በአስፈላጊነት የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በአጥኚው ልምድ እና በሚጠኑት ቡድኖች እውቀት ላይ መሰረት ተደርጎ የሚወሰን ነው ይላል፤በመሆኑም የዚህ ጥናት አከናዋኝ ወይም አጥኚዋ ከላይ በስም የተጠቀሰውን ት/ቤት ካላት ልምድ አንጻር ሆብላ ልትመርጥ ችለዋል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው የናሙና መውሰጃ ዘዴ በመጀመሪያው ኩታ ገጠም ወይም ደግሞ ተጓዳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ የሁሉንም ተማሪዎች ሰምዝርዝር ለመጠቀም እና ናሙና ለመውሰድ አዳጋች ሲሆን እና በቡድን ወይም ደግሞ በክፍል ደረጃ ያሉ ቡድኖች ውስጥ የተወሰኑትን ቡድኖች ብቻ ለመጠቀም የሚያስችል መሆኑን (Gay and e.tal, 2012) ገለጸዋል ፤በመሆኑም ተጓዳኝ ዘዴን በተጫሪነት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የተማሪዎችን የናሙና አመራረጥ በተመለከተ በአጋሮ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙ 10 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በዕጣ ናሙና አወሳሰድ 9ኛA ክፍል በሙከራ ቡድን 9ኛD ክፍል ደግሞ ለቁጥጥር ቡድኑ እንደሆኑ አጥኚዋ መርጣለች፡፡ በተጓዳኝ ከተቀመጡ ወይም ከተመረጡ ክፍሎች ውስጥ ለጥናቱ የተመረጡ ክፍሎች ከላይ ለማስቀመጥ ተሞክረዋል እነዚህ ክፍሎች የተወሰዱቱ ሆን ተብሎ አንድም በትምህርት ቤት አዘወትሮ በመገኘት የተሻሉ ያሉበት ክፍሎች በመሆናቸውና ከቋንቋ ስብጥር አንፃር ተመጣጣኝ በመሆናቸው ነው፡፡

## የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ ከተመረጠው የአጋሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን በናሙና ዕጣ አወሳሰድ አንድ መምህር በመምረጥ የሙከራውን እና የቁጥጥሩን ቡድኖች አጥኚዋ በሰጠችው ስልጠና መሰረት እንዲያስተምሩ አድርጋለች፡፡

ጥናቱን ለማካሄዴ የተመረጠው መምህር የሙከራ ቡድኑን በአዱሱ መንገድ እንዲያስተምር አድርጋለች፡፡ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በነበረው መንገድ እንዱያስተምር አድርጋለች፡፡ በናሙና ዕጣ የተመረጠው መምህር በአዲሱ መንገድ ለማስተማር እንዲረዳው በአጥኚዋ በተዘጋጀው የስልጠና መመሪያ ስልጠና እንዲወስድ አድርጋለች፡፡

### 3.2.2. የስልጠና መመሪያ

የዚህ የስልጠና ማንዋል አላማ መምህሩ የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎችን በዘውግ እና ሂደት ተኮር ጥምር የድርሰት አፃፃፍ ትምህርት አቀራረብ መፃፍ ሲያስተምር ስለዚህ አቀራረብ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማስቻል ነው፡፡ ስለሆነም መምህሩ በአጥኚዋ የተሰጠውን ስልጠና በተገቢ ሁኔታ በመከታተል በመፃፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ የዘውግ ሂደት ተኮር ጥምር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን ተግብሯል፡፡

### 3.2.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለጥናቱ የሚያገለግል መረጃዎች በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተሰብስበዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተገቢ መረጃዎች በቅደመ ፈተናና ድህረ ፈተና ለተማሪዎች ከቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም በምልከታ ልዩ ልዩ መረጃዎችን አጥኚዋ ሰብስባለች፡፡

### 3.2.4. የመረጃ አተናተን ስልት

በዚህ ጥናት አጥኚዋ በዋነኛነት መጠናዊ የመረጃ ትንተና ዘዴን የጠቀመች ሲሆን በደጋፊነት ደግሞ አይነታዊ የመረጃ ትንተና ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ በዚህ መሰረት ከተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዳዎች በቅድመ እና በድህረ ፈተናዎችና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአሃዛዊና አይነታዊ አቀራረብ በመተንተን አሳይታለች፡፡ በአሃዛዊ የመረጃ አሰባሰብ የተሰበሰቡ መረጃዎች ሂሳባዊ ውሳኔ (parametric test) ለመስጠት ከምንጠቀምባቸው የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች መካከል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆነውን አንዱን እንደሚከተለው አጥኒዋ መርጣ ተግባራዊ አድርጋለች፡፡

በርካታ የአሃዛዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን t-test በመባል የሚታወቀውን የመተንተኛ ዘዴን በመተግበር በኮፒውተር SPSS እየተባለ የሚታወቀውን ሶፍት ዌር በመጠቀም ውጤቱን በመተንተን አጥኚዋ የጥናት ውጤቷን አግኝታለች፡፡ ሁለት የተመረጡ ቡድኖች በተለያየ መንገድ በሚያገኙት ድጋፍ የሚያሳዩቱ ውጤት ትርጉም ያለው ልይነት መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያገለግል ዘዴ መሆኑን (Gay and e.tal, 2012) ከዚህ በማስከተል በአይነታዊ የተሰበሰበውን መረጃ በተራኪ የአተናተን ዘዴ አማካይነት በመጠቀም አጥኒዋ በመተንተን በአሃዛዊ መንደገድ የተገኘውን ውጤት ለማስጌጥ ችላለች፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ምእራፍ በጥናቱ ሂደት የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑበት እና የተተረጎሙበት ሂደት ነው። ይህን ሂደት በማከናወን ሂደት ሁለት ቡድኖች ነበሩ። እነሱም የቁጥጥር ቡድን እና የሙከራ ቡድን በሚል የተዋቀሩ ናቸው። እንዚህ ቡድኖች ላይ በሚተገበረው ከፊል ሙከራዊ አካሄድ ላይ የሚገኘው ወይም የተገኘው ውጤት በልዩ ልዩ መንገድ በመሰብሰብ እና በመተንተን የተገኘውን ውጤት በመተርጎም ለማስቀመጥ ተሞክሯል ወይም ተችሏል። በዚህ ሂደት በጽሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ እና በፈተና አማካይነት መረጃዎችን ለመተንተን ተችሏል። የጽሑፍ መጠይቁም፣ምልከታዉ እንዲሁም የፈተና ሂደቱም ሁለት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምንም አይነት የተግባር ልዩነት ወይም የማስተማሪያ ዘይቤ ለውጥ ሳይደረግ ለተማሪዎች በማቅረብ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን፤በሁለተኛው ዙር ደግሞ ለሙከራዉ ቡድን ልዩ ልዩ ተግባራት ወይም ከተልምዷዊ አሰራር ወጣ ባለ መልኩ አንዴት ማስተማር እነዳለባቸው ለመ/ራን ልዩ የግንዛቤ ማስጨበጪያ መድረክ በማዘጋጀት እና ግንዛቤ በማስጨበት የተመረጠውን የሂደተ ዘውጋዊ ዘዴን አንዴት በክፍል ውስጥ ማስተማር እንዳለባቸው ለመ/ራን በተሰጣቸው ግንዘቤ ወይም የትግበራ ስልት አማካይነት ተማሪዎቸን እንዲያስተምሩ በማድረግ የተገኘውን ለውጥ በሶስት ደረጃ መረጃውን በመሰብሰብ እና በመተንተን የተገኘውን ለውጥ ሊያሳይ በሚችል መልኩ የተሰራበትን አካሄድ የሚያሳይ ክፍል ነው።

የትንተናው ዘዴ ወይም ሂደት በሁለት አይነት መንገድ ሲሆን የመጀመሪየው ከመጠይቅ እና ከምልከታ የተገኘውን መረጃ በመቶኛ(በፐርሰንቴጅ) ስልት የተተነተነ ሲሆን። በቅድመ ፈተና እና ድህረ ፈተና ውጤትን ደግሞ በቲ-ቴስት(t-test) ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሁለቱንም ዘዴ በSPSS የሚባለው የኮፒውተር መተግበሪያ ጥቅም ላይ ዉሏል።

### 4.1. አጠቃላይ መረጃዎች

1. **የሙከራ ቡድን** ብዛት፡- ወ= 24 ሴ=26 ድ= 50
   **የቁጥጥር ቡድን ብዛት፡-** ወ= 21 ሴ= 29 ድ=50
2. **ከሙከራ ቡድኑ፡-** ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ= - ሴ= - ድ= -
   መካከለኛ ደረጃ ላያ ያሉ ተማሪዎች፡-ወ= 12 ሴ= 13 ድ= 25

ዝተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ=11 ሴ=14 ድ= 25

**ከቁጥጥር ቡድኑ**፡-ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ=1 ሴ= - ድ= 1

መካከለኛ ደረጃ ላያ ያሉ ተማሪዎች፡-ወ= 5 ሴ= 16 ድ= 21

ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ=15 ሴ=13 ድ=28

3. **አማርኛ አፍ መፍቻ** ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች፡-

**የሙከራ ቡድን፡-**ወ= 12 ሴ= 15 ድ= 27

**ከቁጥጥር ቡድኑ፡-** ወ= 12 ሴ=16 ድ=28

4. **አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋቸው** የሆናቸው ተማሪዎች፡-

**የሙከራ ቡድን፡-** ወ= 12 ሴ= 11 ድ= 23

**ከቁጥጥር ቡድኑ፡-** ወ=9 ሴ= 13 ድ=22

## 4.2. ቅድም ትግበራ ውጤት

ሠንጠረዥ1. ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪ

መጠይቅ (ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ)

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % |
| 1 | የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | 26 | 52 | 21 | 42 | 3 | 6 |
| 2 | በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል? | | | | | 27 | 54 | 22 | 44 | 1 | 2 |
| 3 | የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያለህ/ሽ ልምድ እንዴት ይገለጸን? | | | | | 26 | 52 | 22 | 44 | 2 | 4 |
| 4 | በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | 33 | 66 | 14 | 28 | 3 | 6 |
| 5 | በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት | | | | | 31 | 62 | 17 | 34 | 2 | 4 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመከታተል ፍላጎትህ/ሽ ምን ይምስላል? | | | | | | | | | | |
| 6 | ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያለህ/ሽ ፍላጎት እንዴት ይታያል? | | | | | 30 | 60 | 20 | 40 | | |

ከፍ ሲል የቀረበው ሠንጠረዥ 1 ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና ለመለካት ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ ሲሆን በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ1-9) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው::

በዚህም ተራ ቁጥር “1” ላይ “የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል?” ለሚለው ጥያቄ (52%) ይኸውም 26 ተማሪዎች የሚሆኑት  በመካከለኛ ደረጃ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ (42%)ይኸውም 21 ተማሪዎች የሚሆኑት መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምዳቸው ዝቅተኛ ደረጃ እና (6%) ይኸውም 3 ተማሪዎች የሚሆኑት መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምዳቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በተራ ቁጥር “3” የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያላቸውን ልምድ እንዴት እንድሆነ ያመለከቱት (52)የሆኑት በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን (48)የሚሆኑት ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ በመሆናቸው የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ቃላት ወሳኝ በመሆኑ ቃላትን ለማጎልበት ያላቸው ጥረት ደግሞ አናሳ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል::

“በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል?” ለሚለው በተራ ቁጥር “2” ለቀረበው ጥያቄ 27 ተማሪዎች (54%) በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 23 ተማሪዎች (46%) ዝቅተኛድርሰት የመፃፍ ልምድ እንዳላቸው መረጃው ያሳያል፡፡

በተራ ቁጥር “4”  በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከንደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታ ላይ ለተጠየቁት (66%) ይኸውም 33 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (34%) ይኸውም 17 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን የመፃፍ እና አስተያየት የመቀበል ልምድ እንዳለ ለመረዳት ይቻላል፡፡ይህም ቢታገዝ አዳጊ እና ተሰረፋ ሰጪ ሁኔታ ይታይበታል፡፡

በተራ ቁጥር “5” በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በሚያታስተምሩበት ወቅት የመከታተል ፍላጎታቸው ምን እንደሚመስል በተጠየቁት (62%) ይኸውም 31 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (38%) ይኸውም 19 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ መምህሩ ሲያስተምሩ የመከታተል ፍላጎት በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ያሳያል፤ በተጨማሪም በተራ ቁጥር “6” ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያላቸውን ፍላጎት እንዳመለከቱት

60% በመከካለኛ ደረጃ ፍላጎት እንዳላቸው ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ 40% የሚሆኑት ተማሪዎች ዝቅተኛ ፍላጎት እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡

የቀጠለ...

ሠንጠረዥ 2 ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪ መጠይቅ (ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ)

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % |
| 7 | በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምድህ/ሽ እንዴት ነው? | | | | | 25 | 50 | 25 | 50 | | |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የሰጠችህን/ሽን አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመ/ሩ/ሯ የማሳየት ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | 30 | 60 | 20 | 40 | | |
| 9 | የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘህ/ሽ እንድተመጪ መ/ሩ/ሯ ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ እንዴት ይገለጻል? | | | | | 18 | 36 | 32 | 64 | | |

በተራ ቁጥር “7” በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምዳቸውን እንዳመለከቱት (50%) ይኸውም 25 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (25%) ይኸውም 25 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ ሲሆን በተራ ቁጥር “8” ላይ ከመምህር አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመ/ሩ/ሯ የማሳየት ልምቸውን በተመለከተ (50%) ይኸውም 25 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (25%) ይኸውም 25 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ እነደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘው ለመምጣት መምህራን ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ በተራ ቁጥር “9” በተገለፀው (64%) ይኸውም 32 ተማሪዎች የሚሆኑት

በዝቅተኛ ደረጃ ቀሪው (36%) ይኸውም 18 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ የፅሁፍ ቁሳቁስ ዝግጅት እንደሚያደርጉ መረጃው ያሳያል፡፡

ብዙ የመስኩ ሙሁራን እንደሚመክሩት ተማሪዎች የመፃፍ ተግባር ላይ ትኩረት እነዲሰጡ ፍላጎት እነዲኖራቸው የመምራት የመከታተሉ ያቸውን እነዲያሳድጉ ሚና መወጣት ያለባቸው መምህራን እነደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ Sklvia (1990)ተማሪዎች ዐውዳዊ እና ስነልሳናዊ ገጽታዎችን በሚገባ በማስተዋል ፅሁፍን ቅርፅ ለማስያዝ እና ለማዋቀር እንዲችሉ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ  ደረጀ ገብሬ (2011) በመፅሀፋቸው ሲገልፁ "ፅህፈት የትጉሃን ሥራ ነው፡፡" በማለት ይገልፃሉ፡፡ መምህራን ተማሪዎችን በፅህፈት ስራ በአንድ መንገድ ብቻ ሣይሆን የተለያዩ ስነዘዴዎችን በመጠቀም ልናተጋቸው የገባል፡፡ትጉሃን የማሰብ የመመርመር ፍላጎት ደጋግሞ የመሞከር ትዕግስት፤እንዲሁም የማይቻሉና የማይሰሩ የሚመስሉ ተግባራት ላይ አንዲተጉ ማድረግ እንደሚገባ የገልፃሉ፡፡ Ramines, 1993 በፅሁፉ ሲያብራራ ተማሪዎችን በመረጡት እና በተደራጀ መንገድ እንዲፅፉ እነዲለማመዱ ማድረግ መምህራን የአንበሳውን ድርሻ መወጣት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

የዘውግ አቀራረብ የሚታይ ስነ-ትምህርታዊነት አቀራረብ ቋንቋን ለማስተማር ስራ ላይ ውሏል፡፡ የዘውግ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪው ስለ ቋንቋ ግልጽ የሆነ እውቀት እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን በመምህሩ እና በተማሪው እንዲሁም በተማሪው እና በተማሪው መካከል ለሚኖረው መስተጋብር ዋጋ መስጠት ተገቢ እንደሆነ አበክረው ይመክራሉ፡፡

ሠንጠረዥ 3. የመ/ሩ ሚና በተመለከተ ከቁጥጥሩ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ከመገኘት አንጻር እንዴት ይገለጻሉ? | | | | | 23 | 46 | 19 | 38 | 8 | 16 |
| 2 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን ወይም ድረሰትን ለማስታመር የትርፍ ሰዓት የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይታያል? | | | | | 18 | 36 | 32 | 64 | | |

ከፍ ሲል የቀረበው ሠንጠረዥ 2 የመምህራን ሚና ለመለካት ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ ሲሆን በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ1-9) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

በዚህም በተራ ቁጥር “1” ላይ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ከመገኘት አንጻር 23 ተማሪዎች (46%) በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 27 ተማሪዎች (54%) ዝቅተኛ ድርሰት የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል  እንደማይገኙ መረጃው ያሳያል፡፡

“መምህራን የጽሑፍ ክሂልን ወይም ድረሰትን ለማስተማር የትርፍ ሰዓት የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይታያል?” በተራ ቁጥር “2” ለሚለው ጥያቄ 36% የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ አሰተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ሲያመለክት፤ ምንም እንኳን የምመህራን ተማሪዎችን በትርፍ ጊዜያቸው ማገዝ ለዚህ ክሂል መሻሻል ሚናው ላቅ ያለ ቢሆንም 64% የሚሆኑት መምህራን የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ዝቅተኛ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

የቀጠለ….

ሠንጠረዥ 3. የመ/ሩ ሚና በተመለከተ ከቁጥጥሩ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የተማሪዎችን የድረሰት ጽሁፍን በመመልከት ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ የመስጠት ሁኔታቸው እንዴት ይታያል? | | | | | 22 | 44 | 28 | 56 | | |
| 4 | ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ እና የድጋፍ ሁኔታ እንዴት ይታያል? | | | | | 19 | 38 | 30 | 60 | 1 | 2 |
| 5 | ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጸፉ በማድረግ በኩል የመ/ራን ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | 23 | 46 | 27 | 54 | | |

በተራ ቁጥር “3” ላይ የድረሰት ጽሁፍን በሚመለከት ከመምህራን ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ የማግኘት ሁኔታቸው በተመለከተ 22 ተማሪዎች (44%) በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 28 ተማሪዎች (56%) ይህም ለሚያደርጉት የፅሁፍ ተግባር የሚያገኙት ተከታታይነት ያለው ግብረ መልስ በዝቅተኛ ደረጃ እነደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም በተራ ቁጥር “4” ላይ እንድተገለፀው 62% የሚሆነው ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ እና የድጋፍ ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በተጨማሪም በተራ ቁጥር “5” ላይ ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጸፉ በማድረግ በኩል 54% የመ/ራን ድርሻ ዝቅተኛ እነደሆነና 46% የሆነው በመካከለኛ ደረጃ ሚና እንደነበራቸው አመልክተዋል፡፡

የቀጠለ…

ሠንጠረዥ 3 የመ/ሩ ሚና በተመለከተ ከቁጥጥሩ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል እንዴት ይታያል? | | | | | 18 | 36 | 32 | 64 | | |
| 7 | የድርሰት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | 20 | 40 | 30 | 60 | | |
| 8 | ተማሪዎች ድረሰት እያዘጋጁ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን በማበረታታት በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | 20 | 40 | 29 | 58 | 1 | 2 |
| 9 | ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሽ እንዴት ይገለጻል? | | | | | 25 | 50 | 25 | 50 | | |

በሠንጠረዥ "3" በተራ ቁጥር "6" ስር ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል የተከናወነ ተግባር በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ 18 ተማሪዎች (36%) በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 32 ተማሪዎች (64%) ይህም ተማሪዎች እርስ በእርስ ለመደጋገፍ የሚያስችል ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ እነደሆነ ያሳያል፡፡በተመሳሳይ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር "7" ለቀረበው ጥያቄ 40% ማለትም 20 ተማሪዎች መጠነኛ ድጋፍ እንዳለ ሲያመለክቱ ቀሪው 60% ማለትም 30 ተማሪዎች የድርሰት

ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ ዝቅተኛ እንደነበር መረጃው ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም በተራ ቁጥር “9” ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የተደረገውን አስተዋፅኦ 50% ማለትም 25 ተማሪዎች መካከለኛ አሰተዋፅኦ እና ቀሪው 50% የሆኑት ተማሪዎች በዚህ ሁኔታ በተጨማሪ ተግባር የማትጋቱን ሁኔታ ዝቅተኛ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 4. ቁጥጥር ቡድኑ ላይ የተደረገ የምልከታ ቼክሊስት የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | መለኪያ ተግባራት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰጣቸው የጽሑፍ ክሂል ት/ት በቂ ተሳትፎ ያሳያሉ፡፡ | | ✓ |
| 2 | ተማሪዎች በቡድን ድረሰት የመጻፍ ልምድ አላቸው/ፍላጎት አላቸው፡፡ | | ✓ |
| 3 | ተማሪዎች ከፍተኛ የቃላት ፍቺ አቅም አላቸው | | ✓ |
| 4 | ተማሪዎች ድርሰትን የመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ | ✓ | |
| 5 | መ/ራን ልዩ ልዩ የድረሰት ርእሶችን ለተማሪዎች በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ እንዲለማመዱ ያደርጋሉ፡፡ | ✓ | |
| 6 | ተማሪዎች በልዩ ልዩ ርዕሶች ዙሪያ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ ያበረታታሉ፡፡ | | ✓ |
| 7 | ተማሪዎች ድረሰት በመጻፍ በሚኒሚዲያ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ መልካም አውድ በክፍለ ውስጥ ፈጠረዋል፡፡ | | ✓ |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የጽሁፍ ክሂልን ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ይሰጣሉ? | | ✓ |

ከዚህ የምልከታ መከታተያ ቅፅ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን የተለያዩ የድርሰት ርዕሶች መፃፍ እንዲለማመዱ እንደሚሰጣቸውና ተማሪዎቹም ድርሰት መፃፍ ለመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው፣በቡድን ድረሰት የመጻፍ ልምዳቸው እና የቃላትን የመጠቀም ልምዳቸው ዝቅተኛ እነደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡በተጨማሪም ምምህራን ተምሪዎቹ ሲለማመዱ የማበረታታት ሁኔታ፣ድረሰት በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ  መልካም አውድ ከመፍጠር አናፃር እና ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ከመሰጠት አንፃር ክፍተትም እነዳለ መረጃው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 5. ከሙከራው ቡድን የተገኘ መረጃ ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር

የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % | ቁጥ | % |
| 1 | የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | 21 | 42 | 27 | 54 | 2 | 4 |
| 2 | በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል? | | | | | 20 | 40 | 29 | 58 | 1 | 2 |
| 3 | የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያለህ/ሽ ልምድ እንዴት ይገለጻን? | | | | | 21 | 42 | 28 | 56 | 1 | 2 |
| 4 | በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | 24 | 48 | 26 | 52 | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በምታስተምርበት ወቅት የመከታተል ፍላጎትህ/ሽ ምን ይምስላል? | | | | | 23 | 46 | 27 | 54 | | |
| 6 | ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያለህ/ሽ ፍላጎት እንዴት ይታያል? | | | | | 22 | 44 | 28 | 56 | | |

ከላይ ሠንጠረዥ 5 በቀረበው ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና ለመለካት ከሙከራ ቡድን የተገኘ መረጃ ሲሆን በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ1-6) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው።

በዚህም ተራ ቁጥር “1” ላይ “የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል?” ለሚለው ጥያቄ (42%) ይኸውም 21 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ (54%)ይኸውም 27 ተማሪዎች የሚሆኑት መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምዳቸው ዝቅተኛ ደረጃ እና (4%) ይኸውም 2 ተማሪዎች የሚሆኑት መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምዳቸው በጣም ዝቅተኛ ነው።

“በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል?” ለሚለው በተራ ቁጥር “2” ለቀረበው ጥያቄ 20 ተማሪዎች (40%) በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 30 ተማሪዎች (60%) ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ድርሰት የመፃፍ ልምድ እንዳላቸው መረጃው ያሳያል፡፡

በተራ ቁጥር “3” የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያላቸውን ልምድ እንዴት እንድሆነ ያመለከቱት (42%) የሆኑት በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን (58%)የሚሆኑት ደግሞ በዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ ደረጃ መሆናቸውን ሲገልፅ የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ቃላት ወሳኝ በመሆኑና ቃላትን ለማጎልበት ያላቸው ጥረት ደግሞ አናሳ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል::

በተራ ቁጥር “4” በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታ ላይ ለተጠየቁት (48%) ይኸውም 24 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (52%) ይኸውም 26 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን የመፃፍ እና አስተያየት የመቀበል ልምድ እንደሌለ ለመረዳት ይቻላል፡፡ይህም መምህራን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት እንዳልተወጡ መረጃው ያሳያል፡፡

በተራ ቁጥር “5” በክፍል ውስጥ መምህራን የጽሑፍ ክሂልን በሚያታስተምሩበት ወቅት የመከታተል ፍላጎታቸው ምን እንደሚመስል በተጠየቁት (46%) ይኸውም 23 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (54%) ይኸውም 27 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ መምህሩ ሲያስተምሩ የመከታተል ፍላጎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ ያሳያል፤ በተጨማሪም በተራ ቁጥር “6” ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያላቸውን ፍላጎት እንዳመለከቱት 44% በመከካለኛ ደረጃ ፍላጎት እንዳላቸው ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ 56% የሚሆኑት ተማሪዎች ዝቅተኛ ፍላጎት እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ከመረጃው ለመረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ መምህሩ ሲያስተምሩም ሆነ ለፅሁፍ ክሂልን ለማዳበር በራስ ተነሳሽነት ስሜት እንዲፈጠር የተደረገው ሁኔታ አናሳ መሆኑን ያሳያል፡፡

የቀጠለ…

ሠንጠረዥ 5. ከሙከራው ቡድን የተገኘ መረጃ ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምድህ/ሽ እንዴት ነው? | | | | | 21 | 42 | 29 | 58 | | |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የሰጠችህን/ሽን አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመ/ሩ/ሯ የማሳየት ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | 14 | 28 | 36 | 72 | | |
| 9 | የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘህ/ሽ እንድተመጪ መ/ሩ/ሯ ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ እንዴት ይገለጻል? | | | | | 21 | 42 | 29 | 58 | | |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተገለፀው በተራ ቁጥር “7” በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምዳቸውን እንዳመለከቱት (42%) ይኸውም 21 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (58%) ይኸውም 32 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ ሲሆን በተራ ቁጥር “8” ላይ ከመምህር አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመምህራን የማሳየት ልምቸውን በተመለከተ (28%) ይኸውም 14 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (72%) ይኸውም 36 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከል ልምድ ዝቅተኛ እነደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘው ለመምጣት መምህራን ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ በተራ ቁጥር “9” በተገለፀው (58%) ይኸውም 29 ተማሪዎች የሚሆኑት

በዝቅተኛ ደረጃ ቀሪው (42%) ይኸውም 21 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ የፅሁፍ ቁሳቁስ ዝግጅት እንደሚያደርጉ መረጃው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 6. የመ/ሩ ሚና ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ከመገኘት አንጻር እንዴት ይገለጻሉ? | | | | | 13 | 26 | 29 | 58 | 8 | 16 |
| 2 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን ወይም ድረሰትን ለማስታመር የትርፍ ሰዓት የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይታያል? | | | | | 21 | 42 | 29 | 58 | | |
| 3 | የተማሪዎችን የድረሰት ጽሁፍን በመመልከት ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ የመስጠት ሁኔታቸው አንዴት ይታያል? | | | | | 19 | 38 | 31 | 62 | | |
| 4 | ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ እና የድጋፍ ሁኔታ እንዴት ይታያል? | | | | | 19 | 38 | 31 | 62 | | |
| 5 | ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጸፉ በማድረግ በኩል የመ/ራን ድርሻ አንዴት ይታያል? | | | | | 22 | 44 | 28 | 56 | | |

በቅድመ ትግበራ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና የሚያሳይ ሠንጠረዥ ሲሆን በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ1-9) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

በዚህ ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር “1” ላይ “የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል?” ለሚለው ጥያቄ (26%) ይኸውም 13 ተማሪዎች የሆኑት መካከለኛና፤ (58%) ይኸውም 29 ተማሪዎች ዝቅተኛ ደረጃ ያመለከተ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ (16%)ይኸውም 8 ተማሪዎች የሚሆኑት መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምዳቸው በጣም ዝቅተኛ ደረጃ መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምድ እነዳለ አመልክተዋል። በተራ ቁጥር “3” የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያላቸውን ልምድ እንዴት እንድሆነ ያመለከቱት (38%)የሆኑት በመካከለኛ ደረጃ ሲሆን (62%)የሚሆኑት ደግሞ ዝቅተኛ ደረጃ በመሆናቸው የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ቃላት ወሳኝ በመሆኑ ቃላትን ለማጎልበት ያላቸው ጥረት ደግሞ ክፍተት ያለበት መሆኑን መረጃው ይጠቁማል::

“በልዩ ልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል?” ለሚለው በተራ ቁጥር “2” ለቀረበው ጥያቄ 21 ተማሪዎች (42%) መካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሆኑ የገለፁ ሲሆን የቀሩት 29 ተማሪዎች (58%) ዝቅተኛ ደረጃ ድርሰት የመፃፍ ልምድ እንዳላቸው መረጃው ይገልፃል።

በተራ ቁጥር “4” በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታ ላይ ለተጠየቁት (38%) ይኸውም 19 ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም መካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (62%) ይኸውም 31 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን የመፃፍ እና አስተያየት የመቀበል ልምድ ክፍተት እንዳለ ለመረዳት ይቻላል።ይህም በጉዳዩ ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ መውስድ እንደሚያስፈልግ መረጃው ያመላክታል።

በተራ ቁጥር “5” በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በሚያታስተምሩበት ወቅት የመከታተል ፍላጎታቸው ምን እንደሚመስል በተጠየቁት (44%) ይኸውም 22 ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም መካከለኛ ደረጃ እና የቀሩት (56%) ይኸውም 28 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ መምህሩ ሲያስተምሩ የመከታተል ፍላጎት በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ያሳያል፤ስለሆነም መምህራን የተምሪዎች ድርስት የመፃፍ ተግባርን በተሻለ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ከተለመደው የተለየ አካሄድ መከተል እንደሚገባ መረጃው ያመላክታል።

የቀጠለ...

ከሠንጠረዥ 6. የመ/ሩ ሚና ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል አንዴት ይታያል? | | | | | 18 | 36 | 32 | 64 | | |
| 7 | የድረስት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | 23 | 46 | 27 | 54 | | |
| 8 | ተማሪዎች ድረሰት እያዘጋጁ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን በማበረታታት በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | 20 | 40 | 30 | 60 | | |
| 9 | ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሽ እንዴት ይገለጻል? | | | | | 22 | 44 | 27 | 54 | 1 | 2 |

ከላይ በተገለፀው ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር “6” ስር ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል የተከናወነ ተግባር በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ 18 ተማሪዎች (36%) በጣም መካከለኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 32 ተማሪዎች (64%) ይህም ተማሪዎች እርስ በእርስ ለመደ.ጋገፍ የሚያስችል ሁኔታ በዝቅተኛ ደረጃ እነደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡በተመሳሳይ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር “7” ለቀረበው ጥያቄ 46% ማለትም 23 ተማሪዎች በጣም መካከለኛ ደረጃ ድጋፍ እንዳለ

ሲያመለክቱ ቀሪው 54% ማለትም 27 ተማሪዎች የድርሰት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ ዝቅተኛ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፤በተጨማሪም በተራ ቁጥር "8" ተማሪዎች ድረሰት እያዘጋጁ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን በማበረታታት በኩል የመ/ራን ድርሻ እንዴት እንደሆነ ለቀረበው ጥያቄ 40% በመካከለኛ ደረጃ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው 60% ክንውኑ በዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ መረጃው ያሳያል።

በመጨረሻም በተራ ቁጥር "9" ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የተደረገውን አስተዋፅኦ 44% ማለትም 22 ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ አሰተዋፅኦ እንዳለ ሲያመለክቱ ፣ 56% የሆኑት ተማሪዎች በዚህ ሁኔታ በተጨማሪ ተግባር የማትጋቱን ሁኔታ በዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ ደረጃ እንደሆነ አመልክተዋል፤ስለሆነም መምህራን የተምሪዎች ድርስት የመፃፍ ተግባርን በተሻለ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ከተለመደው አካሄድ የተለየ አካሄድ መከተል እንደሚገባ መረጃው ያመላክታል።

ሠንጠረዥ 7. ከምልከታ ቼክሊስት የተገኘ ውጤት(በቅድመ ትግበራ)

| ተ.ቁ | መለኪያ ተግባራት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰጣቸው የጽሑፍ ክሂል ት/ት በቂ ተሳትፎ ያሳያሉ። | | ✓ |
| 2 | ተማሪዎች በቡድን ድረሰት የመጻፍ ልምድ አላቸው/ፍላጎት አላቸው። | | ✓ |
| 3 | ተማሪዎች ከፍተኛ የቃላት ፍቺ አቅም አላቸው | | ✓ |
| 4 | ተማሪዎች ድርሰትን የመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። | ✓ | |
| 5 | መ/ራን ልዩ ልዩ የድረሰት ርእሶችን ለተማሪዎች በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ እንዲለማመዱ ያደርጋሉ። | ✓ | |
| 6 | ተማሪዎች በልዩ ልዩ ርዕሶች ዙሪያ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ ያበረታታሉ። | | ✓ |
| 7 | ተማሪዎች ድረሰት በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ መልካም አውድ በክፍለ ውስጥ ፈጠረዋል። | | ✓ |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የጽሁፍ ክሂልን ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ይሰጣሉ? | | ✓ |

ከዚህ የምልከታ መከታተያ ቅፅ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን የተለያዩ የድርሰት ርዕሶች መፃፍ እንዲለማመዱ እንደሚሰጣቸውና ተማሪዎቹም ድርሰት መፃፍ ለመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ቢሆንም የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው፣በቡድን ድረሰት

የመጻፍ ልምዳቸው እና የቃላትን የመጠቀም ልምዳቸው ዝቅተኛ እነደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡በተጨማሪም ምምህራን ተምሪዎቹ ሲለማመዱ የማበረታታት ሁኔታ፣ድረሰት በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መልካም አውድ ከመፍጠር አናፃር እና ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ከመሰጠት አንፃር ክፍተትም እነዳለ መረጃው ያሳያል፡፡

## 4.3. ቅድም ፈተና ውጤት

በዚህ ክፍል ስር ሁለቱም ቡድን በተልምዷዊው የማስተማር ሂደት ባለበት ወቅት ለተማሪዎች በቀረበ የጽሑፍ ፈተና የተገኘ የተማሪዎች ውጤት ላይ የተመሰረተ የመረጃ ትንተና እና ትርጉም ሂደት ነው፡፡

ምንም አይነት የተግባር ልይነት ሳይደረግ በቀድሞ የማስተማር ሂደት በነበሩበት ወቅት ሁለቱም ቡድኖች ተመሳሳይ ወይም ደግሞ አንዳይነት ፈተና ወይም ርእስ ተሰጥቷች በተገኘው ውጤት መሰረት የተማሪዎች የድረሰት የጻፍ ወይም የጽሁፍ ኪሂላቸው ሲለካ የተገኘው ውጤት በሚከተለው መልኩ የ SPSS ውጤታቸው ተቀምጦ ወይም ተገጸ ተተንትኗል፡፡

ሠንጠረዥ 8. ቅድመ ፈተና ውጤት

| Group Statistics | | | | | | P-value | Independent Samples Test | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | | t-value | df | L.con | P-value |
| ቅድመ ፈተና ውጤት | የቁጥጥር ቡድን | 50 | 4.5500 | 1.07973 | .15270 | 0.00 | .962 | 98 | 95% | .962 |
| | የሙከራ ቡድን | 50 | 4.5400 | 1.03923 | .14697 | 0.00 | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ የተገኘውን መረጃ አስመለክቶ የተገኘውን ውጤት ለመትንተን ያመች ዘንድ ሳይንሳዊ ትንታኔዎች እንዲመከተለው ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡ እንዲሚታየው ለዚህ መረጃ ብያኔ መስጠት ያመች ይዘንድ የታማኒነት ደረጃውን በ95% በማስቀመጥ የ የእድል ገጠመኙን 0.05 በታች ከሆነ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት መኖሩን በሌላ በኩል ደግሞ 0.05 በላይ ከሆነ ደግሞ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል ማለት ነው፡፡

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው በቅድመ ፈተና የሁለቱ ቡድኖች ውጤት እንዳሳየው አማካይ ውጤት የቅጥጥር ቡድኑ 4.5500 ሲሆን የሙከራ ቡድን ደግሞ 4.5400 የ t-ዋጋ ደግሞ 0.962 በሌላ በኩል የ P- ዋጋ ደግሞ 0.962 የሳያል፡፡ ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሰረት P-ዋጋ ከ0.05 በላይ ከሆነ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የውጤት ልየነት የለም ወይም

ተመሳሳይ ውጤት አላቸው ማለት ነው፡፡ እዚህጋ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በተለምዷዊ የፅሑፍ ክሂል ት/ት ሲማሩ በነበረበት ሂደት የደረጃ ልየኑነት እንደሌላቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለአጥኚው በጣሙን ጠቃሚ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል ለምን ቢባል ቀጥሎ በሚኬደው የትግበራ ልዩነት የሚገኘው ውጤት የዚህን ጥናት ውጤት በእጅጉ ለመወሰን ስለሚያስችል ነው፡፡

በተለየ መልኩ P-ዋጋ በተኛጥል የእያንዳንዱ ቡድን ሲታይ 0.00 ነው ይህ ማለት ዜሮ ነው ማለት ሳሆን ውጤቱ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከመሆነ የተነሳ በኮፒውተር ፕሮግራሙ መግለጽ ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በእያንዳንዱ ተናጥል ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በጣም የተለያየ ውጤት አንዳለቻው ለማይት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ ለየብቻ ሲታይ የታመሪዎች ውጤት ከፍተኛ እና ዝቅተኛ እንዲሁም በእያንዳንዱ የውጤት ደረጃ የተማሪዎች ቁጥር ወይም አሃዛዊ መረጃ ሲታይ አንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

ሠንጠረዥ 9. የቁጥጥር ቡድኑ  ተማሪዎች ውጤት

| pretest score | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Frequency | Percent | Minimum | Maximum |
| Valid | 3.00 | 7 | 14.0 | 3 | 8 |
| | 3.50 | 1 | 2.0 | | |
| | 4.00 | 18 | 36.0 | | |
| | 4.50 | 2 | 4.0 | | |
| | 5.00 | 12 | 24.0 | | |
| | 5.50 | 1 | 2.0 | | |
| | 6.00 | 7 | 14.0 | | |
| | 6.50 | 1 | 2.0 | | |
| | 8.00 | 1 | 2.0 | | |
| | Total | 50 | 100.0 | | |

ከላይ የተቀመጠው ውጤት እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ውጤት ሲታይ በቅድመ ፈተናው ከግማሽ በታች ያመጡ ተማሪዎች መጠን ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ የሚባል ውጤት እንዳስመዘገቡ ያሳያል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ሲታይ ከፍተኛ ውጤት 8 ሲሆን ዝቅተኛ ው ደግሞ 3 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ዘርዘር ባለ መልኩ ስንመከተው ከፍተኛ ተማሪዎች ማለትም 8 ያስመዘገቡ ታመሪዎች ብዛት አንድ ብቻ ሲሆን በመካከለኛ ደረጃ ላይ ያሉ ደግሞ ማለትም ከ5 እስከ 7.5 ውጤት ያላቸው ተማሪዎች 21 ተማሪዎች ሲሆኑ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ደግሞ 29 ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 10. የሙከራው ቡደን ተማሪዎች ውጤት

| | | Frequency | Valid Percent | Minimum | Maximum |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 3.00 | 8 | 16.0 | 3 | 6 |
| | 3.50 | 2 | 4.0 | | |
| | 4.00 | 14 | 28.0 | | |
| | 4.50 | 1 | 2.0 | | |
| | 5.00 | 16 | 32.0 | | |
| | 6.00 | 6 | 12.0 | | |
| | 6.50 | 3 | 6.0 | | |
| | Total | 50 | 100.0 | | |

በዚህ ቡድን ተማሪዎች የተገኘው ውጤት እንዲሚያሳየው ልክ እንደ ቁጥጥር ቡድኑ አብዛኛው ተማሪ ከማካይበታቸው ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ሲታይ ደግሞ ከፍተኛው 6 ዝቅተኛ ደግሞ 3 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ከላይ በተገኘው መረጃ መሰረት ምንም እንኳን በሁለቱም ቡደን ካሉ ተማሪዎች በአመዘኑ ዝቅተኛ ውጤት ቢያስመዘግቡም በአንጻራዊነት ሲታይ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የማለፍ ምጠኔያቸው ወይም ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል በሌላ በኩል ዝቅተኛው ውጤት በሁለቱመ ቡድን ተመሳሳይ ሲሆን ከፍተኛው ሲታይ ግን የቁጥጥር ቡድኑ 8 ሲሆን የሙከራው ቡደን ደገሞ 6 ነው ይህም የጎበዝ ተማሪዎች ውጤት ወይም ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪ  የተገኝበት ቡደን የቁጥጥር ቡድኑ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## 4.4. ድህረ ትግበራ ውጤት

**ተማሪዎችን**  የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ

**ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ**

በዚህ ሙከራዊ(ንጽጽራዊ) ቢጤ የጥናት ንድፍ አተገባበር ላይ በተደረገው አካሄድ ለለቁጥጥር ቡድኑ የተደረገ የተግባር የማተማሪያ ዘዴ ለውጥ ባለመኖሩ የተገኘ ከቅድመ ትግበራ ውጤት የተለየ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በድጋሚ ለማቅርብ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፤ምክንያቱም በቅድመ ትግበራ ውጤት ላይ ለማሳየት ስለተቻለ ነው፡፡

## ከሙከራው ቡድን የተገኘ መረጃ

የሙከራ ቡድኑ የመጻፍ ወይም የጽሑፍ ክሂልን ከተለደምዷዊ የማስተማር ዘዴ በመውጣት እና ሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ዘይቤን መ/ራን እንዲከተሉ እና እንዲያስተምሩ በማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ ለቁጥጥር ቡድኑ መ/ራን ከዚህ ቀደም ማለትም ተማሪዎቹ ለዚህ ጥናት በናሙናነት ከመመረጣቸው በፊት በነበረው ተልምዷዊ የድርሰት ወይም የጽሁፍ ክሂልን በሚያስተምሩበት መንገድ እንዲቀጥሉ የማድረግ ሂደትን ተማሪዎቹን ከሚያስተምሯቸው መ/ራን ጋር የመግባባት ስራ በተሰራበት ወቅት የሙከራ ቡድኑን ሊያስተምሩ የሚችሉበትን ዘይቤ የሚያመለክቱ ተግባራት ከዚህ አንደሚከተለው ያሉት ሲሆኑ እንዚህ ተግባራት መ/ራን ተግብረው የተገኘውን የውጤት ልዩነት ወይም የተገኘውን የተማሪዎች ውጤት በተያያዥነት ለመስቀመጥ ተችሏል፡፡ እንነዚህም ተግባራት በሚከተለው መልኩ ተቀምጣል፡፡ የህም ሲሆን የቁጥጥሩ ቡድን መ/ሩ ቀደምት ሲያስተምር በነበረበት አካሄድ አንዲቀጥል በማድረግ ነው፡፡

ተግባር 1፡- ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ እና እርስ በርሳቸው አስተያየት እንዲሰጣቱ በማድረግ እንዲማር የማድረግ ስራ ሰርተዋል፡፡

ተግባር 2፡-ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና ለቁጥጥር ቡድን ተመሳሳይ በርካታ የድርሰት ርእስ በመስጠት ከተሰጧቸው ርዕሶች ውስጥ ሁለቱም ቡድኖች መርጠው እንዲጽፉ በማድረግ ለሙከራ ቡድኑ በራሳቸው እንዲገመግሙ እንዲያርሙ እና አስተያየት ጭምር በመስጠት ለመ/ራቸው በማስረከብ ተጨማሪ አስተያየት መቀበል አንዲችሉ ማድረግ በሌላ በኩል መ/ራን ለተማሪዎቹ የአማርኛ ደርሰትን የማስተማሪያ ተለምዷዊ ሂደትን በተከተለ መልኩ ማስተማር እና ውጤታቸውን መመዘን ተቸሏል፡፡

ተግባር 3፡-የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደትን ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠሩ በማድረግ ለተማሪዎች ሙሉ የመማር ነጻነት በመስጠት የጹሑፍ ክሂልን የሚማሩበትን አዉድ ለሙከራ ቡድኖች መፍጠር ተችሏል፡፡

ተግባር 4፡-የሙከራ ቡድኖች ለጻፉት ድረሰት የተሰጣቸውን ውጤት መሰረት በማድረግ ስህተታቸውን በራሳቸው እንዲፈልጉ እና ማስተካካያ በማድረግ እንዲሁም ከሳይንሳዊ የድርሰት አጻጻፍ መዋቅር ጋር በማዛመድ ለረሳቸው አስተያየት አንዲሰጡ እና ስህተታቸውን በራሳቸው

እንዲያርሙ የማድረግ ሂደትን መከተል መስተማር ተችሏል፡፡

እንደዳጠቃላይ ከላይ የተገለጹት ተግባራት ተተግብረው የተገኘውን ውጤት እና ለውጥ ለመገምገም ይቻል ዘንድ በሚከተለው መልኩ በመጠይቅ፣በምልከታ እና በፈተና መረጃዎችን ለመስብሰብ እና ለመተንተን እንዲሁም ለመትጎም ተችሏል።

ሠንጠረዥ 11.ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | |
| 1 | የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | 6 | 12 | 23 | 46 | 21 | 42 | | | | |
| 2 | በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል? | 7 | 14 | 26 | 52 | 17 | 34 | | | | |
| 3 | የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያለህ/ሽ ልምድ እንዴት ይገለጻን? | 5 | 10 | 30 | 60 | 15 | 30 | | | | |
| 4 | በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታህ/ሽ እንዴት ይታያል? | 5 | 10 | 33 | 66 | 12 | 24 | | | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በምታስተምርበት ወቅት የመከታተል ፍላጎትህ/ሽ ምን ይምስላል? | 5 | 10 | 26 | 52 | 19 | 38 | | | | |

በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና የሚያሳይ ሠንጠረዥ ሲሆን

ከፍ ሲል የቀረበው ሠንጠረዥ 11 ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና ለመለካት ከቁጥጥሩ ቡድን የተገኘ መረጃ ሲሆን በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ1-9) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው::

በዚህ ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር “1” ላይ “የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል?” ለሚለው ጥያቄ (12%) ይኸውም 6 ተማሪዎች የሆኑት በጣም ከፍተኛና፤ (46%) ይኸውም 23 ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ ያመለከተ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ (42%)ይኸውም 21

ተማሪዎች የሚሆኑት መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምዳቸው በመካከለኛ ደረጃ  መዝገበ ቃላት የመጠቀም ልምድ እነዳለ አመልክተዋል፡፡ በተራ ቁጥር "3" የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያላቸውን ልምድ እንዴት እንድሆነ ያመለከቱት (70%)የሆኑት በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን (30%)የሚሆኑት ደግሞ መካከለኛ ደረጃ በመሆናቸው የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ቃላት ወሳኝ በመሆኑ ቃላትን ለማጎልበት ያላቸው ጥረት ደግሞ የተሸለ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል::

"በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል?" ለሚለው በተራ ቁጥር "2" ለቀረበው ጥያቄ 33 ተማሪዎች (66%)  በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደሆኑ የገለፁ ሲሆን የቀሩት 17 ተማሪዎች (34%) መካከለኛ ደረጃ ድርሰት የመፃፍ ልምድ እንዳላቸው መረጃው ይገልፃል፡፡

በተራ ቁጥር "4"  በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታ ላይ ለተጠየቁት (76%) ይኸውም 38 ተማሪዎች የሚሆኑት  በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ እና የቀሩት (24%) ይኸውም 12 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ በመካከለኛ ደረጃ በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን የመፃፍ እና አስተያየት የመቀበል ልምድ እንዳለ ለመረዳት ይቻላል፡፡ይህም በጣም ጥሩ  ተሰረፋ ሰጪ ሁኔታ ይታይበታል፡፡

በተራ ቁጥር "5" በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በሚያታስተምሩበት ወቅት የመከታተል ፍላጎታቸው ምን እንደሚመስል በተጠየቁት (62%) ይኸውም 31 ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ  ደረጃ እና የቀሩት (38%) ይኸውም 19 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ መምህሩ ሲያስተምሩ የመከታተል ፍላጎት በመካከለኛ  ደረጃ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የቀጠለ…

ሠንጠረዥ 11. በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎችን የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | |
| 6 | ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያለህ/ሽ ፍላጎት እንዴት ይታያል? | 8 | 16 | 25 | 50 | 17 | 34 | | | | |
| 7 | በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምድህ/ሽ እንዴት ነው? | 7 | 14 | 24 | 48 | 19 | 38 | | | | |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የሰጠችህን/ሽን አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመ/ሩ/ሯ የማሳየት ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | 8 | 16 | 26 | 52 | 16 | 32 | | | | |
| 9 | የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘህ/ሽ እንድተመጪ መ/ሩ/ሯ ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ እንዴት ይገለጻል? | 7 | 14 | 26 | 52 | 17 | 34 | | | | |

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተገለፀው በተራ ቁጥር “6” ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያላቸውን ፍላጎት እንዳመለከቱት 66% በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ፍላጎት እንዳላቸው ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ 34% የሚሆኑት ተማሪዎች በመከካለኛ ደረጃ ፍላጎት እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡

በተራ ቁጥር “7” በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምዳቸውን እንዳመለከቱት (62%) ይኸውም 31 ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን፤ የቀሩት (38%) ይኸውም 19 ተማሪዎች የሚሆኑት የሰጡት ምላሽ በመካከለኛ ደረጃ እነደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር “8” ላይ ከመምህር አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመምህራን የማሳየት ልምቸውን በተመለከተ (68%) ይኸውም 34 ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት (32%)

ይኸውም 16 ተማሪዎች የሚሆኑት  የሰጡት ምላሽ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከል ልምዳቸው በመካከለኛ ደረጃ  እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘው ለመምጣት መምህራን ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ በተራ ቁጥር "9" በተገለፀው (66%) ይኸውም 33 ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን ቀሪው (34%) ይኸውም 17 ተማሪዎች የሚሆኑት በመካከለኛ ደረጃ የፅሁፍ ቁሳቁስ ዝግጅት እንደሚያደርጉ መረጃው ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 12. የመ/ሩ ሚና ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ከመገኘት አንጻር እንዴት ይገለጻሉ? | 4 | 8 | 31 | 62 | 15 | 30 | | | | |
| 2 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን ወይም ድረሰትን ለማስታመር የትርፍ ሰዓት የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይታያል? | 8 | 16 | 27 | 54 | 15 | 30 | | | | |
| 3 | የተማሪዎችን የድረሰት ጽሁፍን በመመልከት ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ የመስጠት ሁኔታቸው አንዴት ይታያል? | 4 | 8 | 31 | 62 | 15 | 30 | | | | |
| 4 | ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ እና የድጋፍ ሁኔታ እንዴት ይታያል? | 5 | 10 | 33 | 66 | 12 | 24 | | | | |
| 5 | ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጸፉ በማድረግ በኩል የመ/ራን ድርሻ አንዴት ይታያል? | 7 | 14 | 25 | 50 | 18 | 36 | | | | |

ቀደም ሲል በሠንጠረዡ በቀረበው መረጃ የመምህራን ሚና ለመለካት ከሙከራ ቡድን የተገኘ መረጃ ሲሆን በመጠይቁ ስር የተካተቱ (ከ1-9) ጥያቄዎች እና ምላሾቻቸውን የሚያሳይ ነው:: በዚህም በተራ ቁጥር "1" ላይ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ከመገኘት አንጻር 35 ተማሪዎች (70%) በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 15 ተማሪዎች (30%) በመካከለኛ ደረጃ ድርሰት የመፃፍ ክሂል ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል እንደሚገኙ መረጃው ያሳያል፡፡

"መምህራን የጽሑፍ ክሂልን ወይም ድረሰትን ለማስተማር የትርፍ ሰዓት የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይታያል?" በተራ ቁጥር "2" ለሚለው ጥያቄ 70% የሚሆኑትበጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ አሰተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ሲያመለክት፤ የምመህራን ተማሪዎችን በትርፍ ጊዜያቸው ማገዝ ለዚህ ክሂል መሻሻል ሚናው ላቅ ያለ በመሆኑ ድጋፋቸው በመረጃው በግልፅ ተይቷል፤በሌላ በኩል 30% የሚሆኑት መምህራን የሚያደርጉት አስተዋፅኦ በመካከለኛ ደረጃ እንደሆነና ጥሩ አስተዋፅኦ እያደረጉ መሆኑ መረጃው ያሳያል፡፡

በተራ ቁጥር "3" ላይ የድረሰት ጽሁፍን በሚመለከት ከመምህራን ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ የማግኘት ሁኔታቸው በተመለከተ 35 ተማሪዎች (70%) በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያመለከቱ ሲሆን የቀሩት 15 ተማሪዎች (30%) ይህም ለሚያደርጉት የፅሁፍ ተግባር የሚያገኙት ተከታታይነት ያለው ግብረ መልስ በመካከለኛ ደረጃ እነደሆነ ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር "4" ላይ እንድተገለፀው 76% የሚሆነው ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ በጣም በከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ እየተከናወነ እንደሆነና የድጋፍ ሁኔታው አብዛ ከመካከለኛ ደረጃ በላይ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

በተጨማሪም በተራ ቁጥር "5" ላይ ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጸፉ በማድረግ በኩል 64% የመ/ራን ድርሻ በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ እነደሆነና ቀሪው 36% የሆነው በመካከለኛ ደረጃ ሚና እንደነበራቸው አመልክተዋል፡፡

የቀጠለ….

ሠንጠረዥ 12. የመ/ሩ ሚና በተመለከተ ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበ መረጃ

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | | ከፍተኛ(4) | | መካከለኛ(3) | | ዝቅተኛ(2) | | በ.ዝቅተኛ(1) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | |
| 6 | ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል አንዴት ይታያል? | 8 | 16 | 24 | 48 | 18 | 36 | | | | |
| 7 | የድረስት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ እንዴት ይታያል? | 10 | 20 | 21 | 42 | 19 | 38 | | | | |
| 8 | ተማሪዎች ድረሰት እያዘጋጁ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን በማበረታታት በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሻ እንዴት ይታያል? | 4 | 8 | 30 | 60 | 16 | 32 | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሽ እንዴት ይገለጻል? | 3 | 6 | 25 | 50 | 22 | 44 | | | | |

ከላይ በተገለፀው ሠንጠረዥ በተራ ቁጥር “6” ስር ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል የተከናወነ ተግባር በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ 32 ተማሪዎች (64%) በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ሲሆን የቀሩት 18 ተማሪዎች (36%) ይህም ተማሪዎች እርስ በእርስ ለመደጋገፍ የሚያስችል ሁኔታ በመካከለኛ ደረጃ እነደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡በተመሳሳይ በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር “7” ለቀረበው ጥያቄ 62% ማለትም 31 ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ እንዳለ ሲያመለክቱ ቀሪው 38% ማለትም 19 ተማሪዎች የድርሰት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ መካከለኛ እንደነበር

መረጃው ያመለክታል፤በተጨማሪም በተራ ቁጥር “8” ተማሪዎች ድረሰት እያዘጋጁ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን በማበረታታት በኩል የመ/ራን ድርሻ እንዴት እንደሆነ ለቀረበው ጥያቄ 68% በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው 32% ክንውኑ በመካከለኛ ደረጃ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

በመጨረሻም በተራ ቁጥር “9” ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የተደረገውን አስተዋፅኦ 56% ማለትም 28 ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ አሰተዋፅኦ እንዳለ ሲያመለክቱ እና ቀሪው 22% የሆኑት ተማሪዎች በዚህ ሁኔታ በተጨማሪ ተግባር የማትጋቱን ሁኔታ በመካከለኛ ደረጃ እንደነበር አመልክተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 13. ከምልከታ ቼክሊስት የተገኘ ውጤት(ከሙከራ ቡድኑ)

| ተ.ቁ | መለኪያ ተግባራት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰጣቸው የጽሑፍ ክሂል ት/ት በቂ ተሳትፎ ያሳያሉ፡፡ | ✓ | |
| 2 | ተማሪዎች በቡድን ድረሰት የመጻፍ ልምድ አላቸው/ፍላጎት አላቸው፡፡ | ✓ | |
| 3 | ተማሪዎች ከፍተኛ የቃላት ፍቺ አቅም አላቸው | | ✓ |
| 4 | ተማሪዎች ድርሰትን የመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ | ✓ | |
| 5 | መ/ራን ልዩ ልዩ የድረሰት ርእሶችን ለተማሪዎች በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ እንዲለማመዱ ያደርጋሉ፡፡ | ✓ | |
| 6 | ተማሪዎች በልዩ ልዩ ርዕሶች ዙሪያ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ ያበረታታሉ፡፡ | ✓ | |
| 7 | ተማሪዎች ድረሰት በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ መልካም አውድ በክፍለ ውስጥ ፈጠረዋል፡፡ | ✓ | |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የጽሁፍ ክሂልን ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ይሰጣሉ? | ✓ | |

ከዚህ የምልከታ መከታተያ ቅፅ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን የተለያዩ የድርሰት ርዕሶች መፃፍ እንዲለማመዱ እንደሚሰጣቸውና ተማሪዎቹም ድርሰት መፃፍ ለመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው እና የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው፣በቡድን ድረሰት የመጻፍ ልምዳቸው እና የቃላትን የመጠቀም ልምዳቸው ከቅድመ ትንበራው ዝቅተኛ ቢሆንም በትግበራው መሻሻል እንዳለ መረጃው ያሳያል፡፡በተጨማሪም መምህራን ተምሪዎቹ ሲለማመዱ የማበረታታት ሁኔታ፣ድረሰት በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መልካም አውድ

ከመፍጠር አናፃር እና ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ከመስጠት አንፃር ክፍተቱም እየተቀረፈ እንደመጣ መረጃው ያሳያል፡፡

## 4.5. ድህረ ፈተና ውጤት

ሠንጠረዥ 14. ድህረ-ፈተና ውጤት አንድ

| Group Statistics | | | | | | Independent Samples Test | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | t-value | df | L.con | P-value |
| ድህረ-ፈተና ውጤት | የቁጥጥር ቡድን | 50 | 4.7800 | 1.07930 | .15264 | -4.696 | 95.464 | 95% | .000 |
| | የሙከራ ቡድን | 50 | 5.7200 | .91562 | .12949 | | | | |

ከላይ የተቀመጡ የሂደተ ዘውጋዊ አሰራሮች ወይም የማስተማር ዘይቤዎች ከተተገበሩ በኋላ ቡለቱ ቡድኖች መካከል የተገኘውን ውጤት ከዚህ አንደሚከተለው ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡ አማከይ ውጤት የቁጥጥር ቡድኑ 4.7800 ሲሆን የሙከራ ቡደን ደግሞ 5.7200 ሆኖ ተመዝግቧል በሌላ ቡኩል ደግሞ t-ዋጋ ደግሞ -4.696 ሲሆን P-ዋጋ ደግሞ -000 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በዚህ መረጃ መሰረት ሁለቱ ቡድኖች ያስመዘገቡት ውጤት ሲታይ ልይነት መኖሩን ያሳያል፤ይህም ሲባል በአማካይ ዋጋቸው ሲወዳደሩ የሙከራ ቡድኑ የተሸለ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ እዚህ ላይ ማየት የተቻለው ተማሪዎች በሂደት ዘውጋዊ መማራቸው ለውጤታቸው መሻሻል እንደ ምክንያት ተወስዷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በእያንዳንዱ ቡድን የተናጥል ውጤት በእያንዳንዱ የውጤት ግኝት ለማየት እና የማለፍ ምጣኔውን ለመከታት ይቻል ዘንድ እንዲሁም ከፍተኛ ውን ቅጤት እና ዝቅተኛውን ውጤት ለመለየት ይቻል ዘንድ በሚከተለው መልኩ ተቅምጧል፡፡

ሠንጠረዥ 15. የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ውጤት

| | | Frequency | Valid Percent | Minimum | Maximum |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 3.00 | 5 | 10.0 | 3 | 8.5 |
| | 4.00 | 15 | 30.0 | | |
| | 4.50 | 1 | 2.0 | | |
| | 5.00 | 16 | 32.0 | | |
| | 5.50 | 4 | 8.0 | | |
| | 6.00 | 7 | 14.0 | | |
| | 7.00 | 1 | 2.0 | | |
| | 8.50 | 1 | 2.0 | | |
| | Total | 50 | 100.0 | | |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት እንደተሞከረው በመጀመሪያው የድህረ ፈተና ውጤት ላይ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ቁጥር ከቅድመ ፈተና አንጻር ሲታይ መሻሻል ታይቶበታል፡፡ ይህም ከላይ የተሰጠው ትንታኔ  እና ትረጉም ትክክል መመሆኑን የበለጠ ለማረጋጋጥ አንደ አጋዥ ተደርጎ መውሰድ ይቻላል፤ይሁን እንጂ አሁንም ከፍተኛ ተማሪዎች እዚያው ዝቅተኛ ውጤት ውስጥ ከመሆናቸው በላይ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ውጤት ላይ እንብዛም ልዩነት አልተገኘም፡፡

ሠንጠረዥ 16. የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ውጤት

| post test 1 score | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Frequency | Valid Percent | | |
| Valid | 4.50 | 1 | 2.0 | | |
| | 5.00 | 22 | 44.0 | | |
| | 5.50 | 7 | 14.0 | | |
| | 6.00 | 9 | 18.0 | | |
| | 6.50 | 4 | 8.0 | | |
| | 7.00 | 1 | 2.0 | | |
| | 7.50 | 4 | 8.0 | | |
| | 8.00 | 2 | 4.0 | | |
| | Total | 50 | 100.0 | | |

የሙከራው ቡደን ከላይ ባለው መረጃ መሰረት ከቅድመ ፈተና ውጤቱ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ለውጥ ታይቷል፡፡ በዚሁ ውጤት ላይ ከላይ ካለው ከቁጥጥር ቡድኑ አንጻሸር ሲታይ የሙከራ በድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ከፍተኛ የማለፍ ምጣኔ አሳይተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሂደተ

ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል ለማስተማር አዋጭ መሆኑን ከተማሪዎቹ ውጤት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 17. ድህረ-ፈተና ውጤት ሁለት

| Group Statistics | | | | | | Independent Samples Test | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | t-value | df | L.con | P-value |
| ድህረ-ፈተና ውጤት | የቁጥጥር ቡድን | 50 | 4.7500 | .87043 | .12310 | -9.067 | 79.321 | 95% | .000 |
| | የሙከራ ቡድን | 50 | 6.9500 | 1.47859 | .20910 | | | | |

በድህረ ፈተና መግቢያ አካባቢ የተቀመጡተን የሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ዘይቤዎችን በድጋሚ በማጠናከር እና በማደራጀት መምህራን አጠናክረውን የታዩ ክፍቶችን በማሻሻል እንዲተገብሩ በማድረግ ለሁለተኛ ጊዜ ፈተና ለሁለቱም ቡድን በመስጥ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ስሌት 4.7500 ሲሆን የሙከራ ቡደድኑ ደግሞ 6.9500 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ t-v ዋጋ -9.067 ሲሆን P-ዋጋ ደግሞ .000፡፡ እዚህ ላይ እንደሚታየው P-ዋጋ ዜሮ የሚታየው ዜሮ ሆኖ ሳይሆን በኮፒውተር ፕሮግራሙ በጣም ትንሽ የሆነውን ዋጋ በዚህ ሶስት ዲጅት ማስቀመጥ ባለመቻሉ እንደሆነ ከግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ያም ሆነ ይህ የ P-ዋጋ ከተቀመጠው መቁረጫ ዋጋ በእጅጉ ያነሰ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የውጤት ልዩነት መኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ በአማካይ ዋጋቸው ስናነጻጽራቸው የሙከራው ቡደን ተማሪዎች የተሸለ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውን ለማየት ትችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ወይም ዘይቤ ተማሪዎችን የመጻፍ ኪህልን ለማስተማር ጠቀሚታ እንዳለው ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 18. የቁጥጥር ቡድን

| | | Frequency | Valid Percent | Minimum | Maximum |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 3.00 | 3 | 6.0 | 3 | 7.5 |
| | 4.00 | 15 | 30.0 | | |
| | 4.50 | 3 | 6.0 | | |
| | 5.00 | 18 | 36.0 | | |
| | 5.50 | 5 | 10.0 | | |
| | 6.00 | 5 | 10.0 | | |
| | 7.50 | 1 | 2.0 | | |
| | Total | 50 | 100.0 | | |
| | 3.00 | 3 | 6.0 | | |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት እንደተሞከረው በመጀመሪያው የድህረ ፈተና ሁለት ላይ ዝቅተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ቁጥር ከቅድመ ፈተና እና ከድህረ ፈተና ሁለት ውጤት አንጻር አንጻር ሲታይ መሻሻል ታይቶበታል፡፡ ይህም ከላይ የተሰጠው ትንታኔ እና ትረጉም ትክክል መመሆኑን የበለጠ ለማረጋጋጥ አንደ አጋዥ ተደርጎ መውሰድ ይቻላል፤ይሁን እንጂ አሁንም ከፍተኛ ተማሪዎች እዚያው ዝቅተኛ ውጤት ውስጥ ከመሆናቸው በላይ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ውጤት ላይ እንብዛም ልዩነት አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ ላይ የነበረ ተማሪ ወደ መካከለኛ ዝቅ ብሎ የታየበት ሁኔታም አለ፡፡

ሠንጠረዥ 19. የሙከራ ቡድን

| | | Frequency | Valid Percent | Minimum | Maximum |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 5.00 | 8 | 16.0 | 5 | 9.5 |
| | 5.50 | 3 | 6.0 | | |
| | 6.00 | 10 | 20.0 | | |
| | 6.50 | 4 | 8.0 | | |
| | 7.00 | 5 | 10.0 | | |
| | 7.50 | 6 | 12.0 | | |
| | 8.00 | 2 | 4.0 | | |
| | 8.50 | 3 | 6.0 | | |
| | 9.00 | 4 | 8.0 | | |
| | 9.50 | 5 | 4.9 | | |
| | | 50 | 100 | | |

የሙከራው ቡደን ከላይ ባለው መረጃ መሰረት ከቅድመ ፈተና ሆነ ከድህረ ፈተና ውጤቱ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ለውጥ ታይቷል፡፡ በዚሁ ውጤት ላይ ከላይ ካለው ከቁጥጥር ቡድኑ አንጻሽር ሲታይ የሙከራ በድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ከፍተኛ የማለፍ ምጣኔ አሳይተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎችን የጽሑፍ ክሂል ለማስተማር አዋጭ መሆኑን ከተማሪዎቹ ውጤት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሂደቱ ለውጥ አምጪ እና አዋጪ ዘዴ መሆኑን ከመረጃው ለማየት ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 20. በሁለቱ ቡዶኖች መካከል የታዩ ለውጦች

| | የፈተናው አይነት | ከፍተኛ ደረጃ ውጤት የስመዘገቡ | መካከለኛ ደረጃ | ዝቅተኛ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ፈተና | የቁጥጥር ቡድን | 1 | 21 | 28 |
| | የሙከራ ቡድን | 0 | 25 | 25 |
| ድህረ ፈታና አንድ | የቁጥጥር ቡድን | 1 | 27 | 21 |
| | የሙከራ ቡድን | 2 | 47 | 1 |
| ድህረ ፈተና ሁለት | የቁጥጥር ቡድን | 0 | 29 | 21 |
| | የሙከራ ቡድን | 14 | 36 | 0 |

ከላይ በሰንጠረዥ ለማመልከት እንደተቻለው በነበረው ሂደት በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ልዩነቶች ታይተዋል፡፡ መለትም በሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ከተማሩት እና በዘልማዳዊው የማስተማር ዘዴ በተማሩት ተማሪዎች መካከል ልዩነቶች ታይተዋል ይሄዉም

በሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ሂደት የተማሩት ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ይልቅ ከፍተኛ የውጤት ማሻሻል ከማሳየት ባለፈም የማለፍ ምጣኔያቸው ከፍተኛ መሆኑን ጭምር ለማየት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ፣ግኝት፣መደምደሚያ እና አስተያየት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጋሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት ሂደተ ዘውግ ተኮር የማስተማር ዘዴ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ሚና መመርመር ነው፤ በመሆኑም የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የሚከተሉት የማጠቃለያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል።

### 5.1. ማጠቃለያ ና ግኝት

የጥናቱን ግኝቶች ለማጠቃለል የሚከተሉትን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ነው።

በዚህ ፍተሻ ሂደትም ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ እና የተቀመጠን መላምት ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው። እነሱም፡-

1. ሂደት ወዘውግ ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር ያለውን ፋይዳ ምንድ ነው?
2. ሂደት ወዘውግ ዘዴ በመጠቀም በተማሪዎች የመጻህፍ ትምህርት ላይ ሊያመጣ የሚችለውን የአመለካከት ለውጥ ምን ይመስላል?
3. በመምህራን ልማዳዊ የማስተማር ዘዴ ሂደት የታዩ ችግሮችን ምን ይመስላሉ?
4. መላምት ፍተሻ

1. ሂደት ወዘውግ ዘዴ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር ያለው ፋይዳ

ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት እንዲቻል በሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሊያሳኩ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተመርጠዋል። በተተኳሪነት የቀረበው በዋነኛነት የፅሁፍ መጠይቅ ፣ ምልከታ እና ቅድመና ድህረ ፈተን ውጤትን በመጠቀም የትኩረት ነጥቦቹን ለይቶ በማውጣት በቂ ትንተናና ማብራሪያ ከተደረገ በኋላ በተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ክሂል ላይ ሂደተ ወዘውግ የማስተማር ዘዴ በተተገበረላቸው የሙከራ ቡድን ከቁጥጥሩ ቡድን የተሻለ የትግበራ ውጤት ማሳየት ችለዋል፤ በዚህም ማረጋገጥ እነደተቻለው ከተለምዷዊው የፅሁፍ ክሂልን የማስተማር ዘዴ ይልቅ ሂደተ ወዘውግ አዋጪና ፋይዳ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

በሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ዘዴ ከተማሩት እና በዘልማዳዊው የማስተማር ዘዴ በተማሩት ተማሪዎች መካከል ልዩነቶች ታይተዋል ይሄዉም በሂደተ ዘውጋዊ የማስተማር ሂደት የተማሩት ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ይልቅ ከፍተኛ የውጤት ማሻሻል ከማሳየት ባለፈም የማለፍ ምጣኔያቸው ከፍተኛ መሆኑን ጭምር ለማየት ተችሏል፡፡ በሂሳባዊ ስሌት ለማሳየት ያህል የሙከራ ቡድኑ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ከ 0% ወደ 28% ያደገ ሲሆን ፤የቁጥጥር ቡድኑ ግን ከ2% ወደ 0% ከመሻሻል ይልቅ መቀነስ አሳይቷል፤ ስለዚህ የሂደተ ወዘውግ የማስተማር ዘዴ የፅሁፈ ክሂልን ለማስተማር የጎላ ፋይዳ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

2.ሂደት ወዘውግ ዘዴ በመጠቀም በተማሪዎች የመጻህፍ ትምህርት ላይ ያመጣው

የአመለካከት ለውጥ

የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያላቸውን ልምድ እንዴት እንድሆነ ያመለከቱት 70%የሆኑት በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ደረጃ በመሆናቸው የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ቃላት ወሳኝ በመሆኑና ቃላትን ለማጎልበት ያላቸው ጥረት ደግሞ የተሻለ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል:: 66% ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ የመፃፍ ልምድ እንዳላቸው መረጃው ይገልፃል፡፡76% ተማሪዎች የሚሆኑት በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ ደረጃ በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን የመፃፍ እና አስተያየት የመቀበል ልምድ እንዳለ ለመረዳት ይቻላል፡፡ይህም በጣም ጥሩ ተሰፋ ሰጪ ሁኔታ ይታይበታል፡፡

62% ተማሪዎች የሚሆኑት ከፍተኛ ደረጃ መምህሩ ሲያስተምሩ የመከታተል ፍላጎት እነዳላቸው አመልክተዋል፡፡ ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያላቸውን ፍላጎት እንዳመለከቱት 66% ከፍተኛ ደረጃ ፍላጎት እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ 62% የሚሆኑት ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ ደረጃ እነደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ 68% የሚሆኑት ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ እነደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

በመጨረሻም የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘው ለመምጣት መምህራን ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ 66% የሚሆኑት ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ የፅሁፍ ቁሳቁስ ዝግጅት እንደሚያደርጉ መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም በዘውግ ሂደት ተኮር የተማሩት ተማሪዎች ከልማዳዊ የማስተማር ዘዴ ከተማሩት ተማሪዎች የፅሁፍ ክሂልን ለመማር የተሻለ አመለካከት እንዳላቸው መረጃው ያሳያል፡፡

3. መምህራን ልማዳዊ የማስተማር ዘዴ በመተግበር ሂደታቸው የታዩ ችግሮች

የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ይዘው አለመገኘት፣ድረሰትን ለማስተማር በትርፍ ጊዜያቸው ማገዝ አለመቻል፣ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ መስጠት አለመቻል፣ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለመቻል፣በተጨማሪም ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጽፉ በማድረግ በኩል ሚና ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብን በክፍሉ ውስጥ በመተግበር ረገድ የጊዜ እጥረት፣ የተማሪዎች የመፃፍ ዳራ፣ የባህል ተጽዕኖ፣ የመማሪያ ክፍሎች ሰፊነትና የውይይትና የመተጋገዝ እጥረት እንዲሁም የቋንቋ እጥረት ያለባቸው ተማሪዎች በክፍሉ ውስጥ መኖር ትምህርቱን በመተግበር ረገድ እንደችግር የታዩ ነጥቦች ናቸው። መረጃው በግልፅ አሳይቷል።በቅደመ ትግበራ ወቅት በቁጥጥር እና ሙከራ ቡድኑ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከላይ የተጠቀሱት የመምህራን ሚና እጅግ ዝቅተኛ እንደነበረና በድህረ ትግበራ ወቅት የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው በቁጥጥር ቡድኑቤመምህራን ሚና እነደዛው የቀጠለ ሲሆን በሙከራ ቡድኑ ግን የተሻለ መሆኑ ታይቷል፤ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሱት ተግዳሮቶች ሙሉ በሙሉ ተፈተዋል ማለት አይቻልም።

4.መላምት ፍተሻ

በጥናቱ መጀመሪያ ላይ በሚከተለው መልኩ የተቀመጡትን መላምቶች ለመፈተሽ ይቻል ዘንድ የቲ-ቴስት የመረጃ ትንተና ዓይነትን SPSS በመጠቀም የተገኘውን ግኝት በሚከተለው መልኩ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

1. በሂደተ ዘውግ ተኮር እና በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል አቀራረብ በተማሩ ተማሪዎች መካከል ትርጉም ያለው ልዩነት የለም።
2. በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል አቀራረብ የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ የፅሁፍ ክሂል ውጤት አላቸው።
3. በሂደተ ዘውግ ተኮር የተማሩ ተማሪዎች በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ የፅሁፍ ክሂል ውጤት አላቸው።

በምዕራፍ አራት ለመግለፅ እንደተሞከረው እና አብዛኛው የጥናትና ምርምር ማጠቀሻ መፅሀፍት እንደሚያሳዩት የቲ-ቴስት የመረጃ ትንተና ውጤትን ለዜሮ መላምት ፍተሻ ለመጠቀም የሚከተሉትን መስፈርቴች ሰተዋል።እሱም የቲ-ቴስት ዋጋ ሲጨምር የፒ ዋጋ ይቀንሳል፤ከዚህ በተጨማሪ የፒ ዋጋ ከ0.05 በላይ የሚሆን ከሆነ የዜሮ መላምቱ ተቀባይነት

የኖረዋል፡፡ነገርግን የፒ ዋጋ ከተጠቀሰው በታች ከሆነ የዜሮ መላምት ወድቅ ይሆናል፡፡የህን መስፈርት መሰረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ማሰቀመጥ ተሞክሯል፡፡

በጥናቱ የተገኘው ግኝት እንደሚያሳየው በቅድመ ፈተና ውጤት መሰረት የሁለቱ ቡድኖች የቲ-ቴስት ዋጋ 0.962 ሲሆን የፒ ዋጋም 0.962 ነው፡፡ይህም የሚያሳየው የፒ ዋጋ ከ0.05 በላይ መሆኑን ነው፤ በመሆኑም በቅድመ ፈተና ወቅት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የውጤት ለውጥ አለመኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡ይህ ማለት ሁለቱም ቡድኖች በተመሳሳይ መንገድ ሲማሩ ስለነበረና ተመጣጣኝ የአቅም ደረጃ ስለነበራቸው ልዩነት አልተመዘገበም፡፡

በድህረ ፈተና ውጤት መሰረት የሚከተሉት ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ የህም ማለት በመጀመሪያው ዙር የተማሪዎች አማካይ ዉጤት መሰረት ተደርጎ በተሰራ የቲ-ቴሰት ዋጋ 4.696 ሲሆን የፒ ዋጋ 0.00 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በሁለተኛው ዙር የአማካይ ውጤት ደግሞ የቲ-ቴስት ዋጋ 9.067 ሲሆን የፒ ዋጋ 0.00 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ውጤት መሰረት የዜሮ መላምቱ ስፈተሸ በሁለቱም ቡድኖች መካከል ከፍተኛ የውጤት ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡በዚህ መረጃ መሰረት ዜሮ መላምቱ ውድቅ ተደርጓል፡፡

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የዜሮ መላምቱ ውድቅ በደረግም የትኛው ቡድን ላይ የተሻለ ውጤት ወይም ደግሞ ከዘልማዳዊው እና ከሂደተ ዘውግ የፅሁፍ ክሂልን የማስተማር ዘዴ መካከል በተማሪዎች የመማር ውጤት ላይያመጣውን ለውጥ ለማሳየት በሚከተለው መልኩ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በድህረ ፈተና ወቅት በመጀመሪያው ዙር የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት 4.75 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ 5.72 ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን በሁለተኛው ዙር አማካይ ውጤት ደግሞ የቁጥጥር ቡድኑ 4.78 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ውጤት ደግሞ 6.95 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በዚህ ውጤት መሰረት የአማራጭ መላ ምቶችን ስንፈትሽ በሂደተ ዘውግ ተኮር የተማሩ ተማሪዎች በዘልማዳዊ የፅሁፍ ክሂል የማስተማር ዘዴ ከተማሩ ተማሪዎች የተሻለ የፅሁፍ ክሂል ውጤት ማሳየታቸው ተረጋግጧል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

ከጥናቱ ግኝት በመነሳት የሚከተለውን መደምደሚያ ለመስጠት ተችሏል።በመርሃ ትምህርቱ (በልማዳዊ) መጻፍን ማስተማርያ ዘዴ ብቻ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በቂ ደረጃ ላይ አያደርስም፤ በመሆኑም በሂደተ ዘውጋዊ መጻፍን ማስተማርያ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታ ለማሻሻል አውንታዊ ተፅዕኖ ለመፍጠር ሚናው የጎላ ነው። "በወጉ ያረሰ እንደልቡ ጎረሰ" እንደሚባለው መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጊዜያቸውን፣ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን ምንም ሳይሰስቱ በቁርጠኝነት ማበርከት ከቻሉ እና አዳዲስ አሰራሮችን እየተከተሉ መስራት ከቻሉ በተማሪዎቻቸው ላይ የሚፈለገውን ለውጥ ማየት እንደሚቻል ከዚህ ጥናት መረዳት ይቻላል።

## 5.3. አስተያየት

የሂደታዊ ዘውግ የመጻፍ ማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በማሻሻል ረገድ ያለውን ውጤታመነት መፈተሽ ላይ ትኩረት አድርጎ የተካሄደው ይህ ጥናት በፈተና እና በምልከታ አማካኝነት ያገኛቸውን መረጃዎች በገላጭ እስታቲክስ ስልት በመተንተን የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ ከተለያዩ ድምዳሜዎች ላይ ተደርሷል። በመሆኑም ፡-

1. በመርሃ ትምህርቱ ላይ የቀረበውን የመጻፍ ማስተማርያ ዘዴ ላይ ብቻ በመመስረት የተማሪዎችን የመፃፍ ክኂልን በቂ ደረጃ ላይ ማድረስ እንደማይቻል ተገንዝበን አማራጭ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችንም ልንጠቀም ይገባል። ሂደታዊ ዘውግ የመፃፍ ማስተማርያ ዘዴንም በመጠቀም የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።
2. የተማሪዎችን የመፃፉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሂደታዊ ዘውግ የመፃፍ ማስተማርያ ዘዴን መጠቀም የጎላ ሚና ይኖረዋል።
3. ተማሪዎች መጻፍን እንደ ከባድ ተግባር በማየት እንዳይጨናነቁ ሂደታዊ ዘውግ የመፃፍ ማስተማርያ ዘዴን መጠቀሙ ውጤታማነት ይኖረዋል፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት በመምህራን የሚያቀርበው ትምህርት፣ የተማሪዎችን ምርጫ መሰረት አድርጎ በፍላጎትና በነፃነት እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ሊሆን ይገባል።
4. የትምህርት ባለድርሻዎች ማለትም በሱፐርቫይዘሮች እና ርዕሰ መምህራን የሂደታዊ ዘውግ ግንዛቤ ኖሯቸው ግንዛቤ በመፍጠር መከታተል እንዲችሉ መምህራን የሂደተ ዘውጋዊ አቀራረብን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የሚጠበቀው ትምህርታዊ ለውጥ

እንዲመጣ ተማሪዎች አዲሱን አቀራረብ በሚገባ እንዲረዱት እና በትምህርቱ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ በቂ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

5. የመማሪያ እና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች የይዘት ምርጫውን እና አደረጃጀቱን በሂደተዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትግበራ በሚያመች ሁኔታ ሊያደርጉት ይገባል፡፡
6. የመምህራንን አፈፃፀም በመከታተል ሙያዊ እገዛ ለማድረግ የሚሹ አካላት በዚህ የሚያበቃቸው ግንዚቤ ያላቸው እና የሠለጠኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡

# ዋቢ ፅሁፎች


ሀና ታምራት:: (2003):: "በሆሳህና መምህራን ትምህርት ኮሊጅ የአማርኛ ጽህፈት ክሂል ኮርስ የአቀራረበና የአተገባበር ፍተሻ::" አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ማረው አለሙ::(1887):: "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግል እና በቡድን የሚፃፍ በሳል ዳርሰቶች ንፅፅራዊ ጥናት::" አደስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ሰለሞን ዩሐንስ:: (1991):: "የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስትራቴጂና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞሽ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ስዩም ከበደ:: (1988):: "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት::" አደስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ቅዱስ ሀብት በላቸው፡፡ (2004)፡፡የፅናት ተምሳሌቶች፡፡ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ፡፡ /ያልታተመ/

ተመስገን ፈቀደ:: (2001):: "የ11 ክፍል መምህራን የፅህፈት ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብላሃት ተዛምዶ::" (በሃድያ ዞን በሾኔ መሰናዴ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ (የተካሄደ ጥናት):: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ /ያልታተመ/::

ተካልኝ ለማ፡፡ (2009)፡፡ ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና አመለካከት ላይ የሚኖረው ተፅህኖ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በምዕራብ ሸዋ አካባቢ በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

አስቴር ሳሙኤል:: (1998):: የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ /ያልታተመ/::

ክብሩ ታያቸው፡፡(2006)፡፡ "በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ስልት የመምህራን የማስተማር ዘዴ አተገባበር"ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት /ያልታተመ/::

ክፍሌ ሀብተማሪያም::(1986)::“የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታ::” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ድግሪ የቀረበ ጥናት::

ዳባሽ ዮሐንስ፡፡ (2011)፡፡ በሒደታዊ ዘውግ ማስተማር ዘዴ መፃፍን ለማሻሻል ያለው ሚና በሠቃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ አፈ-ፈት በሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት::ጅማ ዩኒቨርሲቲ አማርኛን ቋንቋ በማስተማር ስነ ዘዴ ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ክፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2005) ፡፡ የስነጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ዮናስ ስዩም (2001)፡፡ የጽፈት ምንነት፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተመሪያ የተዘጋጀ /ያልታተመ/፡፡

Abduh Nasser(2018),Teaching the writing to Yemeni EFL learners: the importance and challenges. South-Asia Journal of multidisciplinary Studies. Volume 3

Atkinson, D. (2003). ‘’L2 Writing in the post process era, Introduction on.’’ Jornal of Second Language Writing .12.3-15. 19

Badger, R. and White, G. (2000) ‘’Product, Process and Gener: Approaches

Best,J.W and Khan,J.V.(1993). Reaserch in education. Needham heights,

Brown (2001). Teaching by Principle: An Interactive Approach to Language University Press. University press.

Byrne, D. (1990).Teaching Writing Skills. London: London: Routledge

Carroll, R.T., 1999. Writing Skills. Students Success Guide. The Skeptic’s Dictionary at www.skepdic.com(Accessed on November 7/2022).

Conner,U &Karen,A .(1997). “Peer response group in ESC Writing class. How much impaction revition? “jornal of language writing. 3(3).257-276.

Creswell, J. W. (2012). **Educational research:** Planning, Conducting and Evaluating Quantitative and Qualitative Research.(4th ed.).Pearson: Pearson Education, Inc.

Carrol.J.A. & et.al (2001).Writing and Grammar:Communication in Action.Prentice Hall.

Frankel, J. and Norman, E. Wallen (1990). How to Design and Evaluate

Gay L. R, Geoffrey E. Mills, Peter, A. (2012).**Educational research**: Competencies for Analysis. London: Rutledge Flamer.

Harmond.J and Drewianka,B (2001).Gener in R.Carter& D.Nunan (eds).The Cambridge guide to teaching English to speakers of other language. Cambridge: Cambridge university press.

Hedge, T. (1988) Writing Resource Book for Teachers. Oxford: Oxford

Hyland, K. (2002). "General in Primary Classrooms: The New Souther Wales (NSW) k-6 Syllabus". Inc N. Candlin and D.R. Hall (Eds). Teaching and Researching (pp. 96-103) Harlow. ESSEX.

Janet, E (2003) Writing as model of Learning, JESOL QUARTWRLY, Vol. 37/21 p. (345-35).

Kroll (ed) Cambridge: Cambridge University Press.

Mojica, L.A., 2010. Effective Report Writing. Newbury Park, CA:Sage.

Pedagogy. (2nd ed), New York: Addison wesly Longman,

Raimes. A. (1983) Techniques in the teaching writing.

Research in Education. New York: McGraw Hill inc.

Silvia T. (1990). Second Language Composition instruction second language writing in Barbara Kroll (ed) Cambridge: Cambridge University.

Walsh. K.(2010). The importance of writing skills-online tools to encourage success.

Willson,G. (2003). Learning through interaction. Cambridge: Cambridg

# አባሪዎች

# በአዱስ አበባ ዩኒቨርስቲ ማሕበራዊ ሣይንስና ስነ-ሰብዕ፣ የተግባቦት ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ጽሑፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## አባሪ አንድ

## መግቢያ

በዚህ አባሪ ስር የተለዩት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች አጠቃላይ መረጃዎች ለምሳሌ፡- ጾታ፣እድሜ፣በአማርኛ ት/ት የክፍል ውስጥ ውጤት መሰረት ያደረገ የተማሪዎች ምድብ ማለትም ከፍተኛ በላይ የስመዘገቡ መካከለኛ ደረጃ ያላቸው እና ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸውን ተማሪዎች እንዲሁም አማርኛ አፍመፍቻ ቋንቋ የሆናቸው እና አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ ቋንቋ ቸው የሆኑ ተማሪዎችን መረጃ በሚከተለው መልኩ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ይህ መረጃ ያስፈለገበት ምክንያት ጥናቱ የተሟላ እንዲሆን እና የሚገኘው ውጤት ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን በሚል ነው፡፡

5. **የሙከራ ቡድን** ብዛት፡- ወ= ሴ= ድ=

   **የቁጥጥር ቡድን ብዛት፡-** ወ= ሴ= ድ=

6. **ከሙከራ ቡድኑ፡-** ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ= ሴ= ድ=

   መካከለኛ ደረጃ ላያ ያሉ ተማሪዎች፡-ወ= ሴ= ድ=

   ዝተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ= ሴ= ድ=

   **ከቁጥጥር ቡድኑ**፡-ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ= ሴ= ድ=

   መካከለኛ ደረጃ ላያ ያሉ ተማሪዎች፡-ወ= ሴ= ድ=

   ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች፡- ወ= ሴ= ድ=

7. **አማርኛ አፍ መፍቻ** ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች፡-

   **የሙከራ ቡድን፡-**ወ= ሴ= ድ=

   **ከቁጥጥር ቡድኑ፡-** ወ= ሴ= ድ=

8. **አማርኛ የሁለተኛ ቋንቋቸው** የሆናቸው ተማሪዎች፡-

   **የሙከራ ቡድን፡-**ወ= ሴ= ድ=

**ከቁጥጥር ቡድኑ፡-** ወ=          ሴ=        ድ=

# አባሪ ሁለት

## የፅህፈት ቅድመ እና ድህረ ፈተና

## በአዱስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሂዩማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍ ክፍል ትምህርት ክሌጅ

# መግቢያ

በዚህ ክፍል ሁለቱ ለጥናት የተመደቡት ክፍሎች ማለትም የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖች ምንም አይነት የማስተማር ዘዴ ልዩነት ሳይደረግ ወይም በተለምዶዊው ማለትም መ/ራንን ለዚህ ጥናት ተማሪዎች ከመመረጣቸው በፊት በነበረው የማስተማር ሂደት ሲጠቀሙበት በነበረው የማስተመር ሂደት አማካይነት ሲማሩ በነበረው አካሄድ በመጻፍ ክሂል በተመለከተ ተማሪዎች የነበራቸውን የእውቀት ልኬት እና ደረጃ ለመለየት እንዲቻል እና የሙከራዉ ሂደት ሲተገበር የተገኘውን ውጤት በአግባቡ በመመዘን ታማኒነት ያለው መድደሚያ ለመስጠት የሚያስችል የጥናት ውጤት ለማስመዝገብ ይቻል ዘንድ የተከናወነ ሂደት ነው፡፡
ለምዘናው የቀረበው የጥናት ጥያቄ

**ስም ........................................**
**ትምህርት ቤት... አጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**
**ክፍል፡- 9ኛ**
**ቀን...**
**የተፈቀደው ጊዜ ፡-አንድ ሰዓት**
**የተሰጠው ነጥብ ፡-100%**

**አጠቃላይ ዓላማ**

የዚህ ፈተና ዋነኛ ዓላማ የሂደተ ዘውጋዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ መሻሻል አለማሻሻሉን ለመፈተሽ የሚረዳ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችል ነው፡፡

ፈተናው 32 ጥያቄዎች ያሉት ሲሆን በአምስት ትዕዛዛት የተከፋፈለ ነው፡፡ጥያቄዎቹን በተገቢው ሁኔታ አንብባችሁ እንደየትዕዛዛቸው ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

## ምንባብ

### እውነት

አባቱ አቶ አየለ የሞቱት÷ስሱ ገና የአራት አመት ህፃን ሳለ ነበር፡፡አቶ አየለ አይተንፍሱ÷ገልቱ ለልጃቸው ነገ÷የማያስቡ ሰው ሆነው አልነበረም÷አደማሱ ከአደገበት ከተማ አንዲት ጎጆ÷ ወይም ለአንዲት ጎጆ መቀለሻ÷ኩርማን መሬት ያጣው፡፡ እንዲያውም አቶ አየለ÷ትጉህ ሰራተኛ÷የመጨረሻው ቀልጣፋ ነጋዴ ነበሩ፡፡ ነገርግን አንዳንድ ለሀብት ያልታደሉትን ሰዎች÷የሚገጥም እድል ገጥሟቸው፤በዘመናቸው ሊያፈሩት የቻሉት ገንዘብ÷ከእጅ ወደ ጉሮሮ እንጂ÷ወደ ልጅ የሚያልፍ አልነበረምና ነው፡፡

ይሁን እንጂ አድማሱ እንዲህ ቀላል ልጅ አልነበረም እርግጥ ከትምህርት ቤት ሲወጣ ኑሮ ጭንቀት ሆኖበት ነበር፡፡ ነገርግን ሁሉንም እያደር ሁሉንም በቶሎ ተላመደው፡፡ ደግሞም ዋናው ነገር÷ወዲያውኑ እራሱን አራሱው ብቻ÷ሰው ማድረግ እንዳለበትአወቀ፡፡ግንባሩ አቧራ እስኪያነሳ ድረስ÷ እጅ ይነሳ ÷ በየትልልቁ ሰው ደጅ ማልዶ እየሄደ ÷ ፊቱን በማስመታት÷ ዘመድ ይገዛ ጀመር፡፡ከዚህ በላይ ደግሞ በቁጠባ ረገድ በጣም ጎበዝ ነበር፡፡ስራ በያዘ በሁለት አመቱ÷እንደምንም ጥርሱን ነክሶ ሁለት ሺህ ብር አጠራቅሞ÷ቀበና ቀበሌ ሜትር ካሬውን በአምሳ ሳንቲም ሂሳብ ÷ አራት ሺህ ካሬ ሜትር መሬት ገዛ፡፡ይህም መሬት በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ÷ካሬ ሜትሩ አምስት ብር ገባ፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንዲያውም ከአንድ ሁለት ዓመት በኋላ አስር ብር ድረስ ይወጣል ብለው ተናግረው ነበር፡፡ ነገር ግን አድማሱ እስከዚያ ድረስ ሳይጠብቅ÷ ሶስቱን ሺህ ካሬ ሜትር መሬት÷ በአስራ አምስት ሺህ ብር ሂሳብ ሸጦ÷ወዲያውኑ በሰባት ሺህ ብር÷ ምን የመሰለ ባለ ስምንት ክፍል የሆነ ቤት÷ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ሠራ፡፡ በሁለቱ ሺህ ብር ደግሞ÷ የሚያምሩ ለቤቱ ተስማሚ የሆኑ ሙሉ የቤት እቃዎች ገዛ፡፡ጥቂት ቆየት ብሎ ደግሞ ÷ ትንሽ እንደተደላደለ÷ በአራት ሺህ ሁለት መቶ ብር ሂሳብ አንዲት ቆንጆ መኪና ገዛ፡፡ከዚህ በላይ ደግሞ በሰራውና በግብርገብነቱ÷ በአላፊዎች ዘንድ በጣም የተመሰገነና ለከፍተኛ ደረጃ የሚታጭ ነበር፡፡በዚህ ጊዜ የወር ደሞዙ መጀመሪያ ከተቀጠረበት ከአንድ መቶ ሀምሳ ብር÷ አራት መቶ ሀምሳ ብር ደርሶ ነበር፡፡በአጭሩ ሕይወት ወይም ኑሮ

ለአድማሱ በዚህ ጊዜ፥ "የአባቶችን ኃጢአት በልጆች የሚቀጣ።" የሚለው መሆኑ ቀርቶ- "የባቶችን ጉዳት በልጆች የሚክስ።" መስሎት ነበር።

(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሁፍ መሰረታውያን፣ 2005፣ ገፅ 254-255)

I. ለሚከተለት ቃላት በፅሁፍ ውስጥ በገቡበት አውድ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺዎችን በመምረጥ መልሱ::

…….. 1. ገልቱ ሀ) ብርቱ ነገን አሳቢ ለ) የሕይወት ተሞክሮ ያለው ሐ) ቅን አሳቢ መ) ሰነፍለነገ የማያስብ

……….2. ኩርማን ሀ) ትልቅ መሬት ለ) ለም መሬት ሐ) አረዳ መሬት መ) ትንሽ መሬት

……….3. ከእጅ ወደ ጉሮሮ ሀ) የተትረፈረፈ ለ) የሚጣፍጥ ሐ) ከእለት ፍጆታ የማይተረፍ መ) ወደ ልጅ የሚልፍ

…….. 4. እጅ መንሳት ሀ) ማመስገን/ማክበር ለ) መገላመጥ ሐ) መግፋት መ) መጥላት

…….. 5. ማለደ ሀ)ለመነ ለ)በጠዋት ተነሳ ሐ)አረፍዶ መ) ውሎውን

…….. 6. የሚታጭ ሀ)ለክፋት የሚታሰብ ለ) የሚጠቀር ሐ) ለትልቅ ደረጃ የሚታሰብ መ) የሚያገባ

II- የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሉ የምትሞሏቸው ቃላት በቀኝ በኩል የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን አለባቸው::

7.ፋናዬ የአባቷን ……… አልሰማችም።/አረፈ/

8. የሞተ …….፣ ቀሪ ምን አለበት?/ጎዳ/

9. ………… የሚሰማው መሪ ህዝብን ጆሮ ዳባ ልበስ አይልም።/ኃላፊ/

10. ሰራዊቱ የያዘውን ቦታ ………….. ታዘዘ።/ነቀለ/

11. ጣይቱ ……. ናት፤የሴት ሁሉ ቁንጮ እሷ ናት።/ሞያ/

12. ልበብር ለሆነ ሰው ቅኔ መዝርፍ ብዙ ግዜ ……….. ይችላል።/ወሰደ/

III. የሚከተለትን ቃላት ትክክለኛ አውዳቸውን በመፈለግ አስገቡና አንቀፁን አሟሉ።

| ይገልጻሉ | መርህ |
|---|---|

| | |
|---|---|
| ባህላዊ | ሳይንሳዊ |
| ሲመረጡ | ሊካተቱ |

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ 1 የሚገባቸው ቃላት ከመምረጥ ጀምሮ ለተማሪው በሚመች መንገድ ማደራጀትንና ለተሳትፎ የሚጋብዙ መልመጃዎች የሚቀናበሩበትን ያካትታል። ተግባራቱም 2 በሆነ የቃላት ትምህርት 3 ላይ ተመስርቶ ማዘጋጀትንና ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት ያብራራሉ። በተጨማሪም ቃላቱ 4 ሲደራጁና መልመጃዎቹ ሲቀረፁ ከተማሪው 5 ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ሙህራን 6።

**IV. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቴ በሚል ርዕስ ከሰምንት ዐረፍተ ነገሮች በላይ የተገነባ አንድ አንቀፅ ፃፉ**

- ትምህርት ቤቱ የሚገኝበትን ክልል፣ ዞን ፣ወረዳ ወይም ከተማ
- ስፋት፣የአካባቢው የአየር ሁኔታ
- የትምህርት አሰጣጡ

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------

## V. ስለአጋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድርሰት ፃፉ

**ስም ………………………………….**

**ትምህርት ቤት… አጋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት**

**ክፍል፡- 9ኛ**

**ቀን…**

**የተፈቀደው ጊዜ ፡-አንድ ሰዓት**

**የተሰጠው ነጥብ ፡-100%**

**አጠቃላይ ዓላማ**

የዚህ ፈተና ዋነኛ ዓላማ የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ መሻሻል አለማሻሻሉን ለመፈተሽ የሚረዳ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችል ነው፡፡ ፈተናው 32 ጥያቄዎች ያሉት ሲሆን በአምስት ትዕዛዛት የተከፋፈለ ነው፡፡ጥያቄዎቹን በተገቢው ሁኔታ አንብባችሁ እንደየትዕዛዛቸው ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

## የህይወት ታሪክ

## ፅናት ያላት አትሌት

ሀምሌ 12 ቀን 1975ዓ.ም  በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደች፡፡ ለወላጆቿ **የበኩር ልጅ** ናት፡፡ ሶስት እህቶችና ሁለት ወንድሞች አሏት አባቷ አነስተኛ የወር ደሞዝ ነበራቸው በዚህ የተነሳ በህፃንነት እድሜዋ ከትምህርቱዋ ጎን ለጎን የቤተሰቧን ችግር ለማቃለል ብዙ ጥረት አድርጋለች፡፡ በእድሜዋም ሆነ በአካል እያደገች ስትመጣ በግንባታ ስራ ውስጥ ተቀጥራ ሰርታለች ፡፡ ጀሪካን ተሸክማ ውሃ በመቅዳት፣ ወደ ጫካ እየሄደች ለምግብ ማብሰያ የሚሆን ቅጠል በመልቀም ቤተሰቦቿን ተረዳ ነበር ፡፡ በአጠቃላይ ኑሮን ለማሸነፍ እጅግ ፈታኝ የሆነ ሂወት አሳልፋለች፡፡ እቺ **ብርቱ** ወጣት አትሌት መሰረት ደፋር ትባላለች፡፡

በዚህ ፈተኝ ሁኔታ ውስጥ ያደገችው መሰረት ወደ ሩጫው አለም የገባችው **በለጋነት** እድሜዋ ነበር የአትሌቲክስ ተሰጦኦ ጎልቶ የወጣው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱዋን በመከታተል ላይ እያለች ነው በወቅቱ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሁም በወረዳና በዞን በኩል በሚደረጉ የሩጫ ውድድሮች 800 ሜትር፣ 1500 ሜትርና በ3000 ሜትር እርቀቶች ተካፍላ በተደጋጋሚ አሸናፊ ሆነች። በሩጫ ያላትንም ተስፋ ተገነዘበች።

ተስፋዋንና ምኞቱዋን ለማሳካት ከቀድሞው በበለጠ ልምምዷን ማጠናከር ጀመረች በዚህም ጊዜ ቢሆን ልዩ ልዩ ችግሮች ያጋጥሙዋት ነበር። ችግሮቹን ግን **በፅናት** ተቋቁማ በልምምድ ላይ እንዳለች ለስኬቱዋ በር ከፋች የሆነ አጋጣሚ ተፈጠረ። በአዲስ አበባ እስታዲየም ለአበበ ቢቂላ መታሰቢያ  በተዘጋጀ ውድድር ላይ በ5000 ሜትር ተሳትፋ አሸናፊ ሆነች። ይህንን ብቃቷን ያየው የባንኮች አትሌቲክስ ቡድን ዋና አሰልጣኝ የቡድኑ አባል አደረጋት። የባንክ ቡድኑን ከተቀላቀለች በኋላ በእቅድ ላይ የተመሰረተ ልምምዷን በትጋት አከናወነች። ለምምዷን ከልብ በመነጨ ፍላጎት መስራቷና ፅናቷ በሀገር ውስጥ ውድድሮች በተከታታይ የአሸናፊነት ክብር **ለመቀናጀት** አበቃት።

ካላት ብቃት አንፃር ብዙም ሳትቆይ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ የአትሌቲክስ ቡድን ተመረጠች። ገና በጠዋቱ ሀገሯን በሩጫ ለማስጠራት የነበራት ምኞትና ቁርጠኝነት በመሳካቱ ተደሰተች። የመጀመሪያዋ የሆነውን ሀገር አቀፍ ውድድር ለማድረግ ሀምሌ 1991 ወደ ፖላንድ አመራች በ3000 ሜትር እርቀት ተወዳድራ ሁለተኛ ወጣች። ይህም በአለም አቀፍ ውድድር የመጀመሪያው አኩሪ ውጤቱዋ ሆኖ ተመዘገበላት። ከዚህ በኋላ ሀገሯን በመወክል በርካታ ውድድሮች ላይ ተሳትፋለች። በተለያዩ ርቀቶችም በመወዳደር የአንደኝነት ድልን በመቀናጀትና አያሌ አኩሪ ድሎችንም በማስመዝገብ የሀገሩዋ ሰንደቅ አላማ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረገች አትሌት ናት።

(ቅዱስ ሀብት በላቸው 2004 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

I.ለሚከተለት ቃላት በፅሁፍ ውስጥ በገቡበት አውድ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺዎችን በመምረጥ መልሱ::

…….. 1. የበኩር ልጅ ሀ) ጀግና ልጅ  ለ) የመጀመሪያ ልጅ  ሐ) የመጨረሻ ለጅ
መ) ሁሉም

……….2. ብርቱ ሀ) ፈሪ ለ) ችግረኛ ሐ) ጠንካራ  መ) ቸልተኛ

……….3. በፅናት  ሀ) ሳታቋርጥ  ለ) ሳትሰለች  ሐ) በትጋት መ) ሁሉም መልስ ይሆናል

……….4. በለጋነት ሀ) በጨቅላ ዕድሜ ለ) በጉልምስና ሐ) ስታረጅ መ) በሳል ስትሆን

…….. 5. በመቀናጀት ሀ) አብሮ በመሆን ለ) ሽልማት በምግኘት ሐ) በማበር መ) ሀ ና መ መልስ ናቸው

…….. 6. አያሌ ሀ)የበላይ ለ)ትንሽ ሐ)የመጀመሪያ መ) ብዙ

II- የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሉ የምትሞሏቸው ቃላት በቀኝ በኩል የሚገኙት ቃላት ዘሮች መሆን አለባቸው::

7.ሽማግሌው ……….. የማይገባ ስራ ቀለለ፡፡/ስራ/

8. የስራ ……… ያለው ሰው ለስራ አይቸገርም፡፡ /ለመደ/

9. ሰራዊቱ የያዘውን ቦታ ………….. ታዘዘ፡፡/ነቀለ/

10.ሌባው ………. ባላፊ አግዳሚው ታወቀ፡፡/ተያዘ/

11.ይህንን ያገጠጠ እውነት ሌላ ……. አንችልም፡፡/አለ/

12.ገንዘብ ከሚቀመጥ ………….. ትርፍ ያመጣል፡፡/ሰራ/

III,የሚከተለትን ቃላት ትክክለኛ አውዳቸውን በመፈለግ አስገቡና አንቀፁን አሟሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ውድድር | መአረግ |
| የያዘችውን | በቃች |
| ፈጥና | በማሻሻሏ |

በአለም የርቀት ሪከርድ ባለቤትም ለመሆን ………..፡፡ ከአንድ አመት በሁዋላም ጃፓን ላይ በተደረገው ውድድር ቀደም ሲል ………. ሪከርድ አሻሽላለች ፡፡ ጥር 26 ቀን 1999ዓ.ም በጀርመን ስቱትጋርት በ3000 ሜትር የቤት ውስጥ ………ተሳትፋ አዲስ ሪከርድ አስመዝግባለች፡፡ ግንቦት 12 ቀን 1999ዓ.ም በአሜሪካ ካሊፎርኒያ የሁለት ማይል ሩጫ ውድድር ተካፍላ ……….. በመግባት ሪከርድ አስመዝግባች፡፡ ቤልጂም ላይ ይህንኑ ሰአት ……………. ከአለም አቀፍ የአትሌቲክስ "የአመቱ ምርጥ አትሌት" የሚል ……….. አግኝታለች፡፡

IV.የእኔ ሕይወት ታሪክ በሚል ርዕስ ከስምንት ዐረፍተ ነገሮች በላይ የተገነባ አንድ

**አንቀፅ ዓፉ**

- የተወዳችሁበትን ዓመተምህረት፣ቦታ
- ከማን እንደተወለዳችሁ(እናትና አባት)
- ትምህርት በስንት አመት እንደገባችሁ እና አሁን በምን ሁኔታ ላይ እንዳላችሁ

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------

V. ስለአጋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድርሰት ዓፉ

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------


-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------

# አባሪ ሶስት

## የቅድመ ፈተና እና የድህረ ፈተና የተማሪዎች የፅሁፍ ምዘና ናሙና



ስም እስክንድር ጉራ   ክፍል 9ኛ A

ቁጥር 6

(ቅጽል ብዛት)

## የህይወት ታሪክ

እኔ እስክንድር ጉራ እገልፃለሁ ስለ ራሴ የተወለድኩ እና ያደግኩ የህይወት ታሪኬ ... በ 2000 ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም ተወለድኩ:: የተወለድኩበትም አካባቢ ... ቀበሌ ... የኖርሁበት አካባቢ ... የሚባል አካባቢ ነው::

እኔ ... በ 2007 ለኢትዮጵያ ሚሌኒየም ትምህርቴን ... የ1ኛ ደረጃ ትምህርቴን ... ትምህርት ቤት ነው:: ... ትምህርት ቤት ... ነው::

... የህይወት ታሪክ ... 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ... 9ኛ A ክፍል ... ::

5.5/10

አስተያየት

1. ... (1) 0.5
2. ... (1) 0.5
3. ... (1) 0.5
4. ... (1) 0.5
5. ... (1) 1
6. ... (1) 0.5
7. ... (1) 1
8. ... (1) 0.5
9. ... (2) - 0.5

[illegible] ስም [illegible] ክፍል [illegible]

(ጅዕዜሬ ልምር)

## የሀገር ፍቅር ስሜትና [illegible]

የሀገር ፍቅር ስሜት ማለት [illegible] ... [illegible] የሀገር ፍቅር ስሜት [illegible] !!

[illegible] የሀገር ፍቅር [illegible] ... [illegible]

የሀገር ፍቅር [illegible] ... [illegible] የሀገር ፍቅር ስሜት [illegible] !!

የሀገር ፍቅር ስሜት እንደ [illegible] ... [illegible]

[illegible] ... [illegible] !!

**አስተያየት**

1. አርዕስትን አጠቃቀም (1) - 1
2. ቃላትን በትክክል መፃፍ (1) - 0.5
3. የሀሳብ ፍሰት (1) - 1
4. አንቀፅ ቃላትን ለተገቢ ሀሳብ መጠቀም (1) - 1
5. የአንቀፅ ቅርፅ (1) - 1
6. የቃላት ምርጫ (1) - 1
7. የእጅ ፅሁፍ (1) - 1
8. ስርዝ ድልዝ መኖር (1) - 0.5
9. መንደርደሪያ እና መቋጫ አንቀፅ ተገቢነት (2) - 2

8/10

[illegible]

ስም አበዲ ጉሩ
ክፍል 9ኛ A
ቁጥር 6

ደረጃ ዕትና

# አበዲ ጉሩ ማነው?

እሺ ስለ እኔ የዝላ የሬመን ታሪክ መረጃ ለክፍለቹሁ፡፡ አበዲ ጉሩ እባላለሁ፡፡ እኔ ከአባቴ ጉሩ ገመቹ እና ከእናቴ ዘማን ከጠላ በ2000 ዓ.ም በአጋሮ ከተማ 01 ቀበሌ ተወለድኩ፡፡ ከዚያ በመቀጠል ስለ ትምህርቴን እና አሁን ስላለሁበት ሁኔታ እንደሚከተለው እገልፃለሁ፡፡

በ2007 ዓ.ም ዕድሜዬ ሰባት አመቴ ሲሞላኝ በአጋሮ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባሁ፡፡ ከ1-8ኛ ክፍል በአርአያነቴ ተምሬ [illegible] በአርአያነቴ ቆይቼ የነበረሁበት እና በተለያዩ [illegible] የሚጠቀሙበት በመሆኑ ትምህርት ቤቱ እና ለሌላ ተማሪ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን መጨረስ [illegible] በአጋሮ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብዙ የለፋሁት [illegible] መምታት አልቻልኩም፡፡ ግን ደረጃዬ ተምሬ አላፍኩ ከዚህ በፊት የነበረ በደረጃ እና በሰፈር መሞላት እየቻልኩም፡፡ ለአሁን [illegible] በአጋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዘጠነኛ ክፍል ተመዝግቤ [illegible] እገኛለሁ፡፡

ለወደፊቱ ያሰብኩት የሕይወቴ የዝላ የሬመን ታሪክ ምኞቴ ማሳካት ነው፡፡ እኔ አበዲ ከሆንኩ ተመረቅ ዶክተር ሆኜ [illegible] የምረዳበት ትምህርቴን ሀሳብ ስላልተሟላ [illegible] ትምህርቴ [illegible] ላይ እመራመራለሁ፡፡

## አስተያየት

1. ሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም (1)-0.5
2. ቃላትን በትክክል መፃፍ (1)-0.5
3. የሀሳብ ፍሰት (1)-1
4. [illegible] ቃላትን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም (1)-0.5
5. የአንቀፅ ውቅር (1)-1
6. የቃላት ምርጫ (1)-1
7. የእጅ ፅሁፍ (1)-0.5
8. ስርዝ ድልዝ አለመኖር (1)-0.5
9. የመንደርደሪያ መጠቃለያ እና ቁጥር ተገቢነት (2)-2

7.5/10

ጥሩ መሻሻል ያሳየ [illegible]

# አባሪ አራት

## መግቢያ

በዚህ ስር ለማስቀመጥ የተቻለው የጽህፈትን ክሂል ተማሪዎች ሲማሩ የነበረበትን እና መ/ራንን ሲያስተምሩበት የነበረውን ሂደት ለማሳየት ይቻል ዘንድ የተማሪዎች እና የመ/ራን ሚና በሚል ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለተማሪዎች በማድረስ መረጃዎች የተሰበሰቡበት መጠይቅ እንደሚከተለው የተቀመጠው ነው፡፡

ይህ የጹሑፍ መጠይቅ ለሁለት ጊዜ ለተማሪዎች በመስጠት መረጃ ይሰበሰባል ይህም ማለት ለሙከራ ቡድኑ ሂደተ-ዘዉጋዊ የማስተማር ዘዴ ሳይተገበር ከሁለቱም ቡድኖች ማለትም ከቁጥጠር ቡድኑ እና ከሙከረራ ቡድኑ መረጃ ይሰበሰባል በመቀጠል ለሙከራዉ ቡድኑ ሂደተ ዘውጋዊ የማስታመር ዘዴ ከተተገበረ በኂላ ያለውን ለውጥ ወይም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን ለውጥ ለማየት ለመለየት መረጃው በድጋሚ ከሁለቱም ቡድን ይሰበሰባል፡፡ ይህ ሂደትም ለውጥን ለማየት ስለሚያግዝ እና ከጥናቱ አላማ አንጻር የሚገኘውን ውጤት ለማወቅ ስለሚያግዝ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ መረጃው ይሰበሰባል ማለት ነው፡፡

**ተማሪዎችን** የጽህፈትን ክሂል ለመማር የነበራቸውን ሚና መለኪያ መጠይቅ

ይህ የጹሑፍ መጠይቅ ለሁለት ጊዜ ለተማሪዎች በመስጠት መረጃ ይሰበሰባል ይህም ማለት ለሙከራ ቡድኑ ሂደተ-ዘዉጋዊ የማስተማር ዘዴ ሳይተገበር ከሁለቱም ቡድኖች ማለትም ከቁጥጠር ቡድኑ እና ከሙከረራ ቡድኑ መረጃ ይሰበሰባል በመቀጠል ለሙከራዉ ቡድኑ ሂደተ ዘውጋዊ የማስታመር ዘዴ ከተተገበረ በኂላ ያለውን ለውጥ ወይም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለውን ለውጥ ለማየት ለመለየት መረጃው በድጋሚ ከሁለቱም ቡድን ይሰበሰባል፡፡ ይህ ሂደትም ለውጥን ለማየት ስለሚያግዝ እና ከጥናቱ አላማ አንጻር የሚገኘውን ውጤት ለማወቅ ስለሚያግዝ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ መረጃው ይሰበሰባል ማለት ነው፡፡

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | ከፍተኛ(4) | መካከለኛ(3) | ዝቅተኛ(2) | በ.ዝቅተኛ(1) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአማርኛ መዝገበ ቃላት የማንበብ ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 2 | በልዩልዩ ርእሶች ዙሪያ በራስ ተነሳሽነት ድርሰት የመጻፍ ልምድህ/ሽ ምን ይመስላል? | | | | | |
| 3 | የቃላት ትርጉምን በማወቅ በኩል ያለህ/ሽ | | | | | |

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | ከፍተኛ(4) | መካከለኛ(3) | ዝቅተኛ(2) | በ.ዝቅተኛ(1) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ልምድ እንዴት ይገለጻን? | | | | | |
| 4 | በትርፍ ሰዓት አጫጭር ድርሰቶችን በመጻፍ ከጓደኛ አስተያየት የመቀበል እና የማስተካከያ ሁኔታህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን በምታስተምርበት ወቅት የመከታተል ፍላጎትህ/ሽ ምን ይምስላል? | | | | | |
| 7 | ለጽህፈት ክሂል ለመማር ያለህ/ሽ ፍላጎት እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 8 | በአንድ ርዕስ ላይ የተጻፈን ጹሁፍ ደጋግሞ በመጻፍ እና በማስተካከል በኩል ልምድህ/ሽ እንዴት ነው? | | | | | |
| 9 | መ/ሩ/ሯ የሰጠችህን/ሽን አስተያየት በመቀበል እና በማስተካከል እንደገና ለመ/ሩ/ሯ የማሳየት ልምድህ/ሽ እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 10 | የጽሁፍ ክሂልን ለመማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይዘህ/ሽ እንድትመጪ መ/ሩ/ሯ ሲያዙ ይዞ የመገኘት ልምድ እንዴት ይገለጻል? | | | | | |
| | | | | | | |

የመ/ሩ ሚና

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | ከፍተኛ(4) | መካከለኛ(3) | ዝቅተኛ(2) | በ.ዝቅተኛ(1) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂሊን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ይዘው በክፍል ውስጥ ከመገኘት አንጻር | | | | | |

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | ከፍተኛ(4) | መካከለኛ(3) | ዝቅተኛ(2) | በ.ዝቅተኛ(1) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | እንዴት ይገለጻሉ? | | | | | |
| 2 | መ/ሩ/ሯ የጽሑፍ ክሂልን ወይም ድረሰትን ለማስታመር የትርፍ ሰዓት የማስተማር ሁኔታቸው እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 3 | የተማሪዎችን የድረሰት ጽሁፍን በመመልከት ተከታታይነት ያለው ግብረመልስ የመስጠት ሁኔታቸው አንዴት ይታያል? | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች የድረሰት ጽሑፉን እንዲለማመዱ የሚደረግበት አካሄድ እና የድጋፍ ሁኔታ እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 5 | ተማሪዎች በቡድን ሆነው ድረሰት እንዲጸፉ በማድረግ በኩል የመ/ራን ድርሻ አንዴት ይታያል? | | | | | |
| 6 | ተማሪዎች እርስ በእረስ አስተያየት እየሰጡ የጽሑፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ በማደረግ በኩል አንዴት ይታያል? | | | | | |
| 7 | የድረስት ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ተጨማሪ እገዛ በመስጠት በኩል የመ/ሩ ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 8 | ተማሪዎች ድረሰት እያዘጋጁ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን | | | | | |

| ተ.ቁ | ሚና | በ.ከፍተኛ(5) | ከፍተኛ(4) | መካከለኛ(3) | ዝቅተኛ(2) | በ.ዝቅተኛ(1) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በማበረታታት በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሻ እንዴት ይታያል? | | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በቤታቸው የጻፉትን ድርሰት በመመልከት እና በማስተካከል በት/ቤቱ ሚኒሚዲያ እድንዲያቀርቡ በማድረግ በኩል የመ/ሩ/ሯ ድርሻ እንዴት ይገለጻል? | | | | | |
| 10 | | | | | | |

# አባሪ አምስት

## ምልከታ

በክፍል ውስጥ የመ/ራን እና የተማሪዎችን ሚና ለመለየት እና በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ለማመሳከር እና ቡከራ ቡድኑ ላይ የተተገበረውን የሂደተ ዘውጋዊ አተገባበር እና ተልምዷዊ የድረሰት ወይም የጽሑፍ የማስታመር አካሄድ እና ውጤት ላይ የመጣውን ለውጥ ወይም የተገኘውን ውጤት ከቁጥጥር ቡደኑ አንጻር በማነጻፀር የጥናቱን ውጤት ለማስቀመጥ ይቻል ዘንድ ይህን የምልከታ ቼክሊሰት በማዘጋጀት እና የክፍል ምልከታ ከመ/ራኑ ጋር በመስማማት እና  በማድረግ እንዲሁም ተማሪዎችን ከክፍል ውስጥ እና ውጪ ባላቸው የት/ት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለውጦችን መመዘን የሚያስችል ምልከታ ማድረግ ተችሏል ለዚህም ጥቅምላይ የዋለውን የምልከታ ቼክሊስት እንደሚከተለው ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡
ይህ የምለከታ ቼክሊስት ለሁለት ጊዜ መረጃ ይሰበሰብበታል ይህም ለሁለቱ ቡድኖች ማለትም ለቁጥጥር ቡድኑ እና ለሙከራ ቡደኑ ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በመማር ሂደት እያሉ እንዲሁም ለመ/ራን ምንም ስለጥናቱ ምንም አይነት ግንዛቤ ሳይደረግ ብክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ያሉ የመ/ራኑን እና የተማሪዎችን እንቅስቃሴ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት መሳሪያ ነው፡፡

የመልከታ ቼክሊስት

| ተ.ቁ | መለኪያ ተግባራት | አዎ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚሰጣቸው የጽሑፍ ክሂል ት/ት በቂ ተሳትፎ ያሳያሉ፡፡ | | |
| 2 | ተማሪዎች በቡድን ድረሰት የመጻፍ ልምድ አላቸው/ፍላጎት አላቸው፡፡ | | |
| 3 | ተማሪዎች ከፍተኛ የቃላት ፍቺ አቅም አላቸው | | |
| 4 | ተማሪዎች ድርሰትን የመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡ | | |
| 5 | መ/ራን ልዩ ልዩ የድረሰት ርእሶችን ለተማሪዎች በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ እንዲለማመዱ ያደርጋሉ፡፡ | | |
| 6 | ተማሪዎች በልዩ ልዩ ርዕሶች ዙሪያ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ ያበረታታሉ፡፡ | | |
| 7 | ተማሪዎች ድረሰት በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ መ/ሩ/ሯ መልካም አውድ በክፍለ ውስጥ ፈጠረዋል፡፡ | | |
| 8 | መ/ሩ/ሯ የጽሁፍ ክሂልን ሲያለማምዱ ለተማሪዎች መማር ሙሉ ነጻነት ይሰጣሉ? | | |
| 9 | | | |

# አባሪ ስድስት

የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል ለሙከራ ቡድኑ የተደረገ ድጋፍ እና ውጤትን በተመለከተ ለመመዘን የተሰራው ስራ ለመፈተሽ የተከናወኑ ተግባራት እና ከላይ የተጠቀሱትን መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ የተገኙ ለውጦችን ለማምጣት የሚከተሉት የድጋፍ ተግባራት የወይም የሂደተ ዘውጋዊ የማስታመር ዘዴ/መንገዶችን መተግበር ተችሏል።

ተግባር 1፡- ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ እና እርስ በርሳቸው አስተያየት እንዲሰጣቱ በማድረግ እንዲማር ማድረግ።(Self-Regulated Learning)

የቁጥጥሩ ቡድን መ/ሩ ቀደምት ሲያስተምር በነበረበት አካሄድ እንዲቀጥል ማድረግ።

ተግባር 2፡-ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች እና ለቁጥጥር ቡድን ተመሳሳይ በርካታ የድርሰት ርእስ በመስጠት ከተሰጧቸው ርዕሶች ውስጥ ሁለቱም ቡድኖች መርጠው እንዲጽፉ በማድረግ ለሙከራ ቡድኑ በራሳቸው እንዲገመግሙ እንዲያርሙ እና አስተያየት ጭምር በመስጠት ለመ/ራቸው በማስረከብ ተጨማሪ አስተያየት መቀበል እንዲችሉ ማድረግ በሌላ በኩል መ/ራን ለተማሪዎቹ የአማርኛ ደርሰትን የማስተማሪያ ተለምዷዊ ሂደትን በተከተለ መልኩ ማስተማር እና ውጤታቸውን መመዘን መቻል።(Metacognition)

ተግባር 3፡-የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደትን ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠሩ በማድረግ ለተማሪዎች ሙሉ የመማር ነጻነት በመስጠት የጹሑፍ ክሂልን የሚማሩበትን አዉድ ለሙከራ ቡድኖች መፍጠር መቻል።(Learner-controlled instruction)

ተግባር 4፡-የሙከራ ቡድኖች ለጻፉት ድረሰት የተሰጣቸውን ውጤት መሰረት በማድረግ ስህተታቸውን በራሳቸው እንዲፈልጉ እና ማስተካካያ በማድረግ እንዲሁም ከሳይንሳዊ የድርሰት አጻጻፍ መዋቅር ጋር በማዛመድ ለረሳቸው አስተያየት እንዲሰጡ እና ስህተታቸውን በራሳቸው እንዲያርሙ የማድረግ ሂደትን መከተል።(Calibration)

## የቅድመ ፈተና የተማሪዎች ውጤት

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 6.00 | | 1 | 4.00 | |
| 2 | 6.00 | | 2 | 5.00 | |
| 3 | 4.00 | | 3 | 5.00 | |
| 4 | 8.00 | | 4 | 4.00 | |
| 5 | 4.00 | | 5 | 6.00 | |
| 6 | 3.00 | | 6 | 5.50 | |
| 7 | 5.00 | | 7 | 4.00 | |
| 8 | 6.00 | | 8 | 5.00 | |
| 9 | 5.00 | | 9 | 6.50 | |
| 10 | 3.00 | | 10 | 3.00 | |
| 11 | 4.00 | | 11 | 3.50 | |
| 12 | 4.00 | | 12 | 3.00 | |
| 13 | 5.00 | | 13 | 4.00 | |
| 14 | 4.00 | | 14 | 3.00 | |
| 15 | 4.00 | | 15 | 4.00 | |
| 16 | 6.00 | | 16 | 5.00 | |
| 17 | 5.00 | | 17 | 3.00 | |
| 18 | 5.00 | | 18 | 4.00 | |
| 19 | 5.00 | | 19 | 5.00 | |
| 20 | 4.00 | | 20 | 5.00 | |
| 21 | 4.00 | | 21 | 4.00 | |
| 22 | 4.00 | | 22 | 4.00 | |
| 23 | 6.50 | | 23 | 5.00 | |
| 24 | 6.00 | | 24 | 4.00 | |
| 25 | 3.50 | | 25 | 3.00 | |
| 26 | 4.00 | | 26 | 4.00 | |
| 27 | 5.00 | | 27 | 5.00 | |
| 28 | 3.00 | | 28 | 5.00 | |
| 29 | 4.50 | | 29 | 4.00 | |
| 30 | 4.00 | | 30 | 5.00 | |
| 31 | 5.00 | | 31 | 4.00 | |
| 32 | 4.00 | | 32 | 5.00 | |
| 33 | 5.50 | | 33 | 6.00 | |
| 34 | 4.50 | | 34 | 3.00 | |
| 35 | 4.00 | | 35 | 4.00 | |
| 36 | 5.00 | | 36 | 5.00 | |
| 37 | 6.00 | | 37 | 6.00 | |
| 38 | 5.00 | | 38 | 4.00 | |

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 39 | 4.00 | | 39 | 3.50 | |
| 40 | 3.00 | | 40 | 5.00 | |
| 41 | 4.00 | | 41 | 6.50 | |
| 42 | 3.00 | | 42 | 5.00 | |
| 43 | 3.00 | | 43 | 6.00 | |
| 44 | 4.00 | | 44 | 6.50 | |
| 45 | 3.00 | | 45 | 3.00 | |
| 46 | 5.00 | | 46 | 5.00 | |
| 47 | 4.00 | | 47 | 6.00 | |
| 48 | 5.00 | | 48 | 6.00 | |
| 49 | 4.00 | | 49 | 5.00 | |
| 50 | 6.00 | | 50 | 3.00 | |

## የድህረ ፈተና1 የተማሪዎች ውጤት

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 5.00 | | 1 | 5.00 | |
| 2 | 7.00 | | 2 | 5.00 | |
| 3 | 5.00 | | 3 | 6.50 | |
| 4 | 8.50 | | 4 | 5.50 | |
| 5 | 4.00 | | 5 | 6.00 | |
| 6 | 5.50 | | 6 | 7.50 | |
| 7 | 4.00 | | 7 | 5.50 | |
| 8 | 5.00 | | 8 | 5.00 | |
| 9 | 6.00 | | 9 | 7.50 | |
| 10 | 5.00 | | 10 | 5.00 | |
| 11 | 5.00 | | 11 | 5.00 | |
| 12 | 6.00 | | 12 | 5.00 | |
| 13 | 4.00 | | 13 | 5.00 | |
| 14 | 4.00 | | 14 | 5.00 | |
| 15 | 4.50 | | 15 | 6.50 | |
| 16 | 5.00 | | 16 | 5.00 | |
| 17 | 6.00 | | 17 | 5.00 | |
| 18 | 5.50 | | 18 | 5.50 | |
| 19 | 4.00 | | 19 | 6.00 | |
| 20 | 5.50 | | 20 | 5.00 | |
| 21 | 5.50 | | 21 | 5.00 | |
| 22 | 3.00 | | 22 | 5.00 | |
| 23 | 6.00 | | 23 | 6.00 | |

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 24 | 5.00 | | 24 | 5.00 | |
| 25 | 4.00 | | 25 | 5.00 | |
| 26 | 5.00 | | 26 | 5.00 | |
| 27 | 4.00 | | 27 | 6.50 | |
| 28 | 5.00 | | 28 | 6.00 | |
| 29 | 5.00 | | 29 | 5.50 | |
| 30 | 4.00 | | 30 | 6.00 | |
| 31 | 5.00 | | 31 | 5.00 | |
| 32 | 5.00 | | 32 | 6.00 | |
| 33 | 5.00 | | 33 | 7.50 | |
| 34 | 4.00 | | 34 | 4.50 | |
| 35 | 5.00 | | 35 | 5.00 | |
| 36 | 3.00 | | 36 | 6.00 | |
| 37 | 4.00 | | 37 | 6.00 | |
| 38 | 4.00 | | 38 | 5.50 | |
| 39 | 3.00 | | 39 | 5.00 | |
| 40 | 4.00 | | 40 | 5.50 | |
| 41 | 6.00 | | 41 | 7.50 | |
| 42 | 5.00 | | 42 | 5.00 | |
| 43 | 4.00 | | 43 | 7.00 | |
| 44 | 3.00 | | 44 | 8.00 | |
| 45 | 3.00 | | 45 | 5.50 | |
| 46 | 5.00 | | 46 | 6.00 | |
| 47 | 4.00 | | 47 | 8.00 | |
| 48 | 6.00 | | 48 | 7.50 | |
| 49 | 6.00 | | 49 | 5.00 | |
| 50 | 4.00 | | 50 | 5.00 | |

## የድረህረ ፈተና2 የተማሪዎች ውጤት

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 5.50 | | 1 | 7.50 | |
| 2 | 5.00 | | 2 | 6.00 | |
| 3 | 4.00 | | 3 | 9.00 | |
| 4 | 7.50 | | 4 | 7.00 | |
| 5 | 3.00 | | 5 | 8.50 | |
| 6 | 4.00 | | 6 | 7.50 | |
| 7 | 3.00 | | 7 | 6.50 | |
| 8 | 6.00 | | 8 | 7.50 | |

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | 6.00 | | 9 | 9.50 | |
| 10 | 4.00 | | 10 | 5.00 | |
| 11 | 4.00 | | 11 | 6.50 | |
| 12 | 4.00 | | 12 | 5.50 | |
| 13 | 5.00 | | 13 | 7.00 | |
| 14 | 4.50 | | 14 | 6.00 | |
| 15 | 3.00 | | 15 | 7.50 | |
| 16 | 4.00 | | 16 | 8.00 | |
| 17 | 5.50 | | 17 | 5.50 | |
| 18 | 5.00 | | 18 | 6.00 | |
| 19 | 5.00 | | 19 | 7.50 | |
| 20 | 5.00 | | 20 | 6.50 | |
| 21 | 5.00 | | 21 | 5.00 | |
| 22 | 4.50 | | 22 | 5.00 | |
| 23 | 6.00 | | 23 | 6.50 | |
| 24 | 6.00 | | 24 | 5.00 | |
| 25 | 4.00 | | 25 | 6.00 | |
| 26 | 4.00 | | 26 | 5.50 | |
| 27 | 4.00 | | 27 | 8.50 | |
| 28 | 4.00 | | 28 | 7.00 | |
| 29 | 4.00 | | 29 | 6.00 | |
| 30 | 5.00 | | 30 | 8.00 | |
| 31 | 4.00 | | 31 | 6.00 | |
| 32 | 4.00 | | 32 | 9.00 | |
| 33 | 5.00 | | 33 | 9.50 | |
| 34 | 5.00 | | 34 | 5.00 | |
| 35 | 5.00 | | 35 | 5.00 | |
| 36 | 5.00 | | 36 | 7.00 | |
| 37 | 4.00 | | 37 | 8.50 | |
| 38 | 6.00 | | 38 | 6.00 | |
| 39 | 5.00 | | 39 | 5.00 | |
| 40 | 5.00 | | 40 | 6.00 | |
| 41 | 5.00 | | 41 | 9.50 | |
| 42 | 5.00 | | 42 | 8.00 | |
| 43 | 5.00 | | 43 | 9.00 | |
| 44 | 4.50 | | 44 | 9.50 | |
| 45 | 5.50 | | 45 | 6.00 | |
| 46 | 5.50 | | 46 | 7.00 | |
| 47 | 5.50 | | 47 | 9.50 | |

| የቁጥጥር ቡድን | ውጤት | | ሙከራ ቡድን | ውጤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 48 | 5.00 | | 48 | 9.00 | |
| 49 | 4.00 | | 49 | 7.50 | |
| 50 | 5.00 | | 50 | 6.00 | |

# ለድረሰት ለተማሪዎች የቀረቡ ርዕሶች

- የግል ህይወት ታሪክ
- ዱርዬው ድመት
- የበጎች እረኛ
- የወባ በሽታ
- ኤች.አይቪ.እድስ
- ቡና
- የላም ጥቅም
- ዶሮ
- ነጋዴ
- ቆሻሻ
- ከተማ እና ገጠር
- የስፖርት ጥቅም
- ሰላም
- ጎበዙ ተማሪ
- ጸሀይ
- ቋንቋ
- ውሃ
- ጤፍ
- የዱር እንሰሳት
- መስከረም ሲጠባ
- ትምህርተ ቤቴ
- የቤተሰብ ፍቅር
- የሀገር ፍቅር
- የእናት ፍቅር